አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ እና ተግባራት

በ


ተስፋዬ ሞላ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY


በሰብዓዊ ሳይንሶች ፋኩሊቲ

የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር ለኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ

የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ እና ተግባራት

በ
ተስፋዬ ሞላ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በሰብዓዊ ሳይንሶች ፋኩሊቲ
የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር ለኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ
የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ እና ተግባራት

በ
ተስፋዬ ሞላ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማካሪ
ሥርግው ገላው (ዶ/ር)

በሰብዓዊ ሳይንሶች ፋኩሊቲ
የኢትዮጵያ  ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር ለኤም.ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ
የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ እና ተግባራት

በ


ተስፋዬ ሞላ


ሰኔ 2003 ዓ.ም


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY


የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ሥርገው ገላው ________ ፊርማ ________

ፈታኝ ________ ________

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከግቡ እንዲደርስ ከትልመ ጥናት ጀምረው እስከ መጨረሻው ድረስ መፃሕፍትን በማዋስ፣ መረጃዎችን በመጠቆም ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ሥርጉው ገላው ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

መረጃ በማሰባሰብ ሂደት አብረውኝ ለደከሙና ለተባበሩኝ ለዲያቆን ምርኩዜ መሰለ፣ ለዲያቆን ዳርጌ ተካዩ እና ለዲያቆን ዳርጌ ተፈራ እንዲሁም የኮረም ወረዳ ቤተ ክህነት ገንዘብ ያዥና የመዝገብ ቤት ኃላፊ መልአከ ሕይወት አበራ ምስጋናዬ ባሉበት ይድረሳቸው፡፡

የኮረሞ ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ሰበካ ጉባኤ አባላት በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ የተፃፉ ዕሑፎች እንዳነብና በአብያተ ክርስቲያናቱ የክብረ በዓላቱን ሥርዓተ ማኅሌት በቪዲዮና በፎቶ ግራፍ እንድቀርፅ ስለተባበሩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የድህረ ምረቃ ሙሉ የትምህርት ወጪዬን በመክፈል ያስተማረኝን ወሎ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡

የጥናቱን ረቂቅ በማረምና ገንቢ ሀሳብ በመለገስ ትብብር ላደረጉልኝ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የግዕዝ መምህር ለሆኑት ለአቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ፣ እንዲሁም ለመምህር ተመስገን በየነ፣ ለመምህር ንጉሴ ገመቹ እንዲሁም የቲዎሪ መፃሐፍትን በማሰባሰብ ሂደት እገዛ ላደረጉልኝ ጓደኞቼ፣ ለኤልያስ ግዛቸው፣ ለሙሉቀን ንጋቱ፣ ለሊያ መዝገቡ፣ ለሄለን ኤፍሬም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

ከልጅነት እስከ እውቀት ተንከባክባ ላሳደገችኝ እና ላስተማረችኝ ለእናቴ ወ/ሮ ብርሃኔ አለሙ፣ እንዲሁም በሃሳብና በገንዘብ የዘወትር ድጋፋቸው ላልተለየኝ ቤተሰቦቼ ለመምህርት ክልል ሞላ፣ ለአቶ ብርሃኑ ገብሩ፣ ለብሃፍታ ወዳጅ፣ ለአቶ ያሬድ ታረቀ ፣ለጓደኛየ ሀብታሙ ገ/ሥላሴ እና ለሐፍቱ ሞላ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ የላይብረሪ መረጃዎችን በወቅቱ እንዳገኝ እገዛ ላደረገችልኝ መሰረት ደምሶ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

የጥናቱን ረቂቅ በመፃፍ እገዛ ያደረገችልኝን አርማዬ አደራን አመሰግናለሁ፡፡

## ❖ ምህፃረ ቃላትና ዝርዝራቸው

ከዚህ በታች የቀረቡት ምህፃረ ቃላት በጥናቱ ውስጥ በአገልግሎት ላይ የዋሉ ናቸው።

| ምህፃረ ቃላት | የምህፃረ ቃላት መፍቻ |
|---|---|
| ዘፍ. | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ዘፀ. | ኦሪት ዘፀአት |
| 1ኛ ዜና. | የመጀመሪያ ዜና መዋዕል |
| 2ኛ ዜና. | ሁለተኛ ዜና መዋዕል |
| 1ኛ ሳሙ. | የመጀመሪያው የሳሙኤል መጽሐፍ |
| 2ኛ ሳሙ. | ሁለተኛው የሳሙኤል መጽሐፍ |
| መዝ. | መዝሙረ ዳዊት |
| ማቴ. | የማቴዎስ ወንጌል |
| ማር. | የማርቆስ ወንጌል |
| ሉቃ. | የሉቃስ ወንጌል |
| ዮሐ. | የዮሐንስ ወንጌል |
| 1ኛ ተሰ. | የመጀመሪያ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች |

❖ እነዚህ ምህፃረ ቃላት በ1980 ዓ.ም ከታተመው ሰማንያ አሀዱ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

## ሙዳዩ ቃላት

ቤተ መቅደስ = ከቤተክርስቲያን ክፍሎች አንዱ ሲሆን ስልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናትና ዲያቆናት ሥርዓተ አገልግሎት የሚፈፅሙበት ክፍል ነው።

ይትበሃል = "በዚህ ጊዜ ይህ ይባላል፤ እንዲህ ማለት ነው" በማለት የቤተክርስቲያንን ሥነ ሥርዓትን አቅጣጫ የሚያሲዝ ነው።

መሪጌታ = ሥርዓተ ማኅሌቱን የሚመሩ፣ የሚቆጣጠሩ፣የቤተክርስቲያን አገልጋይ።

ድጓ = የዓመቱን መዝሙራት ተወጣጥተው የሚገኙበት ክፍል የያዘ መፅሀፍ

አራራይ = ከቅዱስ ያሬድ ዜማዎች አንዱ ሲሆን፣ ትርጉሙም የሚያራራ፣ የሚያሳዝን ማለት ነው።

ምልጣን = የመቋሚያውን አያያዝ፣ የፀናፅሉ አወዳደቅ እና የቃለ እግዚአብሔሩ አደማመቅ የሚያሳይ ክፍል።

መስተበቁዕ = ልመና ፀሎት

ሊጦን = የማታ ምስጋና

አቡን = ካህናት ታቦተ ህጉን ሲያነግሱ በአውደ ምህረቱ ቆመው የሚያዜሙት ዜማ

ዓውደ ምህረት = የቤተክርስቲያን የውጪ ክፍል ሲሆን፣ የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት እና ስብከተ ወንጌል የሚከናወንበት ቦታ

መወድስ = ምስጋና ወይም ማመስገኛ ማለት ሲሆን ከክሥተት በኋላ የሚሰጥ ትምህርት ነው።

ምርፋቅ = ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ፀበል ፀዲቅ ወይም መክፈልት የሚቀምሱበት ቦታ።

አስርቆት = የዋዜማ ፀሎት

ምዕራፍ = ማረፊያ፣ አንድ የትምህርት ዓይነት

ስብሐተ ነግህ = የጥዋት ምስጋና፣ በጥዋት የሚዘመር መዝሙር

አጽሕሶ = በሥርዓት ማኅሌት ክዋኔ ጊዜ የሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ዝማሜ

አርያም = ልዑል፤ አንድም ከፍተኛ ማለት ነው

ሥብሐተ አርያም = በአርያም የተሰማ ዜማ፣ ድርሰት

ጌተሴማኒ = ከኢየሩሳሌም በቄድሮን ወንዝ ማዶ በደብረ ዘይት ግርጌ ያለ የአትክልት ስፍራ። ስሙ በአርማይክ ቋንቋ የዘይት መጥመቂያ ማለት ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ በኮረም ወረዳ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው።

የጥናቱ ዓብይ ዓላማ የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታን ማሳየት ሲሆን ትኩረቱም ስርዓተ ክዋኔውን ክዋኔ ከፎክሎር የክዋኔ ባህሪያት አንፃር ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። ሥርዓተ ማኅሌት እንዴት ይከወናል? ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ንዋያተ መዝሙራት ያላቸው ተምሳሌታዊ ውክልና ምንድን ነው? ምን ምን ተግባራት አሉት? የሚሉ ዋና ዋና የምርምር ጥያቄዎችን አንስቷል። ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ከጽሁፍና ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ላይ በመመስረት ገላጭ እና የይዘት ትንተና አድርጓል። የጽሁፍ መረጃዎች ከቤተመጻህፍትና ከቤተመዛግብት የተሰበሰቡ ሲሆን የመስክ መረጃች ደግሞ በበዓለ ትንሳኤ እና በሚያዝያ ጊዮርጊስ በተከናወኑት ክብረ በዓላት ላይ በመገኘት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመላክተው የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች አስር ሲሆኑ እነዚህም መቃኘት፣ መቀበል፣ መምራት፣ መመራት፣ ዝማሜ፣ ንዑስ መረግድ፣ ዓቢይ መረግድ፣ ጽፋት፣ ድርብ ጽፋትና የጭብጨባ ጽፋት ናቸው። ደረጃዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን መሰረት ያደረጉ ከመሆናቸው የተነሳ የኢየሱስ ክርስቶስን ነገረ መስቀል ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ይገልጻሉ።

ሥርዓተ ማኅሌት ያለ ከበሮ፣መቋሚያ እና ጸናጽል ሊከወን እንደማይችል በጥናቱ ተብራርቷል። ከዚህም በተጨማሪ ስርዓተ ማኅሌት ቀጥተኛና ሰበበ ማኅሌታዊ የሆኑ ተግባራት እንዳሉት በጥናቱ የተገለፀ ሲሆን እነዚህም ሐይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኪነ ጥበባዊ እንዲሁም የማስተማር፣ የመቆጣጠር የማዝናናት፣ የማጠናከር እና የማሳተፍ ተግባራት እንደሆኑ በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል።

ስለዚህ ከደረጃዎቹ፣ ከንዋያተ መዝሙራቱ እና ከተግባራቱ የሚመነጩ ፎክሎራዊ ገጽታዎች ይታዩበታል። ይህ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ተጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሪዎች ከደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ደምወዝ ቢከፈላቸው፤ በአውደ ምሕረቱ የሚደረጉ ጨረታዎች የግዜ ገደብ ቢደረግላቸው የሚሉ የይሁንታ ሐሳቦችን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል።

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........................................ i

ምህፃረ ቃልና ዝርዝራቸው ........................................ ii

ሙዳዬ ቃላት ........................................ iii

አጠቃሎ ........................................ v

የአርዕስት ማውጫ ........................................ vi

1.መግቢያ ........................................ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2. አነሳሽ ምክንያት ........................................ 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........................................ 5

1.3.1. የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ........................................ 5

1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ........................................ 5

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 6

1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ 6

1.6. የአጠናን ዘዴ ........................................ 7

1.6.1.የጥናቱ ቦታ አመራረጥ ........................................ 7

1.6.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ ........................................ 8

1.7. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................ 8

1.7.1. ምልከታ ........................................ 9

1.7.2. ቃለ መጠይቅ ........................................ 10

1.8.የመስክ ተሞክሮ ........................................ 10

1.8.1.ቅድመ መስክ ........................................ 10

1.8.2. በመስክ ወቅት ........................................ 10

1.8.3. ድህረ መስክ ........................................ 12



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሐሳቦች ..... 12

1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች ..... 12

1.9.2. የመፍትሔ ሐሳቦች ..... 13

2. ክለሳ ድርሳን ..... 15

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 15

2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ..... 22

2.2.1 የክብረ በዓላት ብያኔና ፅንሰ ሐሳብ ..... 22

2.2.2. የዜማ ምንነትና ፅንሰ ሐሳብ ..... 25

2.2.3 የሥርዓተ ማኅሌት ብያኔና ፅንሰ ሐሳብ ..... 26

2.2.4. የሥርዓተ ማኅሌት አጀማመር ..... 27

2.2.5. የሥርዓተ ማኅሌት ዓይነቶች ..... 30

2.2.6. የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋም ..... 31

2.2.7. የፎክሎር ክዋኔ ..... 33

2.2.7.1 የክዋኔ ብያኔና ጽንሰ ሐሳብ ..... 33

2.2.7.2 የክዋኔ ባህርያት ..... 35

2.2.7.2.1 የመከወኛ ምክንያት ..... 35

2.2.7.2.2 ከዋኝ ..... 36

2.2.7.2.3 ታዳሚያን ..... 37

2.2.7.2.4 አውድ ..... 38

2.2.7.2.5 ድርሰት ..... 39

2.2.7.2.6 የክዋኔ መሪዎች ..... 39

2.2.7.2.7 የክዋኔ ማዕቀፍ ..... 40

2.2.8 የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ..... 40

2.2.9 ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት፣ ትዕምርታዊ ውክልና ..... 41

2.2.9.1 የንዋያተ መዝሙራት ምንነት ..... 42

2.2.9.2. የንዋያተ መዝሙራት አሰራር እና አመጣጥ ..... 42


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

2.2.9.3. የቁሳዊ ባህሎች ምንነትና ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) ውክልና ..... 43
2.2.9.3.1. የቁሳዊ ባህሎች ምንነት ..... 43
2.2.9.3.2. የቁሳዊ ባህሎች ተምሳሌታዊ ውክልና ..... 43
3. የኮረም ወረዳ አካባቢያዊ ዳራ ..... 45
3.1 ኮረም እና አካባቢዋ ..... 45
3.2. ስያሜና አመሰራረት ..... 45
3.3. በኮረም ከተማ የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ..... 45
3.3.1.የተቀደሱ የጸበል ቦታዎች ..... 45
3.3.2. የሼክ ቢላል የተቀደሰ ቦታ ..... 46
3.3.3. ታሪካዊ የጦር ሜዳ ቦታዎች ..... 46
3.3.4.የአሮጌ ኮረም መሰረት ..... 46
3.3.5. የሆላ ፏፏቴ ..... 46
3.3.6. ምፍሳስ ባሕሪ (ወዲ ሐያሎ) ..... 47
3.3.7. ትኹል እምኒ ..... 47
3.3.8. የሐውሰዋ ተራራ ..... 47
3.4 ማህበራዊ ሁኔታ ..... 48
3.4.1.ጋብቻ ..... 48
3.4.2. የብሔር ስርጭት ..... 48
3.4.3.ሐይማኖት ..... 48
3.5. መሰረተ ልማት ..... 48
3.5.1. ዘመናዊ ትምህርት ..... 48
3.5.2. ንግድ ..... 49
3.5.3. ኢንቨስትመንት ..... 49
3.5.4. ጤና ..... 49
3.6. የደብረ ገነት ኃያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን አመሰራረት እና እድገት ..... 49
4. የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በኮረም ..... 53
4.1. የበዓለ ትንሳኤ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ..... 53
4.1.1. የትንሣኤ ዋዜማ ክዋኔ ..... 53

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

4.1.2. የሌሊት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ........ 53
4.2. የሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ........ 56
4.2.1. የዋዜማው ክንውን ........ 56
4.2.2. ድህረ ዋዜማ (የሌሊት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ) ........ 57
4.2.3. የዓውደ ምህረት ክዋኔ ........ 58
5. የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ፣ ደረጃዎች፣ የንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና፤ ተግባራት ትንተና ........ 59
5.1.የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ባህሪያት ........ 59
5.1.1. የሥርዓተ ማኅሌት የመከወኛ ጊዜ ........ 59
5.1.2. የሥርዓተ ማኅሌት ከዋኝ ........ 60
5.1.3. የሥርዓተ ማኅሌት ታዳሚያን ........ 62
5.1.4. የሥርዓተ ማኅሌት አውድ ........ 63
5.1.5. የሥርዓተ ማኅሌት ድርሰት ........ 66
5.1.6. የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሪዎች ........ 67
5.1.7 የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ማዕቀፍ ........ 68
5.2. የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች እና ተምሳሌታዊ ውክልናቸው ........ 69
5.2.1 መቃኘት ........ 69
5.2.2 መቀበል ........ 70
5.2.3 መምራት ........ 71
5.2.4 መመራት ........ 72
5.2.5 ዝማሜ ........ 74
5.2.6 ንዑስ መረግድ ........ 77
5.2.7 ዓቢይ መረግድ ........ 78
5.2.8 ጽፋት ........ 79
5.2.9. ድርብ ጽፋት ........ 79
5.2.10. የጭብጨባ ጽፋት ........ 80
5.3. ንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና ........ 85
5.3.1 ከበሮ ........ 85

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

5.3.2 መቋሚያ ........ 88
5.3.3. ጸናጽል ........ 89
5.4. የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራት........ 90
5.4.1. ሐይማኖታዊ ተግባር ........ 91
5.4.2. ማህበራዊ ተግባር ........ 92
5.4.3. ባህላዊ ተግባር ........ 93
5.4.4. የማዝናናት ተግባር ........ 94
5.4.5. ሃገራዊ ፋይዳ (ተግባር)........ 95
5.4.6 ኪነ ጥበባዊ ፋይዳ (ኪናዊ ተግባር) ........ 97
5.4.7 የማስተማር ተግባር ........ 98
5.4.8. የማጠናከር ተግባር ........ 99
5.4.9. የመቆጣጠር ተግባር........ 100
5.4.10.የማሳተፍ ተግባር........ 101
6. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሐሳቦች........ 103
6.1 ማጠቃለያ ........ 103
6.2 ይሁንታ........ 104
ዋቢ ጽሑፎች
አባሪዎች
አባሪ 1፡ የመረጃ ሰጪዎች አጭር ገለፃ
አባሪ 2፡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች
አባሪ 3፡ ፎቶዎች
አባሪ 4፡ ደብዳቤዎች
አባሪ 5፡ የሥርዓተ ማኅሌት መከወኛ ንዋያተ መዝሙራት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የክብረ በዓላት ብያኔና ፅንሰ ሐሳብ፣ የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋም፣ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ፣ የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎችና ተምሳሌታዊ ውክልናቸው፣ ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዘሙራት ዓይነት፣ ተግባርና ተምሳሌታዊ (ትዕምር ታዊ) ውክልና እንዲሁም የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራትን ዳስሷል።

ጥናቱ በኮረም ባሉት የሐያሎ ማርያም እና የቅዱስ ጊዮርጉስ አብያተ ክርስቲያናት የተከናወነውን ሥርዓተ ማኅሌት መርምሯል።

ጥናቱ ስድስት ምዕራፎች በውስጡ ያካተተ ሲሆን፤ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ ፣የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች፣ የመስክ ተሞክሮ፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሐሳቦች ተቃኝተዋል።

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ተዳሰዋል። በምዕራፍ ሦስት የኮረም ወረዳ አከባብያዊ ዳራ ተዳሷል።

በምዕራፍ አራት ደግሞ የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋም እና ክዋኔ ቅደም ተከተላዊ ገለጻ ቀርቧል::

በምዕራፍ አምስት የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ፣ ደረጃዎች፣የንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና እና ተግባራት ተተንትነዋል።

በምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሐሳቦች ቀርበዋል። በመጨረሻም ዋቢ ጽሑፎች እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ተደራጅተው ቀርበዋል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ፎክሎርን በተመለከተ ለሁሉም በመስኩ ለተሰማሩት ባለሙያዎች የሚያግባባ አንድ ወጥ እና ቁርጥ ያለ ብያኔ የለም። ከዚህ በመነጨ ምክንያት የመስኩ ተመራማሪዎች(ፎክሎረኞች) ፎክሎርን እንዲህ ነው ብለው ከመበይን ይልቅ በውስጡ የሚያካትታቸው ጉዳዮችን በመመርመር እና በማጥናት ፎክሎርን ማወቅ እንደሚቻል ይጠቁማሉ። (Alan, dundes 1995፣3፤ Dorson፡1972፣2)::

በ1846 እ.እ.አ ፎክሎር የሚለው ቃል ለመስኩ መጠሪያነት የተጠቀመው ዊሊያም ጆንስ ቶምስ ነው። ቃሉን ከመጠቀም ባሻገርም ፎክሎር በውስጡ ይይዛቸዋል ያላቸውን

"የነገራት አሰራር፣ የሰዎች አኳኋን፣ ልማድ፣ በዓላትና ስነ ስርዓት፣ እምነት፣ አምልኮ፣ ዘፈን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች" ዘርዝሯል (Dorson 1972፣1)።[1]

Leach ባዘጋጀችው መጽሐፍ ፎክሎር በሃያ አንድ የአሜሪካ ፎክሎረኞች የተለያየ ፍቺ ተሰጥቶታል። (1949፣398-403)። ብያኔውን ከሰጡት መካከል "ከ14 የማያንሱ ዘርዛሪ (በመዘርዘር ያተኩሩ) ናቸው" (ፈቃደ 1991፣3)። ሌላው ታዋቂው አሜሪካዊ ፎክሎረኛ Alan Dundes በፎክሎር ይካተታሉ ያላቸውን ስልሳ (60) ያህሉን በመዘርዘር አቅርቧቸዋል (1965፣3)።

Dorson በበኩሉ ፎክሎርን ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performing Folk Arts) ሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Custom) እና ቁሳዊ ባህል (Material Culture) በማለት በአራት የጥናት ዘርፎች (Gener) ይከፍላቸዋል (1972፡23)።

Dorson ሀገረሰባዊ ልማድ ባለው የጥናት ዘርፍ ውስጥ ሀገረሰባዊ መድኃኒት፣ሀገረሰባዊ ፌስቲቫሎችና ጨዋታዎች፣ ክብረ በዓላት ተካተው ይገኛሉ (Dorson፣1972፣2)::

Ben Amos "የፎክሎርን የተለያዩ ገጽታዎች ማለትም ይዘቱንና ቅርፁን፣ የአቀራረብ መልኩን፣ ተግባሩን፣ ባህርያቱን፣ ስርጭቱንና ታሪካዊ አነሳሱን መሰረት አድርገን የምንመለከትበት ወይም የምንተነትንበት መከፋፈያ ዝርያ(Gener) ልንለው እንችላለን(1982፣66) በማለት ገልጾዋል።

ከላይ ከተገለጹት የምሁራኑ ሐሳብ መገንዘብ የሚቻለው ለፎክሎር ብያኔ ከመስጠት ይልቅ በውስጡ በሚጠኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይበልጥ ውጤታማ መሆኑን ነው። ይህ ማለት ግን በጭራሽ ፎክሎርን መበየን አይቻልም ማለት አይደለም።በመሆኑም የተለያዩ ምሁራን ፎክሎር ለሚለው ቃል የተለያየ ብያኔ ሰጥተውታል።
Sims እና Stepthens "ፎክሎር ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ስለዓለም፣ ስለራሳችን፣ ስለማኅበረሰባችን፣ ስለእምነታችን፣ ስለባህላችን፣ ስለወጋችን እና ልማዳችን በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በልማድ፣በድርጊት የምንማረው የጋራ እውቀት ነው" (2005፣8) በማለት ብያኔ ሰጥተዋል።

---

[1] *በዚህ የጥናት ሥራ ውስጥ ዓመተ ምሕረት ሲጠቀስ ጽሑፉን ያቀረቡት የውጭ ዜጎች ከሆኑ ስማቸውን ተከትሎ የሚመጣ ዓመተ ምህረት በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሲሆን የጽሑፉ አቅራቢዎች ኢትዮጵያዊያን ከሆኑ ስማቸውን ተከትሎ የሚመጣው ዓመት ምህረት በኢትዮጵያዊያን የዘመን አቆጣጠር መሆኑን ልብ ይሏል።*

ከ Sims እና Stepthens አገላለጽ መረዳት የሚቻለው በህዝብ አማካይነት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ፣ ከአንድ ዘመን ወደ ሌላ ዘመን የሚተላለፈው ማንኛውም ዓይነት ልማድ፣ እምነት፣ወግ፣ ባህል፣ ትውፊት ፎክሎር መሆኑን ነው። ፎክሎር የሚለው ቃል የጥናት ወይም የሙያ መስክ ሆኖም ያገለግላል (ፈቃደ አዘዘ 1991፣16)።

እዚህ ላይ ክብረ በዓል አንዱ የፎክሎር የጥናት ዘርፍ መሆኑን ማስመር ያስፈልጋል። ክብረ በዓላትን ማጥናት የፎክሎር አንዱን ዘርፍ ማጥናት በመሆኑ ይህ ጥናት በክብረ በዓላት በሚከናወነው ሥርዓተ ማኅሌት ላይ ትኩረት አድርጓል። በክብረ በዓላት ውስጥ መንፈሳዊና ህሊናዊ እንዲሁም ቁሳዊ ባህል ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ጥብቅ ትስስርና ዝምድና ያላቸው በመሆናቸው የመጠናቱ ተገቢነት አጠያያቂ አይደለም።

በፎክሎር ጥናት ክብረ በዓል በአንድ ማኅበረሰብ ወይም በአንድ እምነት ያሉ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች በወራት፣ በዓመታት ሽግግር በሐይማኖታዊ፣በፖለቲካ እና በማኅበራዊ ስርዓቶች ወዘተ. ምክንያት በማድረግ ውዳሴ፣ መዝሙር፣ ዘፈን፣ግብግ፣ ደስታና ጭፈራ፣ የስጦታ ልውውጥ የሚከናወነውበት ቀን ወይም ወቅት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ከተለያየ አካባቢ በዓሉን ለማንገስ የሚመጡበት፣መምህራን ልዩ ልዩ ትምህርቶችን የሚያሰተምሩበት፣ዘመድ አዝማድ የሚጠያየቁበት ወቅት ነው። ሰዎች በዓሉን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ። በመካከላቸው በተፈጠረው ግንኙነትና ዝምድና ያላቸውን ስጋዊ እና መንፈሳዊ አስተሳሰብ፣ ስሜት፣ ወዘተ ማወቅ ይቻላል። ስለዚህ ፎክሎር የማኅበረሰቡን እሴት፣ልማድ፣ወግ፣ደስታ ፣ሐዘን፣ተስፋ፣ ወዘተ. ለመግለጽ የሚያገለግል የጥናት መስክ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህንን አስመልክተው Ben Amos "የፎክሎርን ዝርያ ከተፈጠረበት ዓውድ አንፃር ሲጠና የምርምር ሂደቱን ማስፋት ብቻ ሳይሆን በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአገላለፅ ልዩነቶች ለማሳየትና በውስጡ የተካተቱትን ጉዳዮች መርምሮ (ፈትሾ) ለማየት መሰረት (መነሻ) ሆኖ ያገለግላል" (1982፡31) ይላሉ።

በፎክሎር ጥናት ሰዎች ያላቸውን አንድነትና ልዩነት መገንዘብ ይቻላል። በዚህም የጋራ እና የግል ተግባራቸው፣ አከዋወናቸው፣ አጨፋፈራቸው ወዘተ መረዳት ይቻላል።

የዚህ ጥናት ርዕስ እንደሚያመለክተው በክብረ በዓላት ማኅሌት በመቆም በዓል ይከበራል፡ ፡ በዓል ደግሞ በባህሪው ብዙ ፎክሎራዊ ድርጊቶች ሊያካትት ይችላል። በበዓሉ ምክንያት ብዙ ሰዎች ይሰበሰባሉ፣ የምግብ ዝግጅት ይኖራል። በዓሉ ላይ የሚገኙት ሆነ አዘጋጆች (አስተናጋጆች) ከወትሮ (ከዘወትራዊ) በተለየ መልኩ ጌጣጌጦች እና አልባሳት ይለብሳሉ፡ ፡ ሊቃውንቱ በእጃቸው መቋሚያ ይይዛሉ። ካባ፣ላንቃ ይደርባሉ፤ሻሽ ይጠመጥማሉ።

በዓል ሲባል ደግሞ መደሰትን ያመለክታል። ይህም በዝማሬ፣ በዘፈን፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ ሊገለጽ ይችላል::

እንደ Dorson (1972፣165) ገለፃ "በዓል በርካታ ሰዎች የሚሰበሰቡበት በአደባባይ የሚከበር ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የተወሰኑ ቡድኖች የሚያዘጋጁትና የሚሳተፉበት፣ የመከወኛ ጊዜና ቦታ ያለው፣ ከቡድኑ አባላት አንዱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚሸጋገርበት ነው"። ከዚህ ጋር በማያያዝ "በዓላት ሰዎች እርስ በርስ እንዲገናኙ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፣ አብረው እንዲደሰቱና ግንኙነታቸው ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ ዋነኛ የፎክሎር ዘርፍ (Gener) መከሰቻ መሆኑን ያረጋግጣሉ (Dorson 1972፣167-168)።

በአጠቃላይ ሥርዓተ ማኅሌት ሲከናወን ከላይ የተነሱት የበዓላት ገፅታዎች ይታያሉ። ህዝበ ክርስቲያኑ ነጭ ልብስ ለብሰው፣ሊቃውንቱ ጥንግ ድርብ እና ካባ ደርበው፣ ሻሽ ጠምጥመው፣ ለዝማሬና ለምስጋና የሚያስፈልጉ መንፈሳዊ መጻሕፍት፣ መቋሚያ ወዘተ... ይዘው በቤተክርስቲያን በመሰብሰብ በዝማሬ በእልልታ፣ በጭብጨባ እና በአካላዊ እንቅስቃሴ በዓሉን ያከብራሉ።
ጥናቱ የሚካሄደው በፎክሎር የጥናት ዘርፍ በሆነው በክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ላይ ነው። ይህንን ጥናት በርዕስነት ለመምረጥ ያነሳሱኝ ምክንያቶች አሉ።

## 1.2. አነሳሽ ምክንያት

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐይማኖት ተከታይ በመሆኔ ወደ ቤተክርስቲያን በመመላለስ የቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሐይማኖት፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን እንዲሁም የግዕዝን ቋንቋ እማር ነበር። በዚህ ወቅት ከተመለከትኳቸው ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በይበልጥ ትኩረቴን የሳበው የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋምና ክዋኔ ነበር። ከዚህም በላይ እኔም የስርዓቱ ተሳታፊ ሁኜ በማደጌ ስለ ቤተክርስቲያን ካለኝ ልምዳዊ እውቀት በተጨማሪ በጥናት የተደገፈ ስራ ለመስራት ያለኝ ፍላጎት ርዕሱን እንድመርጥ አድርጎኛል። በዚህም የሥርዓተ ማሕሌት ክዋኔ፣ የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎችና ትዕምርታዊ ውክልናቸው፣ ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚያገለግሉ ንዋያተ መዝሙራት እና ተምሳሌታዊ ውክልናቸው እንዲሁም የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራት ለማሳወቅ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ትኩረት አደረግኩ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ንዋያተ ቅድሳት እና ሥርዓተ ማኅሌት ምስጢር አዘሉና የራሳቸው ታሪካዊ አመጣጥ እንዲሁም ትዕምርታዊ ውክልና ያላቸው ናቸው። ይህ አይነቱ ምስጢር የያዘ ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት ሊጠና

ሲገባው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ግን አንድ ወጥ ስራ አለመሰራቱ ይበልጥ ስላሳሰበኝ ትኩረቴን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ አደረግኩ።

በፎክሎር ትምህርት ክብረ በዓል በሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Custom) ከሚጠኑ የጥናት ዘርፎች አንዱ ነው። በሀገራችን የተለያዩ ሐይማኖታዊና ሕዝባዊ ክብረ በዓላት ለዘመናት እየተከበሩ እንደሚኖሩ ግንዛቤ ነበረኝ። ይህ ግንዛቤ በርዕሱ ላይ ይበልጥ እንዳተኩር ገፋፋኝ፤

በሥርዓተ ማኅሌት ዙርያ የተፃፉ ጽሑፎች አብዛኛዎቹ በግዕዝ ቋንቋ በመሆናቸው ቋንቋውን የማይችሉ ሰዎች የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋምና ክዋኔ እንዲሁም ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ንዋያተ መዝሙራትና ትዕምርታዊ ውክልናቸው በተመለከተ ግንዛቤ እንደሌላቸው በተለያዩ ጊዚያት አስተውየ ነበር። ስለዚህ የዚህ ጥናት ትኩረትም የሥርዓተ ማኅሌትን አቋቋምና ክዋኔ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው::

በዚህ ርዕስ ከአንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ውጭ ሌላ ጥናት ባለመኖሩና የተጠናው የመጀመሪያ ዲግሪም ከፎክሎር አንፃር ስላልተቃኘ ትኩረቴን በይበልጥ በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ እና ተግባራት ፎክሎራዊ ገፅታ አደረግኩ።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1. የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ ማሳየት ሲሆን ከዚህጋር በተያያዘ ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ ባህል፣ልማድ፣ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ግንኙነት ይዳስሳል።

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

ጥናቱ ከላይ ከተገለፀው ዓቢይ ዓላማ በተጨማሪ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

1. የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በቅደም ተከተል ማሳየት፤
2. የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልና መግለፅ፤
3. ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት ዓይነት፣ተግባርና ትዕምርታዊ ውክልና ማብራራት፤
4. የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራትን መተንተን ናቸው።

ጥናቱ ከላይ ከተገለጸው ዓቢይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች በመነሳት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል።

1. ሥርዓተ ማኅሌት እንዴት ይከወናል?

2. የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ምን ምን ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው?
3. ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) ውክልናቸው ምንድን ነው?
4. የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራት ምን ምን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ የሚለው ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት።

1. ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋምና ክዋኔ በቪድዮ እና በፎቶግራፍ ሰንዶ በማስቀመጥ ለቤተክርስቲያኗ መረጃ ሆኖ ያገለግላል።
2. ስለ ሥርዓተ ማኅሌት አቋቋምና ክዋኔ ግንዛቤ ለሌላቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች እና ከእምነቱ ውጭ ላሉ ሰዎች ግንዛቤ ይሰጣል።
3. ለትምህርት ክፍሉ በቁሳዊ እና በመንፈሳዊ ባህል ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች እንደመነሻ ሐሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።
4. ተያያዥነት ላላቸው ትምህርት ክፍሎች የስነ-ስብእ፣ የባህል፣ የታሪክ፣የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች መረጃ ይሰጣል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። ለጥናቱም በኮረም ከሚገኙ አምስት አብያተ ክርስቲያናት ሁለቱ ማለትም የቅድስት ማርያም እና የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተመርጠዋል። በእነዚህ አብያተ ቤተክርስቲያናት ከሚያገለግሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና ምዕመናን ለመረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል። ከዚህም በተጨማሪም ከቤተ ክህነት በሥርዓተ ማኅሌት ዙርያ መጽሐፍ የጻፉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓትና ደንብ መሰረት የተፃፉ መጻህፍት በአላማ ናሙና ለጥናቱ ተመርጠዋል።

ጥናቱ የሥርዓተ ማኅሌት ምንነት፣ አቋቋም፣ ክዋኔ፣ የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች፣ ለክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት ምንነትና ተምሳሌታዊ ውክልና ከሐይማኖታዊ ገፅታቸው በመነሳት ፎክሎራዊ ገፅታቸውን በመለየትና በመተንተን የተወሰነ ነው። ጥናቱ ከሦስቱ የማኅሌት አይነቶች የወርኀ በዓል፣ የእሁድ እና የክብረ በዓል ውስጥ አንዱ

ማለትም  የክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት ብቻ በማጥናት የተገደበ በመሆኑ ሌሎችም የማኅሌት ዓይነቶችን አያጠናም።

ሥርዓተ ማኅሌት  በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ባሉበት አካባቢ የሚከናወን ቢሆንም ጥናቱ ግን በኮረም አካባቢ ባሉት የቅድስት ማርያም እና የቅዱስ ጊዮርጊስ  ቤተ ክርስቲያን የተከናወነውን  የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ብቻ ትኩረት አድርጓል። አጥኚው ካለው የገንዘብና የጊዜ እጥረት የተነሳ የበዓለ ፋሲካ(ትንሣኤ) እና የሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ብቻ በማጥናት ተወስኗል።

## 1.6. የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ ዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ የሚጠቀም ሲሆን ከዚህም ውስጥ ገላጭ (Descripitive) ተግባራዊ አድርጓል።
በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በአሃዝ የሚቀመጡ እና ሒሳባዊ ስሌቶችን ለመጠቀም የሚመቹ ስላልሆኑ በገላጭ (descripitive) ዘዴ በቋንቋ አማካይነት ተተንትነዋል።

### 1.6.1.የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ የሚለው ጥናት የተካሄደው በኮረም በሚገኙ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ነው። ጥናቱ በኮረም  አካባቢ የተደረገበት ምክንያት አጥኚው ከዚህ በፊት የማኅሌት ክዋኔ ምን እንደሚመስል እየተገነዘበ ያደገበት አካባቢ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም  በተጨማሪ  አጥኚው  የአካባቢውን ባህል፣ልማድ፣ ስርዓት፣መረጃ የሚያቀብሉ ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን  እና ምዕመናን  የሚያውቅ፤ የአካባቢውን ተወላጅና ኗሪ በመሆኑና በአብያተ ክርስቲያነቱ በመገኘት የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በቪድዮ እና በፎቶ ካሜራ ለመቅረፅ ሰፊ ዕድል የሚያገኝ በመሆኑ ነው።

የጥናቱ አካባቢ እና ለጥናቱ መረጃ የሚሰጡ ሰዎች ማወቅ ይበልጥ ጥናቱን  ጠንካራ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህን አስመልክተው MAC Donald "Field work collecting oral literature" በተሰኘው  ፅሑፍ " የጥናቱ ሁኔታ  ቀደም ሲል ቦታውን በማወቅና ባለማወቅ ይወሰናል። አጥኚው በአካባቢው የሚያውቀው ሰው ካለ ቢያንስ ጅምሩን የበለጠ ያቀለዋል" (1972፣413-414) ይላሉ። MAC Donald እንዳለት እኔ ለጥናት የመረጥኩት ቦታ አዲስ አለመሆኑንና  የአብያተ ክርስቲያናቱ የአገልግሎት ሁኔታ እንዲሁም የኮረም አካባቢ ታሪክ ያውቃሉ ተብለው የሚነገርላቸው ሰዎችም ቀደም ብዬ ማወቁ ለጥናቱ እገዛ አድርጎልኛል።

ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱየተካሄደበት ወረዳ የትራንስፖርት፣ የመብራት፣የስልክ ወዘተ አገልግሎት የሚገኝበት ከመሆኑም በተጨማሪ ለጥናቱ የተመረጡ አብያተ ክርስቲያናት የ125 ዕድሜ እና ብዙ ታሪክ የያዙ በመሆናቸው አካባቢው ለጥናት ተመራጭ አድርጎታል።

### 1.6.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

በኮረም አብያተ ክርስቲያናት ከሚያገለግሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና ምዕመናን ለጥናቱ አስፈላጊ ሆነው የተገኙት 16 መረጃ ሰጪዎች የተመረጡ ሲሆን እነዚህም 3 ከመምህራን፣ 8 ከመሪጌታዎች፣ 1 ከካህናት' 2 ከወንዶች ምዕመናን፣2 ከሴቶች ምዕመናን ለቃለ መጠይቅ ተመርጠዋል። ከእነዚህም 4ቱ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ናቸው።

መምህራን የተመረጡበት ምክንያት በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የተካኑ እና በቂ እውቀት ያላቸው፣በሙያቸው የተመሰከረላቸው፣ ወንበር ተክለው ደቀ መዘሙርት የሚያፈሩ በመሆናቸው ሲሆን መሪጌቶች ደግሞ እንደ መምህራኑ የመምህርነት ማዕረግ ባይኖራቸውም በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ግን በቂ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው። ስለዚህ የስርዓቱን አጠቃላይ ሁኔታ በሚገባ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ እና የማኅሌቱን ስርዓት ስለሚመሩ ለጥናቱ 8 መሪጌቶች ተመርጠዋል።

ለጥናቱ ምዕመናን ወንዶችና ሴቶች የተመረጡበት ምክንያት ለስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን ካላቸው ቅርበትና በተለይም ለሥርዓተ ማኅሌት ካላቸው ዘወትራዊ ተሳታፊነት በመነጨ ነው። እነዚህም እንደሊቃውንቱ ወንበር ተክለው ስርዓቱን ባይማሩትም በቤተክርስቲያን አገልግሎት ዘወትር በመሳተፋቸው የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት በተመለከተ ግንዛቤያላቸው ናቸው። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘወትር በመሳተፋቸው እና ረጅም እድሜ ያላቸው በመሆናቸው ለጥናቱ ተመርጠዋል።

## 1.7. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች በሁለት ምንጮች ተሰብስበዋል። እነሱም ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮች ናቸው።

አንደኛው ወደ መስክ ወጥቶ መረጃዎችን መሰብሰብ ሲሆን፣ ሁለተኛው በቤተ መጽሐፍትና በቤተ መዛግብት አካባቢ በርዕሱ ዙሪያ ፍተሻዎችን በማካሄድ መረጃዎችን ማግኘት ነው።

ወደ መስክ ወጥቶ የምርምር ስራ ከመከናወኑ በፊት በመጀመሪያ በቤተ መጽሐፍትና በቤተ መዛግብት ውስጥ ተቀምጦ በመስክ ሊካሄዱ የሚገባቸውን ስራዎች አካሂድና ቅደም

ተከተሉን ማጤንና መንደፍ ጠቃሚ ነው። ይህንን አስመለክተው MAC Donald "አብዛኛው ሰው ማለት ይቻላል በባህል ወደበለጸገው አካባቢ በመሄድ የተወሰኑ ጠቃሚ ነገሮችን ለማግኘት ይችላል።ነገር ግን በስርዓት የተቀረጸ የመስክ መረጃ የሚጀምረው በቤተ መጻሕፍትና በቤተ መዛግብት ውስጥ ካለ የማንበቢያ ጠረጴዛ ነው" (1972፡408) ይላሉ።

ወደ መስክ ሲወጣ በፎክሎር ጠቃሚ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች 3ት እንደሆኑና እነዚህም የመስክ ምርምር ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ፊቃደ አዘዘ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

"የመስክ ምርምር በሶስት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል። እነዚህም ሶስት መንገዶች ምልከታ (Observation) ኢንተርቪው (Interview) እና መጠይቅ (Questionnaire) ናቸው። የመስክ ምርምር በብዙ ሙያተኞች ዘንድ አስፈላጊና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (1991፣90)።

እኔም መስክ በወጣሁባቸው ጊዜያት ከሶስቱ መንገዶች ሁለቱን ማለትም ምልከታንና ቃለ መጠይቅን ተጠቅሚያለሁ። በመስክ በነበርኩባቸው ጊዜያት አብዛኛዎቹን መረጃዎች ከተፈጥሮአዊ መቼት ማግኘት ችያለሁ። ወደ መስክ የሄድኩባቸው ጊዜያት ዓመታዊ ክብረ በዓላት ስለነበሩ የእኔም ጥናት የትኩረት አቅጣጫ በክብረ በዓላት የተከናወነውን ሥርዓተ ማኅሌት በመሆኑ ተፈጥሮአዊ መቼት ማግኘት ችያለሁ።እንደ ፊቃደ "ተፈጥሯዊ መቼት ማለት የስነ ቃል ዘርፉ በተለምዶም አንበል በባህል የሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ነው (1991፣22) ይላሉ።

### 1.7.1. ምልከታ

ፎክሎረኞች እንደሌሎች የመስክ ተመራማሪዎች ሁሉ ምልከታ የሚያደርጉ (Observers) እንዲሆኑ ይመክራል (Goldestein 1964'25)። ከ Goldestein አገላለጽ መረዳት የሚቻለው በፎክሎር ጥናት ምልከታ ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መሆኑን ነው። ምክንያቱም ሰዎች በጆሮአቸው ከሚሰሟቸው እና ከመጻሕፍት ከሚያነቧቸው ይልቅ ስርዓተ ክዋኔውን በዓይናቸው እያዩ የሚያስተውሉት ይበልጣል። ከዚህ አንጻር የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ አጥኚው በቦታው በመገኘት ሙሉ ስርዓቱን በመመልከት በቪድዮና በፎቶግራፍ ካሜራዎች በመታገዝ መረጃዎችን መሰብሰብ ችሏል።

### 1.7.2. ቃለ መጠይቅ

ለጥናቱ የሚፈለገው ግብ ያስገኛሉ ተብለው የታሰቡ የቃል ጥያቄዎች በአጥኚው ተዘጋጅተው በጥናት ምርምርና ባለሙያ በሆኑት(አማካሪ) ከተገመገሙና አስፈላጊውን ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ መረጃ ለመሰብሰብ ተግባራዊ ሆነዋል።

ቃለመጠይቆቹ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ናቸው።መደበኛ ቃለ መጠይቆቹ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ ብቻ መልስ ለማግኘት ያተኮሩ ሲሆኑ ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቆች ደግሞ እንደ መረጃ አቀባዮቹ ግንዛቤና እውቀት፣ ልምድና ተሞክሮ ማብራሪያ እየተሰጣቸው፤ በተለያየ መንገድ ገለፃ እየተደረገላቸው የቀረቡ ነበሩ። ከዚህ አንፃር ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ በቂ መረጃ በማስገኘት እጅግ ወሳኝ ነበር።

## 1.8. የመስክ ተሞክሮ

አንድ የመስክ ተመራማሪ ከመስክ በፊት፣መስክ ላይ እና ከመስክ መልስ በኃላ ያከናወናቸው ተግባራት የምርምሩ አካል በመሆናቸው በፎክሎር ጥናት ትኩረት ይሰጣቸዋል (Goldstein፣1964፣37-42፤ ፈ.ቃደ፣1991፣124-139)። በመሆኑም ከመስክ በፊት፣ በመስክ ወቅት እና ከመስክ በኃላ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

### 1.8.1. ቅድመ መስክ

የጥናት ርዕሱ በትምህርት ክፍሉ ከጸደቀልኝ ዕለት ጀምሮ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ዳሰሳ አድርጊያለሁ።ከዚህም በተጨማሪ ለጥናቱ የተመረጡ አብያተ ክርስቲያናት ታሪካዊ አመጣጥ፣የኮረም ወረዳ ማኅበረሰብ እና አካባቢያዊ ዳራ በተመለከተ ግንዛቤ የሚያስጨብጡኝን ጽሑፎች አንብቢያለሁ።

በዚህ ወቅት ለጥናቱ መረጃ የሚሰጡኝን ሰዎች ለማግኘት፤ የማውቃቸውን ሰዎች በስልክ በማነጋገር አድራሻዎችን መፈላለግ ጀመርኩ። በዚህም ሂደት መረጃ የሚሰጡኝን ሰዎች አድራሻ አገኘሁ።ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ደብዳቤ አጻፍኩ፤ለመስክ የሚያሰገልጉኝን መረጃ መሳርያዎች የድምጽ መቅረጫ፣የቪድዮ እና የፎቶ ካሜራዎች አዘጋጀሁ። ከዚያ መደ መስክ ተሰማራሁ።

### 1.8.2. በመስክ ወቅት

ጥናቱ ወደሚጠናበት አካባቢ ኮረም ጉዞ በማድረግ ለአንድ ወር ከሚያዝያ 08/08/2003 - ግንቦት 08/08/2003 ዓ.ም የመስክ ቆያታ አድርጊያለሁ።

ሚያዚያ 08/08/2003ዓ.ም ከጧቱ አስራ ሁለት ሰዓት ከአዲስ አበባ መናኸሪያ ወደ ኮረም ወረዳ ጉዞ ጀመርኩ። ጉዞው የሁለት ቀን በመሆኑ ሚያዚያ 08/08/2003ዓ.ም ከቀኑ 8:30 ደሴ ከተማ ገባሁ።

ሚያዚያ 08/08/2003 ዓ.ም. ደሴ ካደርኩ በኋላ በማግስቱ ጠዋት ወደ ኮረም ተጓዝኩ። ኮረም ልክ ከቀኑ 7:30 ገባሁ። ትንሽ እረፍት ካደረግኩ በኋላ ወደማታው ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን ሰዎች የሚያገናኙኝ ጓደኞችን ስልክ በመደወል ለሚያዚያ 10/08/2003ዓ.ም. ቀጠሮ አስያዝኳቸው።

በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ከጓደኞች ጋር ሰለጥናቱ አጠቃላይ ሁኔታ ከተወያየን በኋላ ወደ ኮረም አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አመራሁ። ለኮረም አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የተጻፈልኝን ደብዳቤ  አቀረብኩ። መምህር ሃይለ ምስጉን(የኮረም ወረዳ ምክትል ከንቲባ እና የትምህትት ቢሮ ሐላፊ) ደብዳቤውን ከተመለከቱ በኃላ ወደ ኮረም ከተማ ልማትና እንዱስትሪ ጽሕፈት ቤት የትብብር ደብዳቤ ጺፉልኝ። የተጻፈልኝን ደብዳቤ በመያዝ ወደ ኮረም ከተማ ልማትና እንዱስትሪ ጽሕፈት ቤት  አመራሁ። ለጽህፈት ቤቱ ሐላፊ ሃላፊ ለአቶ አታኸልቲ ደብዳቤውን አሳየሁ። ደብዳቤውን አይተው ወረዳውን በተመለከተ መረጃዎች ሰጡኝ። የጥዋቱ ስራየን ካከናወንኩ በኋላ ልክ ከቀኑ 8:00 ሰዓት በኮረም ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ሰበካ ጉባኤ ጽህፈት ቤት በመገኘት ከሰበካ ጉባኤው ዋና ጽሐፊ ዲ/ን ገ/ሚካኤል ጋር ውይይት አደረግኩ።  ዲ/ን ገ/ሚካኤልም ተገቢ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ 3 መምህራን ጠቆሙኝ። ከዚያም ስለ ኮረም ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን አመሰራረት፣ ታሪክ የሚያትት ወንጌሉ ዘወርቅ የሚል በአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት የተጻፈ ጽሑፍ እንዳነብ ጠቆሙኝ።

11/08/2003 ዓ.ም ከጥዋቱ 3:00 ሰዓት ወደ ኮረም ወረዳ ቤተ-ክህነት ጽሕፈት ቤት በመሄድ ከመልአከ ሕይወት አበራ አወቀ (የወረዳው ቤተ-ክህነት ገንዘብ ያዥና መዝገብ ቤት) ጋር ውይይት አካሄድኩኝ። እሳቸውም መረጃ የሚሰጡኝን 5 ሊቃውንት ጠቆሙኝ። በበኩላቸውም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆኑ ገለጹልኝ።

ከሚያዚያ11-16 ወቅቱ ሰሙነ ሕማማት በመሆኑ ቃለመጠይቅ ለማድረግ አመቺ አልነበረም። በዚህም ወቅት መረጃ ከሚሰጡኝ ሰዎች ጋር እየተገናኘሁ ቃለ መጠይቅ የማደርግበትን ጊዜና ቦታ አመቻቸሁ። በዚህም በሐይማኖታዊ እውቀታቸው፣በስነ-ምግባራቸው፣ በማኅበራዊ ደረጃቸው እና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው የታወቁ 15 ሰዎች በአላማ ናሙና ለቃለ መጠይቅ መረጥኩኝ።

ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ ሚያዚያ 15 ከቀኑ 11፡00 ሰዓት እስከ ሌሊቱ 9፡00 ሰዓት በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገኘት የስርዓተ ማኅሌት አቋቋም እና ክዋኔ በቪድዮ እና በፎቶ ግራፍ መረጃዎችን አሰባስቤአለሁ። በሳምንቱ ቅዳሜ 22 ከዋዜማው ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ 23 ጥዋት 4፡30 ሰዓት በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በመገኘት የሚያዚያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በቪድዮ እና በፎቶ ግራፍ በማስደገፍ መረጃዎች አጠናቅሬአለሁ።

በመስክ ወቅት መረጃዎችን በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ካጠናከርኩ በኃላ ግንቦት 10/09/2003 ዓ.ም. ከመስክ ጉዞየ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

#### 1.8.3.ድህረ መስክ

ከመስክ ጉዞየ መልስ ከመስኩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መጻሕፍትና ሌሎችንም ጽሑፎች በማንበብ ተጨማሪ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። በመስክ ጉዞየ ወቅት በቴፕ ሪከርደር ተቀርጸው የነበሩት መረጃዎች ወደ ጽሑፍ በመቀየር መረጃዎቹ በዓይነት ዓይነት በማደራጀት ትንታኔ አድርጊያለሁ።

## 1.9. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሐሳቦች

### 1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ ሲካሄድ አጥኚው በርካታ ችግሮች ያጋጠሙት ቢሆንም ችግሮቹን በመቋቋም ጥናቱን ተግባራዊ አድርጓል።

❖ ከገንዘብ (ከበጀት) ጋር የተያያዙ ችግሮች

በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለጥናቱ የተመደበው በጀት በቂ ባለመሆኑ ጥናቱ በሁለት አብያተ ክርስቲያናት የተከናወነውን ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ብቻ ተወሷል። ጥናቱ በሁለት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ከሚወሰን ይልቅ ቁጥራቸው በዛ ባሉ አብያተ ክርስቲያናትና ከከተማም ከገጠርም ናሙና ቢወሰድ የተሻለ መረጃ ማግኘት ይቻል ነበር፡ ፡ ይህ ለማድረግ ደግሞ ለጥናቱ የተበጀተው በጀት በቂ ሆኖ አልተገኘም።

❖ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች

❖ ለጥናቱ የተመረጡት መረጃ ሰጪዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን፡-

ፈቃደኛ ያለመሆን ሁኔታ ከሁለት ዓበይት ምክንያቶች የመነጨ ነው ። የመጀመሪው ከውሎ አበል ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛ ፈቃደኛ ያለ መሆን ምንጭ ደግሞ ጥናቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያተኮረ እና ሐይማኖታዊ ይዘት ያለው

በመሆኑ ቁጥራቸው ከሁለት ባይበልጡም አጥኚው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነው ወይስ የሌላ ከሚል ጥርጣሬ የተነሳ ነው።

❖ በቀጠሮ ጊዜ ያለመገኘት

አጥኚው የተሟላ እና ግልጽ መረጃ ለማግኘት ሲል ስለጥናቱ ዓላማ በማስረዳት የመረጃ ሰጪዎቹ ፍላጎት እና የግል ስራ ባገናዘበ መልኩ የጊዜና የቦታ ቀጠሮ ቢይዝም መረጃ ሰጪዎቹ ግን በቀጠሮ ሰዓት አይገኙም ነበር። ይህ ደግሞ የአጥኚውን ፕሮግራምና እቅድ ከማዛባትም በላይ የተፈለገው መረጃ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እንዳይገኝ አድርጎታል። ይህ ደግሞ ለአጥኚው እጅግ እልህ አስጨራሽና ፈታኝ ነበር።

❖ ለሚጠየቁት ጥያቄ ትኩረት መንፈግ

መረጃ ሰጪዎች ለጥናቱ የተፈለገው መረጃ እንዲሰጡ እና የተዘጋጁትን የቃል ጥያቄዎች መሰረት አድርገው እንዲመልሱ በአጥኚው ቢጠየቁም ወቅቱ በዓለ ትንሳኤ በመሆኑ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ለተጠየቁት ጥያቄ አስፈላጊውን ምላሽ መስጠት አልቻሉም።

### 1.9.2. የመፍትሔ ሐሳቦች

ከውሎ አበል ጋር የተያያዙ ችግሮች አጥኚው በሁለት መንገድ መፍትሄ መስጠት ችሏል፡ ፡ የመጀመሪያው ለመረጃ አቀባዮች ተብሎ የተበጀተ በጀት አለመኖሩን በመግለጽ፤ ጥናቱ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሀገር ጠቃሚ መሆኑ በማስረዳት መረጃ ሰጪዎችን በማስማማት ችግሮች ለመቅረፍ ሞክሯል።

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ አጥኚው ከአቅም አንጻር የውሎ አበል መክፈል የማይችል በመሆኑ መጠነኛ የምሳ፣ የእራት እንዲሁም የሻይ ቡና ወጪ በማድረግ የመረጃ ሰጪዎች ጥያቄ መመለስ ችሏል።

❖ ከሐይማኖት ጋር ተያያዞ ለቀረበ ጥርጣሬ፡- አጥኚው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታይ መሆኑን እና በአካባቢው በቤተክርስቲያን እያገለገለ ማደጉን ለማያውቁ እና ለተጠራጠሩ መረጃ ሰጪዎች የሚያውቋቸውን ሰዎች በማፈላለግ ስለ አጥኚው ግልጽ መረጃ እንዲኖራቸው አድርጓል። በዚህም ጥርጣሪያቸውን በማስወገድ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነዋል። ከዚህም በተጨማሪ አጥኚው በአብያተ ክርስቲያናቱ መገኘት በአገልግሎት መሳተፉ ይበልጥ ጥርጣሪያቸው አስወግዶላቸዋል። በዚህ ሁኔታ ችግሩ ለመፍታት ተሞክሯል።

❖ በቀጠሮ ሰዓት ያለመገኘት ችግር፡- መረጃ ሰጪዎች አጥኚው ጋር በተቀጣጠሩበት ጊዜና ቦታ ባይገኙም አጥኚው በትዕግስት እና ተስፋ ባለመቁረጥ ተደጋጋሚ ቀጠሮዎችን በመያዝ እና ስለጥናቱ ጠቃሚነት እና አስፈላጊነት በማስረዳት መረጃ እንዲሰጡት አድርጓል። ችግሩ የተፈጠረው ወቅቱ ሰሙነ ሕማማት በመሆኑ እና ሊቃውንቱ በአገልግሎት በመጠመዳቸው እንጂ ሆን ተብሎ መረጃ ላለመስጠት አይደለም።እንድያውም ቀጥራቸው አምስት የሚሆኑ መረጃ አቀባዮች ከቀጠሮ ሰዓት ቀድመው በመገኘት እና ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመጠቆም ከፍተኛ ትብብር አድርገውልኛል።

❖ ለተጠየቁት ጥያቄ ትኩረት መንፈግ፡- የጠወሰኑ መረጃ ሰጪዎች የተጠየቁትን የቃል ጥያቄ በመተው ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ያተኩሩ ቢኖሩም አጥኚው ዜዴ በተሞላው መንገድ ወደ ጥናቱ በማምጣት እና ወቅታዊ ጥያቄዎች ከጥናቱ መረጃ በኋላ በማድረግ የመረጃ ሰጪዎችን ፀባይ እና ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ችግሮችን መቅረፍ ችላል፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተደረገ ሲሆን ይህን የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሁለት መንገድ መክፈል ይቻላል።

"የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ" በሚል ርዕስ የተጠና ጥናት ባይኖርም ከክብረ በዓላትና ከሥርዓተ ማኅሌት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች ግን አሉ።እነሱም፡-

ሀ. የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፎች

ለ. መጻሕፍት ናቸው።

ሀ. የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፎች

በዚህ ስር ከእኔ ጥናት ጋር በመጠኑ ቅርበት ያለው የአሸናፊ ጌታሁን (1996) "የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ" የሚል የመጀመሪያ ድግሪ ያልታተመ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው።

- አሸናፊ በጥናቱ የሥርዓተ ማኅሌት አጀማመር፣ የቅዱስ ያሬድ የሕይወት ታሪክ፣ ለክዋኔው የሚያስፈልጉ የዜማ መሳሪያዎች ማለት ከበሮ፣ጸናጽል እና መቋሚያ፣ ሐይማኖታዊ ትርጉም (ምስጢር) እንዲሁም የማኅሌት እና የስነ-ቃልን ግንኙነት አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ ዳስሷል። በዚህም ማኅሌት ጥንታዊ የሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ሀብት መሆኑን እና ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ የዜማ መሳሪያዎች ከበሮ፣መቋሚያ እና ጸናጽል ምስጢር አዘል መሆናቸውን በጥናቱ ጠቁሟል፡

የአሸናፊ ጥናት የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች በማውሳቱ እና የንዋያተ መዝሙራት ምንነት በመጠኑ በመዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

የእኔ ጥናት ከአሸናፊ ጥናት የሚለየው የንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና፣ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ባህርያት፣የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ ውክልና እና የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራትን የሚያጠና (የሚመረምር) በመሆኑ ነው።

አሸናፊ የሥርዓተ ማኅሌትን ታሪካዊ አመጣጥ ከሐይማኖት ገፅታ አንጻር ብቻ የቃኘ ሲሆን በእኔ ጥናት ሐይማኖታዊ መሰረቱን ሳይለቅ የሥርዓተ ማኅሌትን አመጣጥ ከሚቶሎጂ (Mythology) ጋር አያይዤ እመለከተዋለሁ።

- መሶበ ወርቅ ቅጣው (1997) "የገና ክብረ በዓል አከባበር" በሚል ርዕስ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርባለች።

የጥናቷ ዋና ዋና ነጥቦች የሚባሉት የክብረ በዓል ምንነት፣ ተግባር፣ ገጽታዎች፣ የክብረ በዓል በጎ ጎኖች እንዲሁም የሐይማኖታዊ ክብረ በዓልን ምንነት፣ተግባር እና የአከባበር ሁኔታ ናቸው። በዚህ ከእኔ ጥናት ጋር ሲያመሳስላት በሚከተሉት ነጥቦች ደግሞ እንለያያለን።

የመሶበ ወርቅ የትኩረት አቅጣጫ የገና ክብረ በዓል አከባበርን ታሪካዊ፣ ሐይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበረ ባህላዊ ገጽታቸውን የቃኘች ሲሆን የእኔ ደግሞ በክብረ በዓላት የሚከናወነው የስርዓተ ማሕሌት አቋቋምና ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታውን አጥንቻለሁ። በመሆኑም የእኔ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ስርዓተ ማሕሌት በመሆኑ ከፎክሎር የክዋኔ ባህሪያት አንጻር ማለትም፤ የመከወኛ ምክንያት፣ ከዋኝ፣ ዓውድ፣ ታዳሚ፣ የክዋኔ መሪዎች፣ የክዋኔ ማዕቀፍ ይቃኛል። ከዚህም በተጨማሪ የስርዓተ ማሕሌት ደረጃዎች እና የንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና፣ የስርዓተ ማሕሌት ተግባራትን በመዳሰሴ ከመሶበ ወርቅ የተለየ ያደርገኛል።

- ሰለሞን ደርቤ (2000) "የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር" በሚል ርዕስ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቧል።

የጥናቱም ትኩረት በዝቋላ አቦ እና በክብረ በዓሉ ዋዜማ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከናወኑ ክንውኖች፣ በክብረ በዓሉ ዋዜማ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚከናወኑ ክንውኖች፣ በክብረ በዓሉ ዕለት በፀበሉ ዙሪያ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚከናወኑ ክንውኖች፣ በክብረ በዓሉ ዕለት በቤተ-ክርስቲያን ግቢ ውስጥ የተካሄዱ ክንውኖች፣ በክብረ በዓሉ ዕለት አጣብቂኝ፣ የሰይጣን መቃብር፣ የአቡዬ ወንበር እና የዓርብ ረቡዕ ዳገት በተባሉ ሥፍራዎች የተካሄዱ ክንውኖች ሐይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ሲሆኑ የደለጋ ስርዓት ደግሞ ከቤተ-ክርስቲያን ውጭ በጥቅምት 5 እና በመጋቢት 5 የሚከናወን ሃገር በቀል የአምልኮ ስርዓት በክብረ በዓሉ የሚከናወኑ ተግባራት እንደሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል።

ሰለሞን የክብረ በዓላት ምንነት፣ ገጽታዎች፣ አከባበርና ጠቀሜታዎች፤ የሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት ምንነትና ተግባራትን በመዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

የእኔ ጥናት ከሰለሞን ጥናት በሚከተሉት መንገዶች ይለያል።

- ✓ ሰለሞን የዝቋላ አቦ ክብረ በዓልን ሲያጠና አብሮ ከክብረ በዓሉ በተጓዳኝየሚፈፀመውን"ሀገር በቀል"የአምልኮ ስርዓት የቃኘ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን ሙሉ በሙሉ በሐይማኖታዊ ጉዳይ ብቻ ያተኩራል። ታሪካዊ አመጣጡም ከሚቲዮሎጂ አንጻር ይመረምራል። በመሆኑም ሥርዓተ ማኅሌቱ ሲከናወን ያለው ፎክሎራዊ ክዋኔ እና ሥርዓቱን ለማከናወን የሚያገለግሉ ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል ያላቸውን ትዕምርታዊ ውክልና (symbolism) ትኩረት ያደርጋል፡ ፡
- ✓ ሰለሞን የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን ክብረ በዓል ብቻ የተመለከተ ሲሆን በእኔ ጥናት በሁለት አብያተ ክርስቲያናት በቅድስት ማርያም እና በቅዱስ ጊዮርጊስ በተከናወነው ሥርዓተ ማኅሌት ላይ ትኩረት አድርጌያለሁ።
- ✓ ሰለሞን በዝቋላ አቦ የሚከበረውን ክብረ በዓል ትኩረት ያደረገ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በኮረም አካባቢ ባሉት ሁለት አብያተ ቤተክርስቲያናት የተከወነውን የበዓለ ትንሳኤ እና የሚያዚያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ እና ተግባራት ትኩረት አደርጓል።

- ፍሬሕይወት ባዩ( 2000) "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሐይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገጽታ በሚል ርዕስ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርባለች።

ፍሬሕይወት በጥናቷ ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት፡- ህንፃ ቤተ-ክርስቲያን፣ የቋጳሳት ልብሶች፣ በህንጻ ቤተክርስቲያን ዓውድ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች እንደሆኑ ዳስሳለች። ፍሬሕይወት የንዋያተ ቅድሳት ምንነት፣ ለሥርዓተ ማኅሌት የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት (ከበሮ፣ መቋሚያ፣ ጸናጽል) በመቃኘቷ ያመሳስለናል። የእሷ ጥናት ሙሉ በሙሉ በቁሳዊ ባህል ላይ መሰረት ያደረገ ሲሆን የእኔ ደግሞ በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በዚህም የሁለታችን ጥናት የተለያየ ነው።

- Wallelgn Emiru (2003) "The Dynamic of Religious Rituals and Secular ceremonies in public place of Addis Ababa (Spail, Temporal and symbolic aspects) በሚል ርዕስ ለሶሻል አንትሮፖሎጂ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል።

የ Wallelgne ትኩረት በአዲስ አበባ የመስቀልና የጥምቀት በዓላት ላይ ነበር። የመስቀልን እና የጥምቀትን በዓላት ምንነት፣ ክዋኔ፣ የመከወኛ ወቅት እና ማኅበረ ባህላዊ ዓውዶችን መዳሰስ የሚሉ ይዘቶች ላይ ትኩረት አድርጓል።

Wallelgn የመስቀል እና ጥምቀት ተምሳሌታዊ ውክልና (symbolism) የቃኘ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የንዋያተ መዝሙራት (ከበሮ፣መቋሚያ እና ጸናጽል) ተምሳሌታዊ ውክልና ትኩረት አደርጓል። ስለዚህ የምናያቸው ተምሳሌቶች የተለያዩ በመሆናቸው ጥናታችን የተለያየ ያደርገዋል።

ለ. የታተሙ መጻሕፍት

በዚህ ርዕስ ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታና በተጓዳኝ ዝምድና ያላቸው መጽሐፍት ተቃኝዋል።

- ልሳነ ወርቅ ገ/ጊዮርጊስ (1997) ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ

  ልሳነ ወርቅ በዚህ መጽሐፋቸው የቅዱስ ያሬድን ከልደት እስከ መሰወር ያለውን የሕይወት ታሪክ፣ የቅዱስ ያሬድ ስራዎች (ድጓ፣ ምዕራፍ፣ መዋስዕት፣ ዝማሬ) የሥርዓተ ማኅሌት ምንነት፣ አደራረስ፣ የምዕራፍ አደራረስ፣ የመዋስዕት አደራረስ፣ ስለቅዳሴ ማርያም ድርሰት የዜማ አጻጻፍ ዝግጅት፣ ስለ ስርዓተ ጥምቀት፣ ስለስርዓተ ምህላ ታሪክ፣ የቅዱስ ያሬድ ስርዓተ ትምህርት፣ ስለ መሪጌታዎች ታሪክ ዳስሰዋል።

- አምደ ጽዮን ተሰማ(1959) የቅዱስ ያሬድ ታሪክና የዜማው ምልክቶች

  አምደ ጽዮን በዚህ መጽሐፋቸው የቅዱስ ያሬድ የሕይወት ታሪክ፤ የዜማ ዓይነቶች፤ የቅዱስ ያሬድ ታሪክ የሚገኙባቸው መጻሕፍት ዝርዝር፣ 10 የዜማ ምልክቶች እና ትርጓሜያቸው እንዲሁም የሥርዓተ ማኅሌት ምንነት፣ አመጣጥ እና አገልግሎት ዳስሰዋል።

- ርዕሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሳ(1962)ያሬድና ዜማው በሚል ርዕስ መጽሐፍ አሳትመዋል።በዚህ መጽሐፋቸው ቅዱስ ያሬድ የተነሳበትና የነበረበት ዘመን፣ የቅዱስ ያሬድ ምናኔ እና ምንኩስና፣ ቅዱስ ያሬድ የተማራቸው ብሉያትና የትርጓሜ መጻሕፍት፣ ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ የነበሩ የድጓ መምህራን የትምህርት ሐረግ አወራረድ፣ የቅዱስ ያሬድ የድርሰቱ ምንጮች፣ የቅዱስ ያሬድ የዜማው ምድቦች፣ በቅዱስ ያሬድ የነበሩ የፊደል ቅርጽ የሌላቸው ምልክቶች፣ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በትምህርት ላይ በስዕልና በተግባር ሲታይ፣ የተክሌ አቋቋም አመጣጥ፣የማኅሌት አገልግሎትና የስነ-ስርዓቱን አፈፃፀም ቃኝተዋል።

* ሊቀ ስልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ(1963) ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት

ሀብተ ማርያም በዚህ መጽሐፋቸው የፊደል ትምህርት፣ አቡጊዳ፣ የሒሳብ ትምህርት፣ ፊደል ሐዋርያና ገበታ ሐዋርያ፣ የጽሕፈት ትምህርት፣የንባብ ትምህርት፣ ዳዊት መድገም፣ የሐይማኖት ትምህርት፣የቃል ትምህርት፣ የዜማ ቃል ትምህርት፣ መወድስ፣ የድጓ ትምህርት፣ ዝማሬ፣ መዋስዕት፣ አቋቋም፣ የአቋቋም ትምህርት ስልት፣ ክፍለ ማሕሌት፣ ስርዓተ አደራረስ፣ የማኅሌት መሳሪያዎች (መቋሚያ፣ ጸናጽል፣ ከበሮ)፣ የቅዳሴ ትምህርት፣ የግዕዝ ትምህርት፣ የቅኔ ትምህርት፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ፣ ፍትሐነገስት፣ የዘመን አቆጣጠር (ባህረ ሐሳብ)፣ አቡሻክር፣ በዓላትና አጽዋማት ጥንታዊ የኢትዮጵያ ስዕል፣የድጉስ ስራ፣ የመምህራን ሕይወት፣የኢትዮጵያ የካህናት የማዕረግ ስም የሚሉትን ርዕሰ ጉዳዮች ዳስሰዋል።

* ዘወንጌል ገ/ኪዳን እና ሌሎች (1996) ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ

ዘወንጌል እና ሌሎች በዚህ መጻሕፋቸው ስለ ጸምና ጸሎት፣ ስለስግደት፣ ምስጢራተ ቤተ-ክርስቲያን፣ የመዝሙር ምንነት፣ መዝሙርና ጥቅሙ፣ ያሬዳዊ ዜማ፣ የዜማ ምንነት፣ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች የቅዱስ ያሬድ የዜማ አይነቶች፣ የመዝሙር መሳሪያዎችና ምስጢራዊ ትርጉማቸው ፣ ያሬዳዊ መዝሙር አሁን ያለበት ሁኔታ የሚሉትን ጉዳዮች ዳስሰዋል።

* ማህበረ ቅዱሳን (2000) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም

ማህበረ ቅዱሳን ባሳተሙት በዚህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ልማት፣ አስተዳደር፣ የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ፣ ክርስቲያናዊ ሕይወት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዐዋትወ ዜማ ፣የዜማ አጀማመር፣ የቅዱስ ያሬድ ታሪክና አነሳስ፣ የቅዱስ ያሬድ ሐዋርያዊ አገልግሎት፣ የቅዱስ ያሬድ አርዕስተ ዜማ፣ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ይዘት፣ የቅዱስ ያሬድ ድምጸ ዜማ ዓይነቶች፣ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ትምህርት ቤት፣ የቅዱስ ያሬድ ስራዎች፣ የዜማ ምልክቶች አመጣጥ፣ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ጉባኤ ቤቶች፣ የቅዱስ ያሬድ ማኅሌት በአቋቋም፣ የበዓላት ሥርዓተ ማኅሌት አመዳደብ፣ የሥርዓተ ማኅሌት አፈፃፀምና ትርጉማዊ ገፅታው፣ የማኅሌት መሳሪያዎች (ከበሮ፣ መቋሚያ፣ ጸናፅል)፣ የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች የሚሉ ነጥቦች አብራርተዋል።

- (ሊቀ ጉባኤ) መልአከ ስብሐት ኤርምያስ ወልደ ኢየሱስ (2000) ድርሳነ ቅዱስ ያሬድ በግእዝና በአማርኛ

መልአከ ስብሐት ኤርምያስ በዚህ መጽሐፋቸው የዜማ ምንነት፣ የዜማ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የዜማ መሳሪያዎች፣ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች፣የቅዱስ ያሬድ ድርሳንና ተአምር ቃኝተዋል።

- ክፍ ያለው መራሒ (1986) የቤተ-ክርስቲያን አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ

ክፍያለው መራሒ በዚህ መጽሐፋቸው ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ያላት ቦታ፣ ስልጣነ ክህነት (ዲቁና፣ ቅስና፣ ጵጵስና)፤ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት (ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ መጻሕፍት ቤት)፤ ኪነ ጥበባት (ቅድሳት ስዕላት፣ ቅርጻ ቅርጽ፣ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት)፣ የዜማ ምንነት፣ የዜማ አይነቶች፣ የቅዱስ ያሬድ ስራዎች፣ ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት (ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል) ታሪካዊ አመጣጥ እንዲሁም ስነ-ልሳንና ስነ-ጽሕፈት የሚሉትን ጉዳዮች አብራርተዋል።

- *Kefyalew Merahi. The most versatile Ethiopian Scholar St. Yared and His out standing works.*

Kefyalew Merahi በዚህ መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ የቅዳሴ ትምህርት እንዲሁም እነዚህ ጥንታዊ ትምህርት ቤቶች ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ያበረከቱት አስተዋጽኦ፣ የዜማን ምንነት እና ጽንሰ ሐሳብ፣ ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት (ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል) ቃኝተዋል።

- Sergew Habileselassie (1970) The church of Ethiopia: a panorama of history and spiritual life.

Sergew Habileselassie በዚህ መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አሰራር፣ የጸሎት፣ የስግደት ስነ ስርዓት፣ የበዓላት አከባበር፣ የስርዓተ ጋብቻ አፈጻጸም፣ ስርዓተ አምልኮ፣ ሰባቱ አፅዋማት፣ ስርዓተ ቅዳሴ፣ ሰዓታት፣ የጌታ ዓበይት በዓላት፣ የቤተ-ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች (ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ መፃሕፍት ቤት) እንዲሁም የሥርዓተ ማኅሌትን ምንነትና ጽንሰ ሐሳብ የሚሉትን ነጥቦች አብራርተዋል።

- Christian, challot (2002) The Ethiopian orthodox Tewahido Church Tradition

Christian challot በዚህ መጽሐፋቸው የክብረ በዓላት አከባበር፣ የአፅዋማት ስነ-ስርዓት፣ የጸሎት፣ የስግደት ሁኔታ፣ የቤተክርስቲያን አብነት ትምህርት ቤቶች፣ የታቦት ምንነትና አከባበር፣ ስርዓተ ቀብር፣ስርዓተ ጥምቀት፣ መስቀል እንዲሁም የሥርዓተ ማኅሌት ምንነት፣ ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት (ከበሮ፣መቋሚያ፣ ጸናጽል) ዳስሰዋል።

- Budge sir Wallis (1928) A history Ethiopia, Nubia, Abssinia.

Sir Wallis በዚህ መጽሐፋቸው የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስርዓተ አምልኮ፣ ምስጢራተ ቤተ-ክርስቲያን፣ የቤተ ክርስቲያን አሰራር፣ ስርዓተ ፆም፣ የክብረ በዓላት አከባበር፣ የካህናትና የህዝበ ክርስትያን ትስስር፣ የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የስርዓተ ማሕሌት ፅንሰ ሐሳብና ለሥርዓተ ማሕሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት (ከበሮ፣ መቋሚያ፣ ጸናጽል) የሚሉትን ነጥቦች አብራርተዋል።

- Pankrust, Silvia (1955) Ethiopian a Cultural history,

Pankrust, silvia በዚህ መጽሐፋቸው የኢትዬጵያን ባህል ከቤተ-ክርስቲያን ጋር እያወዳደሩ ያቀረቡ ሲሆን የኢትዮጵያን የቀብር ስነስርዓት፣ ልማድ፣ ጋብቻ ኪነ-ጥበብ እንዲሁም የቤተ-ክርስቲያን አብነት ትምህርት ቤቶች፣ የቅዱስ ያሬድ ስራዎች፣ የሥርዓተ ማኅሌት ምንነት፣ ህዝበ ክርስቲያንና ካህናት በቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ያላቸውን ግንኙነት ገልጸዋል::

- Ullendorff Edward. (1966) The Ethiopians: an introduction to country and people.

Ullendorff Edward በዚህ መጽሐፋቸው የኢትዮጵያን ታሪክ ቅድመ ክርስትና ያለው ባዕድ አምልኮ፣ የቤተ-ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ የካህናት ቁጥር፣ የስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ቅዳሴ፣ ሰዓታት፣ ማኅሌት ዳስሰዋል።

- Aymro Wondemagenehu and Joachim (1970) The Ethiopian Orthodox Church.

Aymro እና Joachim በዚህመጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ስርዓተ አምልኮ፣ የግዕዝ ቋንቋ፣ የቤተ-ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና፣ ስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን፣ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ፣ ቤተ-ክርስቲያን የገጠሟት ፈተናዎች እና ያለፈችባቸው መንገዶች፣ የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት እና ለዚሁ የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳትን አብራርተዋል።

የእኔ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩት መጻህፍት የሚለየው የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔና ተግባራት ከፎክሎር አንጻር ስለሚመረምር ነው። በመሆኑም ማኅሌት የራሱ ፎክሎራዊ ክዋኔ አለው። ለክዋኔው የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራትም የራሳቸው ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው። ከዚህም በተጨማሪ ማኅሌት የራሱ መሰረታዊ ተግባራት አሉት። እነዚህም በጥናቱ ተቃኝተዋል።

## 2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

### 2.2.1 የክብረ በዓላት ብያኔና ፅንሰ ሐሳብ

Sims እና Stephens የክብረ በዓላትን ምንነት በተመለከተ "ክብረ በዓላት አንድ ማኅበረ ሰብ ስራዬ ብሎ፣ ጊዜ ሰጥቶ በተደጋጋሚ የሚያከብራቸው ናቸው። አከባበራቸውም በጋራ ነው። ይህ ደግሞ የበዓሉን ተሳታፊዎች አንድነት ያመለክታል (2005፣95) በማለት ብያኔ ሰጥተዋል።

Jerome "ክብረ በዓላት ከአንድ ወራት ወደ ሌላ ወራት፣ ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላ የሕይወት ምዕራፍ መሸጋገሪያ ድልድይ፣ የታሪክ ክንውን፣ የአንድ "ተጋዳሊ" ወይም የአምላክ ልደትና ሞት የሚዘከርበት፣ የሐይማኖት መሪ የሆነ ሰው ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) ድርጊቶችን በማሰብ፣ ሳቅና ጨዋታ እንዲሁም ድግስ የሚደረግበት ወቅት ነው" /1972፣ 159/ በማለት ገልጿል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ክብረ በዓል የአንድ ሐይማኖት መሪ ወይም "ተጋዳሊ" የአምላክ ልደትና ሞትን በማሰብ የሚከበር ሲሆን በዕለቱ አንድ መልእክት የሚገኝበት፣ ሰዎች በፍቅርና በደስታ እየበሉ፣ እየጠጡ ለአምላክ ምስጋና እና ጸሎት የሚያቀርቡበት ቀን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ክብረ በዓላት ሲከበሩ መዝናናት፣ መዘመር እና ከተለመደው ዘወትራዊ ተግባር የተለየ ተግባር በማከናወን የሚከበሩ ቢሆኑም ከዚህ የተለየ ማኅበራዊ ጥቅም እንዳላቸው መገንዘብ ያስፈልጋል።

እንደ Jerome ገላጻ "ክብረ በዓል ሰዎች በስራ ውጥረት፣ በሃሳብ የተጨናነቀ አዕምሯቸውንና አካላቸውን ከስራ የሚያሳርፉበትና በጋራ ሆነው የሚዝናኑበት ነው" /1972፣168/ በማለት ያስረዳል።

ክብረ በዓል አክብሮ የማሳለፍ ሂደት በመሆኑ የራሱ የሆነ ሰበበ ምክንያት እና የሚከበርበት የጊዜ ሰሌዳ አለው። የአከባበሩም ተግባር በእልልታ፣ በጸሎት፣ በምስጋና፣

ማኅሌት በመቆም፣ መዝሙር በመዘመር፣ በማሸብሸብ፣ በማጨብጨብ፣ መሪና ተመሪ፣ አውራጅና ተቀባይ በመሆን ሊከናወን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

ክብረ በዓላት የተለያየ አከባበርና ገፅታ እንዳላቸው (Sims እና Stephens፣ 2005፣55፤ Jerome፣1972፣167-168 ፤Rapport፣1999፣242) በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልጿሉ።

ክብረ በዓላትን በምድብ ምድብ መከፋፈል አስቸጋሪ ቢሆንም ከሚከበሩበት ምክንያትና ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በመነሳት መመደብ እንደሚቻል ያትታሉ። David እና Melivn "በዓላት በጥቅሉ ሐይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ብሔራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ስፖርታዊ" እያሉ መከፋፈል እንደሚቻል ይገልጻሉ (1996፣484)። ብርሃኑ አድማስ "በዓላት" በሚለው መፅሐፍ ውስጥ "ክብረ በዓላቱን ብሔራዊ፣ ዓለም አቀፋዊ፣ ሃይማኖታዊና ሌሎችም ክብረ በዓላት እያሉ መዘርዘር እንደሚቻል" (2002፣169) ገልጸዋል።

ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች አንፃር በኢትዮጵያ የተለያዩ ክብረ በዓላት እንደሚከበሩ እና ክብረ በዓላቱም ብሔራዊ፣ ዓለም አቀፋዊና ሐይማኖታዊ እንደሚባሉ መገንዘብ ይቻላል።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሰረት በኮረም አካባቢ የሚከበረውን "የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ" የሚዳስስ በመሆኑ ከዚህ በታች ስለ ሐይማኖታዊ ክብረ በዓል ምንነት እንመለከታለን።

❖ ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት

David እና Melivn "ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት አምላክ ወይም የሐይማኖቱ መስራች፣ በሐይማኖት ውስጥ ያሉ ቅዱሳን፣ ታላላቅ ድርጊቶች መታሰቢያ በዓላት በመደበኛነት የሚከበሩባቸው ዕለታት ናቸው" (1997፣33) በማለት ገልጸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ Jerome "የሐይማኖት መስራች ወይም በሐይማኖቱ ውስጥ በቅድስና እና በንጽህና የታወቁ ሰዎች የተወለዱባቸው፣ የሞቱባቸው እና ተዓምር የፈጸሙባቸው ቀኖች ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት" ተብለው እንደሚጠሩ ገልጸዋል (1972፣159)።

በመሆኑም ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት የሐይማኖት መስራች እግዚአብሔር የሚከበርበት እና እሱ ያከበራቸው እና የባረካቸው ቅዱሳን የሚዘከሩበት፣ ተዓምራታዊ ስራዎቻቸውን ለታዳሚዎች(ተሳታፊዎች) የሚነገሩበት ቀን መሆኑን ያወሳሉ። በመሆኑም እነዚህን ቀናት ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ታስበው የሚውሉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

በሐይማኖታዊ በዓላት ምክንያት ሰዎች እርስ በእርስ በመገናኘት የተለያዩ ተግባራትን ይፈጽማሉ።ይህንን አስመልክተው Fletcher "ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት ክብረ በዓሉን በሚያከብሩ ሰዎች መካከል ሁለንተናዊ የመረዳዳትና የመተሳሰብ ዕድል ይፈጥራሉ። በዚህም የተነሳ ውስጣዊ ስሜታቸውን በመግለጽ ሐሳብ ለሐሳብ እንዲለዋወጡ መንገድ ይከፍታሉ" (1966፣89) በማለት ገልጸዋል።

Kottak ሐይማኖታዊ ስርዓቶች የራሳቸው መዋቅር፣ ድግግሞሽ፣ መልእክቶች የሚያስተላልፉ፣ የተለያዩ እሴቶችንና አስተሳሰቦችን ወደ ድርጊትና ተግባር መተርጐም የሚያስችል ጥበብ የያዙ ናቸው" (2004፣50) ይላሉ።

በተመሳሳይ መልኩ Robert ደግሞ "ሐይማኖታዊ ስርዓቶች የእምነቱ ተከታዮች ለአምላካቸው ክብርና ኃይል ሲሉ በተግባር የሚገልጹት የአምልኮ ስርዓት ነው" (1999፣381) በማለት ጠቁመዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች የምንገነዘበው ሐይማኖታዊ በዓል ሰዎች ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ክብርና ኃይል ሲሉ በአንድ መንፈስ በመሆን ፍቅራቸውን የሚገልጹበት፣ ከአምላካቸው የተደረገላቸውን መልካም ነገር የሚያስታውሱበት፣ በእልልታ፣ በጭብጨባና በመዝሙር እያጀቡ በዓሉን የሚያከብሩበት ዕለት መሆኑን ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ያሉ በዓላትን የእምነቱ ተከታዮች የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ያከብሯቸዋል። ፍትሐ ነገስት "በዓላት ሲከበሩ በፍጹም ደስታ እና በምስጋና መሆን አለበት፣ ደስታው የስጋ ምኞቶችንና የዓይን አምሮቶችን መሰረት በማድረግ አይደለም። ይልቁንም ፈሪሃ እግዚአብሔር ባልተለየው መንፈሳዊ ሐሴትና ልባዊ ምስጋና በያዘ መልኩ እንጂ" (1995፣259) ሊሆን እንደሚገባ ተገልጿል።

ሐይማኖታዊ በዓላት በመንፈሳዊ ሐሴት የሚከበሩ ናቸው። የደስታው ምንጭና ባለቤት እግዚአብሔር ነው ብለው ስለሚያምኑ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ያከብሩታል። ስለዚህ በጋራ መሰባሰብ አንዱ የሃይማኖታዊ ስርዓት መገለጫ ነው። ፍትሐ ነገስት "በፃድቃን፣ በሰማዕታት፣ በቅዱሳን በዓላት፣ በፃድቁ፣ በሰማዕቱ ወይም በቅዱሱ ስም ወደተሰየመው ቤተ-ክርስቲያን ሂዶ መፀለይ፣ እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ከቅዱሱ በረከት ለማግኘት እግዚአብሔርን መማፀን" (1995፣ 271) አንዱ የበዓላት አካባበር ስርዓት እንደሆነ ተገልጿል። በተመሳሳይ መልኩ ብርሃኑ አድማስ "በፃድቃን፣ በሰማዕታት፣ በሐዋርያት የዕረፍት በዓላትም ቅዱሱ ተጋድሎውን ወደፈፀመበት ወይም አፅሙ ወዳረፈበት በመሄድ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በዚያ በመሰባሰብ" (2002፣ 127) ማክበር ሌላው የበዓላት አከባበር ስርዓት እንደሆነ ገልጿል።

ከላይ ከተገለፁት ሐሳቦች የምንረዳው በሐይማኖታዊ በዓላት ምክንያት የእምነቱ ተከታዮች በቤተክርስቲያን ተሰባስበው በመማር፣ በመፀለይ፣ በመቀደስ፣ በማስቀደስ፣ በመዘመር፣ ስጋ ወደሙን በመቀበል ማክበር የሚቻል መሆኑን ነው።
ብርሃኑ "በዓላት ባህላዊ እና የማንነት መግለጫ ከመሆናቸው በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አላቸው" (2002፣140) ይላሉ።

በአጠቃላይ ሐይማኖታዊ ስርዓቶች ሲከበሩ የራሳቸው የሆነ መንፈሳዊ ትርጉምናፋይዳ አላቸው። የእምነቱ ተከታዮችም አምላካቸውንና ቅዱሳንን በማመስገን በረከት የሚቋደሱባቸው ዕለታት እንደሆኑ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ይታመናል። ማኅሌት በዜማ የሚዜም በመሆኑ ስለ ምንነቱ ከመግለጻችን በፊት የዜማን ምንነት እንመለከታለን።

### 2.2.2. የዜማ ምንነትና ፅንሰ ሐሳብ

የዜማን ምንነት በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ሰጥተዋል።
ሀብተማርያም ወርቅነህ ዜማን እንደሚከተለው ይበይኑታል፡-

> *ዜማ ማለት በጠቅላላ አነጋገር ጩኸት፣ ድምፅ ማሰማት ማለት ነው፤ከዚህ ላይ ግን ዜማ ባልን ጊዜ የምስጋና መዝሙር፣ አዜመ ካለው ቃል ጋር ይመሳሰላልና የሆነ ሆኖ ዜማ ማለት ለምስጋና ብቻ ሳይሆን የለቅሶ፣ የቀረርቶ፣ የሽለላ፣ የፉከራ፣ የሀዘን፣ የደስታ ይኸን የመሳሰለውን ስሜት ሁሉ መግለጫ የሆነው ድምፅ ነው። ለቤተ ክርስቲያን ማገልገያ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቢያ የሆነው ይህ ጩኸት አንድም ድምፅ ዜማ ይባላል (1963፡95)።*

በተመሳሳይ መልኩ ማህበረ ቅዱሳን የዜማን ምንነት እና በውስጡ የሚይዛቸው ክፍሎች እንደሚከተለው አብራርተዋል።

> *ዜማ ማለት ጣዕም፣ ለዛና ስልት ባለው ተከታታይ ቅንቃኔ የሚያሰሙት ድምጽ ማለት ነው፤ ወይም በልዩ ልዩ ስነ ድምጽ ተቀነባብሮ፣ ተደራጅቶና ተስማምቶ ልዩ ስሜትና ተመስጦ ሊሰጥ በሚችል መልኩ የሚያሰሙት ቅንቀና ነው። ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ በአምስት ዓይነት ተከፍሎ ጥቅም ላይ ይውላል። መንፈሳዊ ዜማ (ማኅሌት)፣ የደስታ ዜማ (ዘፈን)፣ የሀዘን ዜማ (ለቅሶ)፣ የልመና ዜማ (ልመና)፣የፉከራ ዜማ (ቀረርቶ) ናቸው። ዜማ ለእነዚህ ሁሉ የጋራ መጠሪያቸው ነው። ሆኖም የዜማዎቹ ድምጸ ቃና፣ ስነቃልና እንቅስቃሴ የአንዱ ከሌላው የተለየ ነው (2000፡9)።*

በማለት ማህበረ ቅዱሳን ዜማ[2] የብዙ ነገሮች መጠርያ መሆኑን ይገልጻሉ። የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ሥርዓተ ማኅሌት በመሆኑ ዜማ እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚያገለግል መንፈሳዊ ይዘት ያለው እና በመንፈሳዊ ቃና የሚቀነቀን ያመለክታል ነው። ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች የምንረዳው ዜማ የራሱ የሆነ ለዛና ስልት ያለው እንዲሁም ድምፅ ባላቸው መሳሪያዎች (መቋሚያ፣ ጸናጽል፣ እምቢልታ፣ አታሞ፣ ዋሽንት) የሚታጀብ ሲሆን አገልግሎቱም ለለቅሶ፣ ለፉከራ፣ ለቀረርቶ፣ ለሀዘን፣ ለልመና እና እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው። በዚህም የሰው ልጅ ስሜቱን፣ ፍላጉቱን፣ ደስታውንና ጭንቀቱን ይገልጥበታል።

### 2.2.3 የሥርዓተ ማኅሌት ብያኔና ፅንሰ ሐሳብ

የማኅሌትን ብያኔ በተመለከተ የተለያዩ ሰዎች ተመሳሳይ እና ተቀራራቢነት ያላቸው ብያኔዎች ሰጥተዋል። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ማኅሌትን እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> *ማኅሌት ማለት ኀለየ ዘፈነ፣ ዘመረ፣ አመሰገነ ካለው ከግዕዝ የወጣ ቃል ነው። አገልግሎቱም ምስጋና፣ መዝሙር ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው። የሆነ ሆኖ ማኅሌት ሲባል የተለየ ስም ያለው ከቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት አንደኛው ክፍል ነው። እሁድ የሚቆም መዝሙር እና መወድስ ሲባል፣ በየወር በዓላት፣ በዓመት በዓላት የሚደረገው የቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ደግሞ ማኅሌት ይባላል (1969፣2010-213) ።*

ከሥርግው ሐብለ ሥላሴ ብያኔ መገንዘብ እንደሚቻለው ማኅሌት[3] ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋና፣ መስዋዕት ነው።

በአማርኛ መዝገበ ቃላት "ማኅሌት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን በከበሮና በጸናጽል እየታጀበ በዜማ የሚባል መንፈሳዊ መዝሙር፣ ምስጋና ጸሎት" (1993፣93) በማለት ገልጾታል።

ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች የምንገነዘበው ማኅሌት[4] መንፈሳዊ መዝሙር፣ ምስጋና እንዲሁም ጸሎት ሲሆን ስርዓቱ የሚከወነውም በከበሮ፣ በጸናጽል እና በመቋሚያ መሆኑን

---

[2] ዘወንጌል ገ/ኪዳን እና ሌሎች "ዜማ በድምፅ ወይም ድምፅ ባላቸው መሳሪያዎች ወይንም በድምፅና በመሳሪያ ተቀነባብሮ ለሕሊና ደስታን የሚፈጥርና የሚሰጥ ስልትና ለዛ ያለው ሬኢኸት ነው። መንፈሳዊ ዜማ አባቶች በቤተ ክርስቲያን ስብሐተ ነግህ (የጧት ምስጋና) ፣ ማኅሌት፣ ስዓታትና ቅዳሴ ለማድረስ የሚጠቀሙበት ነው" (1996፥6-7) ይላሉ።

[3] ደስታ ተክለ ወልድ "ማኅሌት በከበሮ፣ በጸናጽል የሚደረግ መንፈሳዊ ዘፈን፣ ምስጋና የዜማ ጸሎት" (1963፣524) በማለት ይበይኑታል።

[4] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ደግሞ "ማኅሌት ዘፈን፣ ምስጋና፣ ወረብ፣ ለዘብ፣ ቅዳሴ፣ ውዳሴ፣ ቅኔ፣ ግጥም፣ ጉማ፣ ተመማ፣ የብዙ ሰው ዜማ" (1948፣444) በማለት ገልፀዋል።

ነው። ስለዚህ የዜማ መሳሪያዎቹ ሥርዓተ ማኅሌቱን በአግባቡ ለማከናወን ጉልህ ሚና እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ በክብረ በዓላት የሚከናወነውን የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔና ተግባራት መዳሰስ ነው። ፈ.ቃደ "ፌስቲቫልና" "ክብረ በዓል (ከበራ)" በሀገረሰባዊ ልማድ ስር በመመደብ (1991፣13) እንደሚጠኑ ጠቁመዋል።

ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌት በክብረ በዓላት የሚከናወን ምስጋና፣ ጸሎት እንዲሁም ልመና በመሆኑ ፎክሎራዊ ገጽታ አለው።

### 2.2.4 የሥርዓተ ማኅሌት አጀማመር

እንደ ዘርፉ ምሁራን ገለጻ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚለያት አንዱ ሥርዓተ ማኅሌቷ ነው። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅሌት በከበሮ፣ በጸናጽል እና በመቋሚያ ታጅቦ የሚከናወን በመሆኑ ነው፤( ከፍያለው፣1986-6-8፣ ሀብተ ማርያም፣ 1963፡123-125፣ ማህበረ ቅዱሳን፣ 2000-242፣ Sergew ፣1970-68) ይገልፃሉ። Challot "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅሌት ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማ ሰው ሊገርመውና ሊደንቀው ይችላል። ምክንያቱም የሥርዓተ ማኅሌቱ፡ ዜማዊ ቃና እና ስርዓተ አገልግሎቱ (ክዋኔው) ከሌሎች ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ፍጹም የተለየ ነው" (2002፡11) በማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በክዋኔው እና በዜማው ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተለየ መሆኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ልዩ የሚያደርጋት ሥርዓተ ማኅሌቷ ከሆነ ይህን መንፈሳዊ ዜማ ማን ፈጠረው? ከየት መጣ? እንዴት ተጀመረ? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀሬ ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ባይሆንም የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ከፎክሎራዊ ገፅታ ሲያጠና አጥኚው በመጠኑ የሥርዓተ ማኅሌት አጀማመር ታሪካዊ አመጣጥ ቃኝቷል።

ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው ድርሰቶች ድጓ፣ ፆመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ዝማሬ፣ መዋስዕት ናቸው። (ልሳነ ወርቅ ፣1997፣23፤ አምደ ጽዮን፣ 1959፣4፤ ጥዑሙ ልሳን፣1981፣44፤ሀብተ ማርያም፣ 1963፣110 ፤ ማህበረ ቅዱሳን፣2000፣109-110፤ Challot፣ 2002፣111፤ Sergew ፣1970፣68፤ Slvia ፣1955፣241 Aymro Wondemagenehu and Joachim፣1971፣50)።

ያሬድ ከደረሳቸው ድርሰቶች ውስጥ ለስርዓተ ማሕሌት መሰረቱ ድጓ ነው ማለት ይቻላል። ከፍ ያለው "ለመንፈሳዊም ሆነ ለዓለማዊ ሙዚቃ መሰረቱ ድጓ በመባል የታወቀው የቅዱስ ያሬድ የዜማ ልክ መሆኑ አያጠራጥርም" (1986፤68) በማለት ይገልፃሉ።ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌት በዓለመ መላእክት በሰማይ እንደተጀመረ የሚያስረዱ የተለያዩ ሐይማታዊ ጽሑፎች አሉ። ለምሳሌ ማኅሌት በዓለመ መላእክት እንደተጀመረና ከሰማይ በማየትና በመስማት ለዓለም ያስተዋወቀው ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ (ጥዑመ ልሳን፤1981፤ 44፤ ልሳነ ወርቅ፤1997፤40፤ ከፍ ያለው፤1986፤68፤ ሀብተማርያም፤1963፤102፤ ማህበረቅዱሳን ፤2000፤ 98፤ አምደ ፅዮን፤ 1959፤5) ይገልፃሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ማኅሌት መሰረቱ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ አይደለም የሚል አመለካከትና እምነት ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ ማኅሌት ከሰማይ የመጣ ሳይሆን የሰው ልጅ የፈጠራ ስራ ነው የሚል አመለካከት አላቸው። ማኅሌት የሰው ልጅ የፈጠራ ስራ ነው ከሚሉት መካከል አንዱ ሥርግው ገላው የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል።

> *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ዜማ ከምዕራብም ከምስራቅም ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ዜማ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። የራሳቸው የኢትዮጵያውያን ፈጠራ ሁኖ ሳለ ራሳቸው ኢትዮጵያውያንም ይህንና ሌላውንም የራሳቸው የሆነውን የፈጠራ ስራ እኛው እራሳችን ለራሳችን የፈጠርነው ነው ብሎ የመናገር ባህል የላቸውም። ሁሉንም ነገር ከሰማይ ወረደ ወይም ደግሞ ከውጭ ሀገር መጣ ማለት ነው የተለመደው (ያልታተመ መጣጥፍ 2-3)።*

Slvia በበኩላቸው "ሥርዓተ ማኅሌት የደረሰው ያሬድ ቢሆንም ከሰማይ መጣ የሚለው አስተሳሰብ ግን በአፈታሪክ ደረጃ ካልሆነ በቀር ለማመን የሚያስቸግር ነው" (1955፡23) በማለት ከሥርግው ገላው ጋር በሐሳብ ይስማማሉ።

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች ሁለት ነገሮች መረዳት ይቻላል። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ዜማ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዜማ የተለየ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይህ ዜማ እራሳቸው ኢትዮጵያውያን የፈጠሩት እንጂ ከሰማይ የመጣ አለመሆኑን ነው።

በአጠቃላይ የሥርዓተ ማኅሌት ደራሲ ቅዱስ ያሬድ መሆኑ ብዙዎቹ የሚስማሙበት ቢሆኑም ማኅሌት ከሰማይ መጣ፤በዓለመ መላእክት ተጀመረ የሚለው አስተሳሰብ ግን በእምነት የምንቀበለው ካልሆነ በቀር ሁሉንም ሰዎች የሚያስማማ እንዳልሆነ ከላይ ከተገለፁት የምሁራን ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል።

ሥርዓተ ማኅሌት ሐይማኖታዊ ገፅታው እንዳለ ሆነ ከፎክሎር ገጽታው ደግሞ ከሚት አንጻር የሚታይ የስነ ጥበብ ዘርፍ ነው።

የሰው ልጅ የነገሮችን አመጣጥ፣ የህልውናው ምንነት፣ የዓለምን አፈጣጠር የህይወትን ትርጉም የሚገነዘብበት ጥበብ ሚት ይባላል። ይህንን አስመልክተው ቴዎድሮስ "ሚት የሰው፣ የነገረ ፍጥረት እና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን (Cosmological and Ontological Questions) ለመመለስ የሞከረበት፣ እየተመሰቃቀለ ለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርዓት (Cosmic Order) ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው" (2000፣XII) ይላሉ።

ይህ የሚያሳየው የሰው ልጅ ሐይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ የነገሮችን አፈጣጠርና ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች በሚት መልስ የሚያገኝ መሆኑን ነው።
የሰው ልጅ በራሱ የመረዳት ጥበብ ይህ ትክክል፣ ስህተት፣ ጥሩና መጥፎ እያለ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስነ ምግባር ነክ ጉዳዮችን ይመድባል። ከዚህም አልፎ ሐይማኖታዊ ጉዳዮችን በመረዳትና በመገንዘብ ለአንድ ነገር አስገኚ እውቅና ይሰጣል። የእምነት ስርዓትም ያበጃል። በባበጀው የእምነታ ስርዓት ጥበቡን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፋል። ቴዎድሮስ "ሚት የየማህበረሰቡ የእሴት ሥርዓት ነው። እንደ ጥሩና መጥፎ፣ ትክክልና ስሕተት፣ ጽድቅና ሃጥአት፣ ንጽሕናና ወንጀል ያሉ እጅጉን ምግባራዊ፡ እምነታዊ የሆኑ ህሊናዊና አእምሯዊ ጉዳዮች ምን ማለት እንደሆኑ በይኗል" (200፣XII-XIII) በማለት አስረድተዋል።

በአጠቃላይ ሚት የረጅም ጊዜ ታሪካዊ መረጃ የሚሰጥ በመሆኑ የነገረ ህላዌና የነገረ ፍጥረት ጥያቄዎችን መልስ ለመስጠት የሚሞክር ነው። ሥርዓተ ማኅሌትም ስለ አጀማመሩ እና አመጣጡ የራሱ ሚት አለው። ይህም ሚት "ማኅሌት ከሰማይ መጣ፣ በዓለመ መላእክት ተጀመረ" የሚል ነው። ይህም አስተሳሰብ ለእምነቱ ተከታዮች እውነት ነው። ስለዚህ ማኅሌት እንደሚት የታየው ሚቱን በሚያምኑት የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ብቻ የሚታመንና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ነው። ከዚህ አንጻር ማኅሌት በሰማይ መጀመሩንም ሆነ አለመጀመሩን ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን መሰረት በማድረግ ማረጋገጥ አይቻልም።

የዚህ ጥናት ዋናው ትኩረት የሥርዓት ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ መዳሰስ ቢሆንም እግረ መንገዱን በአጀማመሩ እና በታሪካዊ አመጣጡ ዙሪያ ያሉ ክርክሮች ምን እንደሚመስሉ ጠቁሟል። አጥኚው የማኅሌትን አጀማመር፣ አመጣጥ ሰፊ ጊዜ፣ ጉልበት የሚጠይቅ መሆኑንን ስለተገነዘበ ታሪካዊ አመጣጡን ዓላማው ላደረገ አጥኚ በመተው በክዋኔው ፎክሎራዊ ገፅታ ላይ ምን ትኩረት አድርጓል።

### 2.2.5 የሥርዓተ ማኅሌት ዓይነቶች

ማኅሌት በተለያዩ በዓላት የሚቆም ለአምላክ የሚቀርብ ምስጋና እና ጸሎት መሆኑ ከዚህ በፊት ተገልጿል። በዚህ ክፍል የሥርዓተ ማሕሌት ዓይነቶች እና በውስጣቸው የሚይዙት ክፍሎችን እንመለከታለን።

ሥርዓተ ማኅሌት በሦስት ምድብ (አይነት) እንደሚከፈልና በውስጡም የተለያዩ ክፍሎች እንደሚይዝ ማህበረ ቅዱሳን እንደሚከተለው ያብራራሉ።

1. የክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት፡ ይህ ሥርዓተ ማኅሌት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል እነሱም፡

   ሀ. ሥርዓተ ዋዜማ
   ለ.ሥርዓተ መልክዕ
   ሐ. ሥርዓተ አርያም ወይም ሥርዓተ ዓቢይ ስብሐተ ነግህ ናቸው።

2. የእሁድ ሥርዓተ ማኅሌት

   የእሁድ ሥርዓተ ማኅሌት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፤ እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

   ሀ. ክብረ በዓልነት ያላቸው እሁዶች ከሆኑ፣
   - ሥርዓተ ዋዜማ
   - ሥርዓተ መልክዕ
   - ሥርዓተ መወድስ ይቆምባቸዋል።

   ለ. ክብረ በዓልነት የሌላቸው ሆነው ከወርኀ በዓል ጋር ተደርበው ከዋሉ
   - ሥርዓተ መልክዕ
   - ሥርዓተ መወድስ ይቆምባቸዋል።

   ሐ. ተራ እሁድ ከሆኑ ደግሞ ሥርዓተ መወድስ ብቻ ይቆምባቸዋል።

3. የወርኀ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት
   - የወርኅ በአል ሥርዓተ ማኅሌት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

   ሀ. ሥርዓተ መልክዕ
   ለ. ሥርዓተ አርያም ወይም ሥርዓተ ዓቢይ ሰብሐተ ነግህ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ያለ ከበሮ የሚቆሙ የዘወትር ሰብሐተ ነግህ፣ የዓቢይ ፆም፣ ፆመ ድጓና ዐስሩ ምህላት አሉ። እነዚህ ሁሉ ከጥንት ጀምሮ አገልግሎት የሚፈፀምባቸው ሥርዓቶች ናቸው (2000፣ 122)።

ሥርዓተ ማኅሌት በተለያዩ ክፍሎች የተከፈለ እንደሆነ እና እያንዳንዱ ክፍልም እንደ ዓይነቱ አገልግሎቱም የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ከሌሎች የሥርዓተ ማኅሌት ዓይነቶች የሚለየው ከበዓሉ ዕለት ከዋዜማ ቀን ጀምሮ የሚቆም ሲሆን ነግስ፣ ወረብ፣ መልክ፣ ዚቅ፣ አርኬ፣ አንጋርጋሪ፣ እስመለዓለም፣ ቅኔ፣መዋስዕት የሚያካትት በመሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ዑደት አለው::

## 2.2.7 የሥርዓተ ማኅሌት አቋቋም

ሥርዓተ ማኅሌት የራሱ የሆነ የአቋቋም ሥርዓት አለው። ሀብተ ማርያም "አቋቋም ማለት የመቆም ሥነ-ሥርዓት፣ የአቋቋም ልክ፣ መልክ የሚናገር ትምህርት ማለት ነው። ማኅሌት ተቁሞ በሚሰራበት ጊዜ የአገልግሎቱን ሥነ-ሥርዓት የዜማውን ስልት የሚገልጥ እቅድ ማለት ነው" (1963፡99) በማለት ገልጸዋል።

ከሀብተ ማርያም ብያኔ ሁለት ነገሮች መገንዘብ ይቻላል። የመጀመሪያው አቋቋም[5] የትምህርት ዓይነት (department) ሲሆን ይኸውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ከዜማ የትምህርት ክፍሎች ለምሳሌ ድጓ፣ ዝማሬ መዋስዕት፣ ቅዳሴ፣ አቋቋም አንዱ መሆኑን ያመለክተናል። ሁለተኛ ደግሞ አቋቋም የማኅሌትን ክወና የሚገልጥ እቅድ መሆኑን እንገነዘባለን።

ማህበረ ቅዱሳን አቋቋም "ማኅሌት እንዴት መከናወን እንዳለበት የሚገልፅ ስርዓተ ቁመት ነው። ይኸውም የማኅሌቱን የአባባል ቅንብር ለመግለጽ የወጣ ስም ነው" (2000፡112) በማለት ሲገልጹ Challot ደግሞ "አቋቋም በመንፈሳዊ የዜማ መሳሪያዎች በመታጀብ የሚቀርብ ምት (Rythim) ያለው ስልት ነው። ይህም የተጀመረው በመዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት ነው (2ኛ ሳሙ 65-15) በማለት ገልጸዋል። የአማርኛ መዝገበ ቃላት አቋቋም "መዘምራን ከመቋሚያ ውዝዋዜ፣ ከጸናጽል፣ ከከበሮ ድምጽ ጋር እያቀናጁና እያስማሙ

---

[5] ሔኖክ ወልደ ሚካኤል አቋቋም የተባለበት ምክንያትና በውስጡ የሚይዛቸውን ክፍሎች በተመለከተ እንደሚከተለው ያብራራሉ።
አቋቋም የተባለበት ምክንያት ውስተ ዝንቱ፡ መካነ ቅዱስ ንቁም ንሰብሕ ወንዘምር (በዚህ ቅዱስ ስፍራ በመቆም እናመስግን እንዘምርም) ያለውን የሊቁ ባስልዮሰን ድርሰት መነሻ በማድረግ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ መዝ 2፡23 ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሐት (ለእግኢዘብሔር በፍርሐት ተገዙ) የሚለውን የነብዩ ዳዊትን ቃለ ምክር በመከተል የጌታን ወይም የእመቤታችንን ወዘተረፈ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ስለበዓሉ ክብር ልዩ ልዩ ልብስ ይለብሳሉ። ጸናጽል፣ መቋሚያ ይይዛሉ። ፊታቸውንም ወደ ቤተ መቅደሱ ማለት ወደ ምስራቅ አዙረው ሁለት እግሮቻቸውን አስተካክለው ከቅኔ ማኅሌቱ ቀጥ ብለው ይቆማሉ። ስለዚህ የአቋቋማቸው ሁኔታ የሚገልጽ በመሆኑ አቋቋም ተብሏል። ከዝማሜ እስከ ጽፋት ድረስ ያለው ባህለ ድምጸ ዘምሮ አቋቋም በሚል ስም ይጠራል። (1991፡20)



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የሚያዜሙት የማሕሌት ዜማ፣ ትምህርቱም አቋቋም" ይባላል (1993፡204) በማለት በይኗል።

ከላይ ከተገለፁት ሐሳቦች የምንገነዘበው አቋቋም የማሕሌትን ስልት ማቅረቢያ ሲሆን ዜማውም በከበሮ፣ በጸናጽልና በመቋሚያ የሚታጀብ መሆኑ ነው።

በአጠቃላይ አቋቋም የማሕሌትን ስነ ስርዓት፣ ስልት፣ እንዲሁም ክዋኔው ምን እንደሚመስል የሚገልፅ ከመሆኑም በተጨማሪ አንድ የትምህርት ዓይነት መሆኑን ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች መገንዘብ ይቻላል።

በመስክ ቆይታየ እንዳስተዋልኩት ሥርዓተ ማኅሌት የራሱ የአቋቋም ስርዓት ያለው በመሆኑ ስርዓቱን ለማከናወን የደብሩ ሊቃውንት፣መምህራን፣ ቀሳውስት (ካህናት) ዲያቆናት፣ ዘማሪያንና ሌሎች የስርዓቱ ተሳታፊዎች በቅኔ ማኅሌቱ እንደየመዓርጋቸው ይቆማሉ። በሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌነት በሁለት መስመር ፊት ለፊት እየተያዩ የመንበረ ስላሴ አምሳል በሆነችው ቅኔ ማኅሌት ይሰለፋሉ። በቀኝ በኩል "በቀኝ ጌታ" መሪነት ሲሆን በግራ በኩል ደግሞ "በግራ ጌታ" መሪነት ይቆማሉ። ሁሉንም የሚመራ "መርጌታ" ይኖራል። "ቀኝ ጌታ" የሚባለው ማዕረጉ ከርዕሰ ደብር በታችና ከግራ ጌታ በላይ የሆነ በቅኔ ማኅሌት ውስጥ በስተቀኝ በኩል በመቆም ስርዓቱን የሚቆጣጠር ሹም ማለት ነው። "ግራጌታ" የሚባለው ደግሞ በቅኔ ማኅሌት ላይ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደሪ (አለቃ) ከሚቆምበት በስተግራ በኩል የሚቆም እና ማዕረጉ ከ "ቀኝ" ጌታ ዝቅ ያለ የመዘምራን አለቃ ነው።

በሥርዓተ ማኅሌት ቁመት ስነ ስርዓት ውስጥ ስርዓት የሚያስይዝ እና ሁሉን ነገር የሚያስተባብር "አጋፋሪ" የሚባል አለ። "የአጋፋሪ" ዋና ተግባር ወረቡን በአግባቡ እንዲወረብ ማዘዝ፣ ከበሮ መቺዎችን መምረጥ፣ ግራቀኝ የሚያስረግጡትን ሰዎች መወሰንና መሪና ተመሪውን ማቀናጀት ነው። "አጋፋሪ" እነዚህን ተግባራት በኃላፊነት የሚሰራ ይሁን እንጂ አብሮት ቀኝ ጌታ አለ።

ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች የምንገነዘበው ሥርዓተ ማኅሌት የራሱ የአቋቋም ሥርዓት ያለው በመሆኑ ሥርዓቱን ለማከናወን የሥርዓቱ ተሳታፊዎች እንደየማዕረጋቸው እና እንዳላቸው ተሰጥኦ በቅኔ ማኅሌት በመቆም አምላክን የሚያመሰግኑበት ጥበብ መሆኑ ነው።

### 2.2.7 የፎክሎር ክዋኔ

#### 2.2.7.1 የክዋኔ ብያኔና ጽንሰ ሐሳብ

አብዛኛዎቹ የፎክሎር ዘርፎች እንደ አይነታቸውና ባህርያቸው ይለያዩ ይሆናል እንጂ ክዋኔ ግን የጋራ ባህርያቸው ነው። እንደ ባህሉ፣ ዘመኑ እና እንደ ሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ መለያየቱ ፎክሎር ተለዋዋጭ (daynamic) መሆኑን ያሳያል እንጂ ያለ ክዋኔ ፎክሎር ማጥናት አይታሰብም። በፎክሎር አንድ ክብረ በዓል ሲከናወን ፤የመከወኛ ምክንያት፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ዓውድ የሚደርሰበት መንገድ፣ የክዋኔ መሪዎች፣ የክዋኔ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልጉ (Finnegan፣1970፣2፣1977፣28፤ Bauman፣ 1977፣13፤ Vanssina፣ 1985፣ 94፤ Sims እና Stphens፤ 2005፣128) ይገልፃሉ።

Rapport "ክዋኔ ከሌለ ክብረ በዓል የሚባል ነገር የለም" (1999፣250-251) በማለት ለክብረ በዓል ክዋኔ ወሳኝና መሰረታዊ እንደሆነ ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ Deborah "አንድ ነገር መከወን ማለት የበለጠ ነገሩን ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ነው" (1995፣ 479)በማለት የክዋኔ አስፈላጊነት አብራርተዋል። ሥርዓተ ማኅሌት ሲከወንም የመከወኛ ምክንያት፤ ከዋኝ ፤ታዳሚ፤የክዋኔ መሪዎች ክዋኔ የሚቀርብበት መንገድ፤የክዋኔ ማዕቀፍ፤የክዋኔ ጠቅላላ ዓውድ የማይቀሩ ናቸው:: እነዚህም የክዋኔ ባህርያት አንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ ትስስርና ዝምድና በመፍጠር ከዋኞቹና ተሳታፊዎቹ መካከል የጋራ ግንኙነትና ተግባር እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ::

በከዋኞችና በተሳታፊያዎቹ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት Sims እና Stphens "ክዋኔ በተግባር የሚገለፅ ስራ ሲሆን ተሳታፊዎችን ማሳተፍ የግድ ይላል። ይህም እንደየ ልምዳቸውና እንዳላቸው ክህሎት መሳተፍ እንዲችሉ እድል ይፈጥራል። ክዋኔ በአግባቡ እንዲከወን ከተፈለገ ክዋኔው የሚከናወንበት መቼት (ጊዜና ቦታ)፣ ተሳታፊዎች እና ከዋኞች መገኘት አለባቸው" (2005፣129) በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ Bauman "ክዋኔ የሚለው ጽንስ ሀሳብ በውስጡ በርካታ ነገሮች የያዘ ሲሆን ዋናው አላማው ኪነ-ጥበባዊ ፋይዳ (መፍጠር) ማስገኘት ነው።በመሆኑም የፎክሎርን ክዋኔ ኪነ-ጥበባዊነቱ የሚታወቀው በክዋኔውን ሁኔታ፤ በከዋኝ፤ በኪነ ጥበቡ ቅርጽ፤ በተሳታፊዎች፤ በመቼት ነው (1977፣4) በማለት አብራርተዋል።

በመስክ ቆይታየ እንዳስተዋልኩት ወደሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ስንመጣ የዋዜማ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ለማከናወን የተጋብኦ ደወል ይደወልና ሁሉም አገልጋዮች እንደየማዕረጋቸው በቅኔ ማኅሌት ከቆሙ በኋላ ለሁሉም መዘምራን መቋሚያ ይታደላል። በመቀጠል በደብሩ አስተዳደር ወይም በዕድሜ ገፋ ካሉት ካህናት መካከል በአንዱ

ሥርዓተ ጸሎት ወይም አስርቆቱ ይጀምራል። የሚታደለው የህብረት ጸሎት ታድሎ እንዳበቃ ካህኑ "ቅዱስ" ይላሉ። መዘምራን ተቀብለው "ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ሐያል ቅዱስ ሕያው ዘአይመውት" የሚለውን ኪዳን ያደርሳሉ። ከፀሎቱ በኋላ ዋዜማው ይጀምራል።

ከዋዜማው ቅኝት በኋላ መሪው የዜማውን ቀለም ይመራል። ተመሪ ይመራል። በመቀጠል ከግራ ከቀኝ ይነሳል። የቤተክርስቲያን ህግና ደንብ መሰረት በማድረግ የዋዜማው አገልግሎት ከስዓት በኋላ ይከናወናል። በመሆኑም የዋዜማ ማኅሌት አገልግሎት የክብረ በዓሉ መጀመሪያ ነው። ስለዚህ ዋዜማ የማንኛውም ክብረ በዓል መሪ ማሕሌት ነው።

የዋዜማው አገልግሎት ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ከተከናወነ በኋላ ለዕለቱ ወደተዘጋጀው የመስተንግዶስፍራ(ምርፋቅ) በመሄድ ሁሉም የስርዓተምግቡ ተሳታፊ ይሆናሉ። ከእራት በኃላ ለተወሰነ ጊዜ ካህናቱ እረፍት ያደርጋሉ። ከእረፍት በኋላ የተጋብኦ ደወል እንደገና ይደወልና ካህናቱ በቅኔ ማሕሌት ይሰበሰባሉ። በማስከተልም መቋሚያ ይታደላል። የህብረቱ ጸሎት በአንድ በእድሜ ገፋ ያሉ ካህን ይጀመርና ለሁሉም ውዳሴ ማርያም ይታደላል። ጸሎቱ እንዳለቀ በመሪው ወገን "ሚካኤል ሊቀመላእክት ሰአል በእንቲአነ" (የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሆይ ስለኛ ጸልይ) የሚለው መቅድመ ማሕሌት በግራ ና በቀኝ በመቀባበል ይደርሳል።

ከዚህ በመቀጠል "ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ" (ጌታሆይ እባክህ ጸሎቴን ስማኝ) የሚለው ከመዝሙረ ዳዊት (መዝ101፣1) የተወሰደው ቀለም በመሪጌታው ይመራል። ከዚያም በግራና በቀኝ በቁም ዜማ በህብረት በመቀባበል ይዘመርና ከሲኖዶስ መፅሐፍ "ሰቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኵሎ ዓለመ በአሐቲ ቃል (በአንዲት ቃል ዓለምን ሁሉ የፈጠረ ፈጽሞ የተመሰገነ ነው) የሚለው ዜማ በቁም ዜማ ከተዜመ በኋላ ጸናጽል ይጸነጸላል። በዚህ ሁኔታ ሥርዓተ ማኅሌቱ በቁምና በመረገድ ደረጃ በደረጃ ይከናወናል።

በማስከተል በዓሉን የሚመለከት የዕለቱ ቀለም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የሚጸነጸለው ይጸነጻላል። የሚመረገደው ይመረገዳል። በዚህ ሁኔታ የሥርዓተ ማኅሌት ሂደት የሚከናወን ሲሆን አልፎ አልፎ በድምፃውያን መዘምራን ጣዕመ ዜማ(ለዙብ) እየተዜመ አጽሕሶውና ሽብሸባው በየተራ ይከናወናል። በዚህ ጊዜ ህዝበ ክርስቲያን (ምዕመናን) በእልልታና በጭብጨባ ካህናቱን ያጅባሉ። ካህናቱም በፈጣን የሰውነት እንቅስቃሴ ወደፊትና ወደኋላ እየተመላለሱ የምስጋና ስነ ስርዓቱን ያከናውናሉ። በክብረ በዓላት የሚከወነው ማኅሌት ሙሉውን ሌሊት የሚባል ሲሆን ሥርዓቱ በነገ ጠዋቱም የሚቀጥል ነው። ማኅሌት ስቡሕ ወውዱስ በማለት ይጀመርና በንዑስና በአብይ መረገድ እየተመላለሰ

ከተጸነጸለ በኋላ ወደ ሁለተኛው ክፍል ነግሥ (ሥርዓተ አርያም) ወይም ሥርዓተ ዓብይ ስብሐተ ነግህ ይካሄዳል። ነግሥ ግጥም ሲሆን እንደ መልክዕ ሆኖ የቅዱሳንን፣ የመላእክትን፣ የፃድቃንን የሰማእታትን በይበልጥ ደግሞ የስላሴን ምስጋና የሚናገር ነው።

ሦስተኛው የማኅሌት ክፍል መልክዕ ሲሆን ይኸው ዕለቱ ወይም በዓሉ የሚመለከተው ቅዱስ መልክዑን እየተቀባበሉ በማድረስ (በማዜም) ማኅሌቱ ይመረገዳል።ሌላው ተጨማሪ የማኅሌት ክፍል ዚቅ የሚባል ሲሆን ትርጉሙም "ከያሬድ ድርሰት ዝቅ ያለ ማለት ነው" ሥርግው ሐብለ ሥላሴ(1964፡2)።

በዚህ ሁኔታ የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ጥዋቱ ስርዓቱን ጠብቆ ይከናወናል።

በፎክሎር ክብረ በዓላት የራሳቸው ክዋኔ ያላቸው በመሆናቸው ክዋኔው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከሚፈጸም ድረስ ያለውን አጠቃላይ ድባብ ያመለክታሉ። ሥርዓተ ማኅሌትም ሲከወን የራሱ አጀማመር፣ ሂደት እና አፈጻጸም አለው ። በፎክሎር ክዋኔ መሰረታዊ እንደሆነ ሁሉ በሥርዓተ ማኅሌትም ክዋኔ መሰረታዊ ነው። በአጠቃላይ ማኅሌት ከፎክሎር አንፃር የሚጠናው እንዴት? በምን? በማን? እና መቼ? እንደሚከወን ታሳቢ በማድረግ ነው።

### 2.2.7.2 የክዋኔ ባህርያት

#### 2.2.7.2.1 የመከወኛ ምክንያት

አንድ የፎክሎር ዘርፍ የራሱ የሆነ የሚዘመርበት፣ የሚነገርበት፣ የሚከወንበት የተወሰነ ምክንያት አለው።በመሆኑም በዘፈቀደ የሚከወን የፎክሎር ዘርፍ የለም። አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን የራሱ የሆነ የመከወኛ ምክንያት እንዳለው vansina "ክዋኔ የሚከወንበት ጊዜና ወቅት ያለው በመሆኑ በዘፈቀደ የሚከወን አይደለም። በመሆኑም ጊዜና ወቅቱን ጠብቆ ሲከወን የምናየውና የምናስተውለው ነው" (1985፣39) በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ Sims እና Stphens "ክዋኔ ግልፅ የሆነ መቼት ያለው ሲሆን የራሱን የአከዋወን ቅርፅም ይይዛል። ቅርፁም የተሳታፊዎቹን የክዋኔ ሁኔታና ክዋኔው የሚከወንበትን ቦታ ያመላክታል" (2005፣128) በማለት ገልጸዋል። ሥርዓተ ማኅሌት የራሱ የሆነ የመከወኛ ወቅት[6] እንዳለው (ከፍ ያለው ፣1986፣68፤ሀብተ ማርያም፣

[6] ከመስከ ያገኘሁት መርጃ የሚያመለክተው ስርዓተ ማሕሌትም የሚከወንበት የራሱ ጊዜና ወቅት አለው። የማሕሌት የመከወኛ ምክንያት እሁድ፣ የወርን በዓል እና ክብረ በዓላት ናቸው። ከክብረ በዓላት መካከል በዓለ ትንሳኤና ሚያዚያ ጊዩርጊስ ተጠቃሽ ናቸው።(ሚያዚያ 2003)

1963፣102፤ ማህበረ-ቅዱሳን፤2001፣121፤ ልሳነ ወርቅ፣1999፣23-24)፤ Challot፣ 2002፣112) ይገልጻሉ።

### 2.2.7.2.2 ከዋኝ

ከዋኝ ያወቀውን፣ የተማረውን እና ያለው ሙያ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚያስተላልፍ መልእክት አድራሽ ነው። በመሆኑም የስርዓቱን ቀጣይነት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ እንዲተላለፍ በማስተማርና በመተግበር ድርሻውን የሚወጣ ነው። በፎክሎር በቃል የተፃፉ ነገሮች ህይወት የሚኖራቸው ሲከወኑ ስለሆነ ለዚህ ክዋኔ መሳካት ደግሞ የከዋኙ ድርሻ የጐላ ነው። Finnegan "ቃላዊ ነገሮች የሚተላለፉት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው፣ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የተደረሰውን (የተፃፈውን) መሰረት በማድረግ ቢሆኑም በዕለቱ ግን የሚተላለፈው በቃል ነው። በመሆኑም ቃላዊ ነገሮች በከዋኙ የሚወሰኑ ናቸው፤(1970፣2) በማለት ገልፃለች።

ከ Finnegan አገላለፅ የምንገነዘበው ዕሁፋዊ ነገሮች በቃል በሚደርሱበት /በሚከወኑበት/ ጊዜ ለክዋኔው መሳካት ጉልህ አስተዋፅኦ ያለው ከዋኙ መሆኑ ነው። ስለዚህ ያለ ከዋኙ ክዋኔ አይታሰብም ማለት ይቻላል።

ሥርዓተ ማኀሌትም ከአንድ ዘመን ወደ ሌላ ዘመን፣ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ እንዲተላለፍ የሚያደርጉ ማኀሌታውያን ናቸው። ኪዳነ ወልድ "ማኀሌታዊ (ማኀሌታይ)፤ የማኀሌት ሰው፣ ደብተራ፣ አወዳሽ፣ መርቶ የሚቃኝ፣ ራሱን የቻለ፣ድምጣም፣ ድምጠ መልካም፣ ማኀሌት የሚያሞቅ፣ የሚያደምቅ፣ መዝፈን፣ መቀንቀን መወረብ፣ ማስረገጥ፣ ከበሮ መዝበጥ የሚያውቅ" (1948፣445) በማለት የማኀሌታዊ(ማኀሌታይ)ን ምንነትና ድርሻውን ገልፀዋል። በተመሳሳይ መልኩ Challot (2002፣11) "የሥርዓተ ማኀሌትን ምንነት አውቀው የሚከውኑ እና ሥርዓቱን የሚተገብሩ መርጌታዎች" የሚባሉ ሲሆን ከመርጌታዎች በመቀጠል የሥርዓተ ማሥሌት አቋቋም ደንብ እና ስርዓት የሚያውቁ ደግሞ ደብተራዎች" ይባላሉ (2002፣11) በማለት ድርሻቸው ምን እንደሆነ አብራርተዋል።

በፎክሎር ጥናት እያንዳንዱ ከዋኝ እንዳለው ማኅበራዊ ማዕረግ፣ የትምህርት ደረጃ፣ እንደ ወሰደው የስልጣና አይነት ሊለያይ እንደሚችል (Finnegan፣1977፣213) ፤Vansina፣ 1985፣34-37) ይገልጻሉ።

ማሊታውያን፣ባላቸው ሐይማኖታዊ እውቀት በህዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ የተከበሩ እና ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው። እነዚህም በቂ ሐይማኖታዊ እውቀት ያላቸውና ስራዬ ብለው ስልጠና የወሰዱ ናቸው። ባላቸው ሙያም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት

ተቀጥረው የሚሰሩ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮ እና በሌላ ስራ ተሰማርተው እየሰሩ ከሙያቸው በተጓዳኝ እንዳላቸው ተስጥኦና ጸጋ ቤተ-ክርስቲያን እና ህዝበ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ናቸው። አንዳንዶቹ ጥሩ ጣዕመ ዜማ (ድምጸ ቃና)፣ የጸናጽል አያያዝ፣ የሻሽ አጠማጠም ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ የማስረገጥ፣ የማሽብሸብ እና የመምራት ወይም የመመራት ጸጋ ሊኖራቸው ይችላል። ሁሉም ማኅሌታውያን እንደ ጸጋቸው ለሥርዓተ ማኅሌት መከናወን ጉልህ ሚና እንዳላቸው (ሀብተ ማርያም፣1963፣106፤ ከፍያለው፣1986፣72፤ልሳነ ወርቅ፣1997፣24፤ Challot፣2002፣111-112) ይገልጻሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች የምንገነዘበው ለአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ መሳካት ከዋኙ ወሳኝ ሚና የሚጫወት መሆኑን ነው። በመሆኑም ያለ ከዋኝ ክብረ በዓል ማከናወን እንደማይቻል መረዳት ይቻላል።

### 2.2.7.2.3 ታዳሚያን

ታዳሚያን[7] /ተሳታፊዎች/ የሚባሉት አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን ልብ ብለው የሚመለከቱ፣ የሚያስተውሉ ሲሆኑ አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ ከዋኙን የሚያግዙ እና በክዋኔው ትልቅ ሚና ያላቸው እንደሆኑ (Finnegan፣1977፣176-177፤ Vansinna፣ 1985 35-36፤ Sims እና Stphens፣2005፣128-129፤Rapport፣1999፣255፤ Bauman፣1977፣4-5፤BenAmos፣1971፣4) ይጠቁማሉ።

በፎክሎር ክዋኔ ውጤታማ የሚሆነው ተሳታፊዎቹ ክዋኔውን በአግባቡ መከወን ሲችሉ እንደሆነ (Finnegan፣1977፣172-175፤ Vanssina ፣1985፣34-35፤ Sims እና Stphens 2005፣128-130) ይገልፃሉ።

ከላይ ከተገለጸው መሰረተ ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ሥርዓተ ክዋኔ የታዳሚዎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ነው። በዚህም የተነሳ አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን ለታዳሚዎች ትልቅ ቦታ ይሰጣል። ታዳሚያን በተፈጠረላቸው ዕድል ስሜታቸው፣ ፍላጎታቸው፣ ደስታቸው እና ሐዘናቸው ይገልጿል። በዚህም የክዋኔን ውጤታማነት መገምገም ይቻላል።

---

[7] በመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልኩት በሥርዓተ ማኅሌት ታዳሚያን (ተሳታፊዎች) የሚባሉት ህዝበ ክርስቲያን ሲሆኑ እነዚህም የማኅሌታውያንን እንቅስቃሴ በማየት በእልልታና በጭብጨባ ስርዓተ ማኅሌቱን የሚያደምቁ ናቸው። የማኅሌት ክዋኔ በህዝበ ክርስቲያን ተሳትፎ የታጀበ ነው። ስለዚህ በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የህዝበ ክርስቲያን ተሳትፎ ያስፈልጋል። በህዝበ ክርስቲያንና በማኅሌታውያን መካከል የሚፈጠረው ጥብቅ ትስስር ሥርዓተ ማኅሌቱን በአግባቡ ለመከወን ያስችላል።(ሚያዚያ 2003)

### 2.2.7.2.4 አውድ

አውድ አንድ የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት ያለውን አጠቃላይ የክዋኔውን ድባብ (ገፅታ) የሚያመላክት ነው። ክዋኔው የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ (መቼት)፣ የክዋኔው ሁኔታ፣ የመከወኛ ቁሳቁሶችን፣ የክዋኔውን ድርጊቶች፣ የታዳሚንና የከዋኙን መስተጋብር ይይዛል (Martha እና Marthin፣2005፣128-131፤ Goldstein፣1964፣44፤ Ben Amos፣1971፣5፤ Bauman፣1977፤ Bascom፣1986፣36) በማለት አብራርተዋል። ዓውድ ተጨባጭ አውድ (physical context) እና ማህበራዊ ዓውድ (social context) ተብሎ ይከፈላል (Sims እና Stphens ፣2005፣137-139፤ Bauman፣1977፣36)።

#### I. ተጨባጭ ዓውድ[8]

ይህ የአውድ ዓይነት ክዋኔው የሚከወንበት ጊዜና ቦታ፣ መልከዓ ምድራዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታ፣ የክዋኔው ሁነት፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ የአከዋወኑ እንቅስቃሴ፣ ዜማ፣ የድምፅ አወራረድ እና የክዋኔው ድግግሞሽ እንደሚያጠቃልል (Sims እና Stphens ፣2005፣ 138፤ Ben Amos፣ 1971፣5) ይጠቁማሉ።

#### II. ማኅበራዊ ዓውድ[9]

ይህ የክዋኔ ዓውድ በክዋኔ ወቅት የሚታየውን አጠቃላይ ድባብ የሚያመለክት ሲሆን በውስጡም የከዋኞቹና የተሳታፊዎቹ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ሐይማኖታዊ እውቀት፣ የስራ ድርሻቸው እና በዘር፣ በቋንቋ፣ በጐሳ፣ በፆታ ወዘተ መለያየታቸው የሚፈጥረው አጠቃላይ ድባብ ማኅበራዊ ዓውድ እንደሚባል (Sims እና Stphens ፣2005፣139-140፤Ben Amos፣1971፣8-9፤Finnegan፣1977፣214፤Bauman፣1977፣38፤ Vansina፣1985፣34) ይገልጻሉ።

---

[8] በመስክ ቆይታየ እንዳስተዋልኩት ሥርዓተ ማኅሌት የሚከወነው ቅኔ ማኅሌት በተባለው የቤተክርስቲያን ክፍል ውስጥ ሲሆን በዚህም የካህናቱን ዝማሬ፣የመቋሚያ አያያዝ፣ የጸናጽል አጸናጸል፣ የከበሮ አመታት፣ የህዝበ ክርስቲያኑን እልልታና ጭብጨባ የምናስተውልበት ነው።ከዚህም በተጨማሪ በታላላቅ አድባራት ያሉ ካህናት በክብረ በዓላት የሚለብሷቸው ካባ፣ ጥንግ ድርብ፣ ሻሽ የክዋኔውን ተጨባጭ አውድ የሚያመለክቱ ናቸው።(ሚያዚያ 2003)

[9]በመስክ ቆይታየ እንዳስተዋልኩት በሥርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ካህናት በቅኔ ማሕሌት የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ዝማሜ፣ የወረብ አወራረብ የህዝበ ክርስቲያንን እልልታና ጭብጨባ፣ የማሕሌታውያንን ንቁ ተሳትፎ እና አጠቃላይ የዝማሬውን ድባብ ይታያል።ይህ ደግሞ የሥርዓተ ማኅሌትን አጠቃላይ ማኅበራዊ አውድ የሚያመለክት ነው።(ሚያዚያ 2003)

በአንድ ሥርዓተ ክዋኔ የሚሳተፉ ሰዎችን በዕድሜ፣ በፆታ፣ በሐይማኖታዊ እውቀት፣ በማኅበራዊ ደረጃ እና በሙያ መለያየታቸው መገንዘብና መረዳት የማኅበራዊ ዓውዱን አጠቃላይ ድባብ በቀላሉ ለማወቅ ያስችላል።

### 2.2.7.2.5 ድርሰት[10]

እንደ ኪዳነ ወልድ አገላለፅ "ድርሰት መድረስ፣ አደራረስ፣ ደረሰ፣ በቁሙ፣ የምስጋና ቃል፣ መልክ፣ ሰላምታ፣ ግጥም"(1948፣44) በማለት ይበይኑታል። ከዚህ አገላለፅ የምንገነዘበው ድርሰት በዜማ ለሚከወኑ ግጥሞች መሰረታዊ መሆኑ ነው። በይበልጥ ደግሞ በክዋኔ ወቅት ግጥሞች የሚገጠሙበትን መንገድ የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ከዋኙ ስርዓተ ክዋኔውን በሚከወንበት ጊዜ ነባሩን ዜማ አወራረድ፣ ስልት እና አስነኛኘት ተከትሎ የራሱን ቃላትና ሐረጋት፣ ዓረፍተ ነገሮች እና አዳዲስ ስንኞች ሊፈጥር እንደሚችል ትጠቁማለች (Finnegan 1977፣52-86)።

### 2.2.7.2.6 የክዋኔ መሪዎች[11]

አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወንክዋኔው የሚከወንበት ሁኔታ፣ የአከዋወኑ አጀማመር፣ ሂደትና አጨራረስ፣ ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ ክዋኔው የሚከወንበት ጊዜና ቦታ (መቼት) የሚያመለክቱ መሪዎች (markers) አሉት (Sims እና Stphens 2005፣ 141-143፤ Rapport 1999፣255-256)።

የክዋኔ መሪዎች ሚና አንድ የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት ለታዳሚዎች እና ለፎክሎር ባለ ሙያው ማመላከትና መጠቆም ብቻ አይደለም። ከዋኞቹ እና ታዳሚዎቹ እርስ በርስ የሐሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ፣ መጠነኛ ዕረፍት እንዲወስዱ፣ ስለ ክዋኔው አጠቃላይ ሁኔታና ድባብ አስተያየት እንዲለዋወጡ እና የፎክሎር ባለሙያው ከክዋኔው አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት ተገቢ ማብራሪያናትንታኔ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ናቸው (Sims እና Stphens፣2005፣141-142) በማለት ገልጸዋል።

መሪዎች (Markers) የከዋኞችን እና የታዳሚዎችን ድምፀ ቃና፣የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የፊት መለዋወጥ እና የመከወኛ ቁሳቁሶችን ድምፅ ግምት ውስጥ በማስገባት መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡

---

[10] በመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልኩት የክብረ በዓላት ሥርዓት ማኅሌት በሚከናወንበት ጊዜ ማኅሌታዊው በድጓ ውስጥ የተጻፈውን ነባሩን ዜማ መሰረት በማድረግ እግዚአብሔርን ለማገልገልና አማልክትን ለማስደሰት በየአመቱ አዳዲስ ወረቦች እና አዳዲስ ቅኔዎች ይቀኛል።(ሚ.ያዚ.ያ 2003)

[11] በመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልኩት የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በበላይነት የሚቆጣጠር እና የሚመራ መርጌታው ነው።(ሚ.ያዚ.ያ 2003)

### 2.2.7.2.7 የክዋኔ ማዕቀፍ

አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን ከክዋኔው መሪዎች በተጨማሪ የራሱ የሆነ የተወሰነ ማዕቀፍ[12] (frame) አለው። ከዚያ ከተፈቀደለት ማዕቀፍ ሊወጣ አይችልም። ምክንያቱም ከተፈቀደለት ማዕቀፍን እና የአከዋወን ስልት ከወጣ አጠቃላይ የክዋኔው ድባብ ይበላሻል፡ ፡ ይህ ደግሞ ክዋኔውን በአግባቡ እንዳይከወን ያደርገዋል። ስለዚህ በተፈቀደለት የክዋኔ ማዕቀፍ መከወን የግድ ነው። ከዚህም በተጨማሪ አንድ የክዋኔ ማዕቀፍ መጀመርያ (Begning)፣መካከል(Midle) እና መጨረሻ(Eniding) ሊኖረው ይችላል።

በአጠቃላይ አንድ የፎክሎር ባለሙያ አንድን የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ (Theory) ለማጥናት ሲነሳ ግምት ውስጥ የሚገቡና የማይቀሩ ነገሮች፤ የከዋኙ የግል ተውኔታዊ አቀራረብ (Performer dramatization)፤ የተመጠነ ምታዊ እንቅሳቃሴ(Rhythmic movement) የሰውነት እንቅሳቃሴ እና የፊት ገጽታ (Gestures and Facial Expressions)፤ የአከዋወን ስልት (Performing style)፤ የከዋኙና የታዳሚው መስተጋብር(Interactions between Performer and Audience)፤ የክዋኔው መቼት(Setting)፤ የአከዋወኑ ሁኔታ (Performing Situation)፣ የክዋኔው አጠቃላይ ድባብ (Performing Atmosphere) በሚገባ ማጤንና ማስተዋል ተገቢነት እንዳለው (Bauman፣1977፣28፤Mackdonald፣1972፣410፤ Finnnegan፣1977፣214፤ Sims እና Stphens ፣2005፣155፤) ይጠቁማሉ።

ከዚህ በላይ የፎክሎር ክዋኔ ባሕሪያት ከሥርዓተ ማሌት አገልግሎት ጋር በማያያዝ ቀርቧል። ሥርዓተ ማኅሌት ውጤታማ የሚሆነው ደረጃዎችን ጠብቆ ሲከወን ነው። በመሆኑ ከዚህ በታች የሥርዓተ ማሕሌት ደረጃዎች እንመለከታለን።

## 2.2.8 የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች

ሥርዓተ ማኅሌት በከበሮ፣ በመቋያሚና በጸናጽል ታጅቦ ለእግዘአብሔር የሚቀርብ ምስጋና መሆኑ ከዚህ በፊት ተገልጿል።

በሥርዓተ ማኅሌት አስር ደረጃዎች አሉ። እነዚህ ደረጃዎች23. አስር መሆናቸው ቅዱስ ዳዊት "አስር አውታር ባለው መዝሙር እዘምርልሃለሁ" (መዝ 150፣3-5) ያለውን

---

[12] በመስክ ቆይታየ እንዳስተዋልኩት ስርዓተ ማሕሌት በከበሮ፣ በጸናጽልና በመቋሚያ የሚታጀበው የራሱ የሆነ የአከዋወን ስርዓት የራሱ የሆነ ቀለም ስላለው ነው። ስርአተ ማሕሌቱ ሲከወንም ከዚህ ማዕቀፍ አይወጣም። የስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ መሪዎች ከስርዓተ አቋቋሙ ውጭ አይቆሙም። የስርዓተ ማሕሌት ተሳታፊ ህዝበ ክርስቲያንም የስርዓተ ማሕሌቱን አቋቋም ተከትለው በእልልታና በጭብጨባ ደስታቸውን ይገልፃሉ።(ሚያዚያ 2003)።

መሰረት በማድረግ እንደሆነ (ከፍ.ያለው፣1986፣72)፤ማህበረ ቅዱሳን፣1993፣3) ይገልጻሉ። የስርዓተ ማሕሌት ደረጃዎች እርስ በርስ የተያያዙ ከመሆናቸው የተነሳ አንዱን ከሌላው መለየት አይቻልም። እነዚህም ደረጃዎች የራሳቸው የሆነ ትርጉምና ትዕምርታዊ ውክልና አላቸው (ማህበረ ቅዱሳን፣ 1993፣ 28-29፤ 2000፤ 124-125፤ ሀብተማርያም1963፣106-108 እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

1. **መቃኘት፡-** ቃለ እግዚአብሔሩን መዘምራኑ እንዲያስታውሱትና በአንድ ቃል እንዲዘምሩት ማድረግ ነው።
2. **መቀበል፡-** የተቃኘውን ቃለ እግዚአብሔር ከቃኚው ተቀብሎ በአንድነት መዘመር ነው።
3. **መምራት፡-** ቃለ እግዚአብሔርን በዜማ ለሌላው ማቀበል ነው።
4. **መመራት፡-** ቃለ እግዚአብሔርን ከመሪው ተቀብሎ ማዜም ነው።
5. **ዝማሜ፡-** በመቋሚያ ግራናቀኝ መዝመምና ቀና ብሎ መቋሚያውን ከዜማው ጋር አስማምቶ ከመሬት ላይ መጣልና መደሰቅ ነው።
6. **ንዑስ መረገድ** ይህ ክፍለ ማሕሌት በግራ እጅ መቋሚያ፣ በቀኝ እጅ ጸናጽል ተይዞ ቀጥ ብሎ በመቆምና ጸናጽሉን ላይና ታች እየጣሉና ከበሮ እየመቱ የሚያዜሙት ነው።
7. **ዓቢይ መረገድ፡-** ከንዑስ መረግድ በኋላ ዜማውን ፈጠን ባለና ሞቅ ባለ የከበሮ አመታት እየተደረበ፣ እንዲሁም መጠነኛ የሆነ የአካል እንቅስቃሴ ወደ ቀኝና ግራ እየተደረገ፣ ጸናጽሉም እንደ ከበሮ ፈጠን እያለ የሚባል ነው።
8. **ጽፋት፡-** ቃሉ ጸፍዐ በጥፊ መታ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሆኖ ትርጉሙ በጥፊ መምታት ማለት ነው። ይህ ክፍለ ማሕሌት ጸናጽሉም ሆነ ከበሮው በፍጥነት እየተመታ የሚባልበት ነው።
9. **ድርብ ጽፋት፡-** በጸናጽል በዜማ ቃና(ጉሮሮ) ከተራው ጽፋት በአመታት ለየት አድርጎ መዘመር ነው።
10. **የጭብጨባ ጽፋት፡-** ከተራው ጽፋት ጋር በጉሮሮው( በአጣጣሉ) በመጠኑ ፈጠን ፈጠን አርጎ በጸናጽል ፈንታ እያጨበጨቡ በከበሮ መዘመር ነው።

## 2.2.9 ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት፣ ትዕምርታዊ ውክልና

ስለ ንዋያተ መዝሙራት ትዕምርታዊ ውክልና ከማየታችን በፊት ስለ ምንነቱ ፣አሰራሩ እና አመጣጡ በቅድሚያ እንመልከት።

### 2.2.9.1 የንዋያተ መዝሙራት ምንነት

"ንዋይ ማለት ገንዘብ ማለት ነው። ቅዱስ ማለት ደግሞ የተለየ፣ የተከበረ፣ የተመረጠ ማለት ነው። ንዋያተ ቅድሳት ማለትም በቤተ-ክርስያቲያን የአምልኮ ስርዓት የሚፈፀምባቸው የተቀደሱ እቃዎች ማለት ነው" ኪዳነ ወልድ (1948፣632)። እነዚህ ንዋያተ ቅዱሳት ከሌሎች እቃዎች የተለዩ ናቸው። የተለየ የሚያደርጋቸውም የሚቀቡት ቅባትና የሚደረግላቸው ጸሎት ነው። ይህ ስርዓት ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የነበረ ነው። "የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት፣ ገበታውንም፣ እቃውንም ሁሉ፣ መቅረዙንም፣ የዕጣን መሠውያውንም፣ ለሚቃጠል መስዋዕት የሚሆነውን መሰዊያና ዕቃውንም ሁሉ የመታጠቢያውን ስንና መቀመጫውንም ትቀባለህ፡ ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ፣ ቅድስተ ቅዱሳንም ይሆናል" (ዘፀ 30፣26-30)።

ከላይ ከተገለፀው መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ የምንገነዘበው ንዋያተ ቅድሳት ከሌሎች እቃዎች የተለዩ፣ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሁም ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ መሆናቸውን ነው። በመሆኑም ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል ለስርዓተ ማኅሌት መከወኛ የሚውሉት ከዚህ በመነጨ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል።

### 2.2.9.2. የንዋያተ መዝሙራት አሰራር እና አመጣጥ

**1.መቋሚያ፡** መቋሚያ የሚሰራው ከእንጨት ነው፣ ዘንጉ እንጨት ሆኖ ላዩ ከብር፣ ከወርቅ፣ ከነሀስ፣ ከመዳብ፣ ከብረትም ሊሰራ ይችላል። አገልግሎቱም ለመደገፊያነት እና የማሕሌትን ስነ-ስርዓት ለመምሪያ ነው ።

**2.ጸናጽል፡** ጸንጸለ መታ ከሚለው ግስ፣ የተገኘ ስም ሲሆን ነብየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት "እግዚአብሔርን ድምፀ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑ" በማለት ጸናጽል ለዝማሬ ያለውን ታላቅ አገልግሎት ገልጿል። (መዝ 150፣1) ፣ (1ኛ ቆሮ 13፣2)፣ (2ኛ ዜና 29፣25)፣ (1ኛ ዜና 15፣16)።

**3.ከበሮ፡** ከበሮ የሚባለውንዋየ መዝሙር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ልዩ ድምፅ ያለው ውስጡ የተፈለፈለ እንጨት ሆኖ በቆዳ የተጠፈረ ነው።

የእነዚህን ንዋያተ መዝሙራት ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ሀሳቦችን ይሰነዝራሉ። አንዳንዶቹ "ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል ከብሉይ ኪዳን የተወረሱ ናቸው" (ከፍያለው፣1986፣72፣ ሀብተ ማርያም፣1963፣123) ይላሉ። ለዚህም እንደ መረጃ የሚያቀርቡት መፅሐፍ ቅዱስን ነው (መዝ 150፣3-5)። ሥርግው ገላው ደግሞ "ከበሮ፣ መቋሚያና ጸናጽል ከእስራኤል ይልቅ አፍሪካዊ መሰረት ያላቸው ናቸው" ይላሉ (ያልታተመ መጣጥፍ 2-3)።

ከላይ ከተጠቀሱት የምሁራን ሐሳቦች መገንዘብ የሚቻለው የእነዚህን የዜማ መሳሪያዎች ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ ሁሉንም የሚያስማማ እና አንድ ወጥ የሆነ ሐሳብ አለመኖሩን ነው። ሆኖም ግን ምሁራኑ የዜማ መሳሪያዎቹ የሚወክሉት ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) ውክልና እንዳላቸው በሐሳብ ይስማማሉ።

## 2.2.9.3. የቁሳዊ ባህሎች ምንነትና ተምሳሌታዊ ውክልና

### 2.2.9.3.1. የቁሳዊ ባህሎች ምንነት

ቁሳዊ ባህል (Material Culture) አንድ የፎክሎር የጥናት ዘርፍ (gener) ነው:: ስለዚህ ከበሮ፣ መቋሚያና ጸናጽል የተሰኙት የሥርዓተ ማኅሌት የክዋኔ መሳሪያዎችም በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደቡ ናቸው።

በፎክሎር እያንዳንዱ ቁስ የራሱ የሆነ የሚወክለው ነገር አለ። ትዕምርታዊ (ተምሳሌታዊ) ውክልናውን በሚገባ መገንዘብ ካልተቻለ የፎክሎር ጥናት ውጤታማ አይሆንም። ስለዚህ ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል የተሰኙት ንዋያተ መዝሙራት ሥርዓተ ማኅሌትን ለማከናወን ወሳኝ ናቸው የተባሉበት ዋናው ምክንያት ሥርዓቱን አስመልክተው የሚወክሉት እና የሚሰጡት ትርጉም ስላላቸው ነው።

ስለ ቁሳዊ ባህል ምንነት የዘርፉ ምሁራን የተለያዩ ሐሳቦችን አስፍረዋል።
Hennery "በቁሳዊ ባህል ቁስ አካልና አእምሮ በነሮች ውስጥ አንድ የሚሆኑበት አጋጣሚ (ክስተት)፣ ሁናቴ ነው" (1999፡1 ይላሉ።በተመሳሳይ መልኩ Jones "ቁሳዊ ባህሎች ሰዎች የሚሰሯቸው፣ የሚጠቀሟቸው ሲሆኑ ከሚሰጡት ጥቅምና አገልግሎት በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚወክሉት ነገር አለ" (1972፤9) በማለት ይገልጻሉ።

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ሐሳብ የምንገነዘበው ቁሳዊ ባህሎች ሰዎች ከአካባቢያቸው በሚያገኙዋቸው መሳሪያዎች በመታገዝ ወጋቸውን፣ ባህላቸውን እና የእምነት ከባህሎች ከዚህ በፊት የነበረውን የጥበብ፣ የፍልስፍና፣ የአስተሳሰብ፣ የአተያይ ሁኔታዎችን የሚያንፀባርቁ መሆናቸው ነው።

### 2.2.9.3.2. የቁሳዊ ባህሎች ተምሳሌታዊ ውክልና

ስለ ትዕምርታዊ ውክልና የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ሐሳቦችን ሰንዝረዋል። Ritzer "ትዕምርቶች ሰዎች አንድን ጉዳይ ከቁሳዊና ከማህበራዊ ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት በመረዳት ለመስየም፣ ለመመደብና ነገሮችን በክፍል በክፍል ለማደራጀት የሚያግዝ ነው" (2000፤360) በማለት ገልጸዋል።

Ballenger በበኩላቸው "ተምሳሌት አንድን ቁሳዊ አካል ሞራላዊ (Moralistic) እና መንፈሳዊ እውነት (Spiritual truth) ወክሎ የሚቆም ነው። (1988፣769) በማለት የተምሳሌትን ተግባር ምን እንደሆነ ጠቁመዋል። ከዚህ ሐሳብ መገንዘብ የሚቻለው በትዕምርታዊ ውክልና የሚወከሉ ቁሶች በማኅበረሰቡ ወይም በአንድ እምነት ተከታይ ዘንድ ትርጉም ያላቸው መሆናቸው ነው።

ከላይ ከተገለጹ ሃሳቦች መገንዘብ የሚቻለው ሰዎች በቁሳዊ ባህሎቻቸው ምክንያት ለነገሮች ምሳሌ መስጠትን፣ መረጃ ማቀበልን እና ማኅበራዊ መስተጋብር መፍጠር የሚችሉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በትዕምርታዊ ውክልና የሚወከሉ ቁሶች በማህበረሰቡ ወይም በአንድ እምነት ተከታይ ዘንድ ትርጉም ያላቸው መሆናቸው ነው።

ትዕምርታዊ ውክልና በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን የተለመደ ነው ማለት ይቻላል። ትዕምርት (ተምሳሌት) የራሱ የሆነ ተግባር አለው። Shipley "ትዕምርት/ተምሳሌት/ የቤተ-ክርስቲያን እምነት በተለይም የሐዋርያትን እምነት አጠቃሎ የያዘ ነው።አንድ ነገር አንድን ሌላ ነገር የሚወክለው በቀጥተኛ ተመሳስሎ (ተምሳሌት) ሳይሆን በስውር አገላለጽ ወይም በጋራ ስምምነት በተፈጠረ ግንኙነት ነው። ስለሆነም ቀጥተኛ ውክልና የሚባል የለም" (1970፣321) በማለት ትዕምርታዊ ውክልና በቤተ ክርስቲያን የጎላ ድርሻ እንዳለው ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ የአንድን ነገር ውክልና ለማወቅ የማኅበረሰቡን ወይም የእምነቱን ተከታዮች የአተረጓጐምና የምሳሌ አሰጣጥ ዜዴን በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል።

የሥርዓተ ማኅሌት ንዋያተ መዘሙራት (ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል) ተምሳሌት ለማወቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዶግማን እና ቀኖናን እንዲሁም መረዳት ያስገልጋል። ከዚህም በተጨማሪ የቤተ-ክርስቲያኗን የአተረጓጐም ይትባሃል እና የተምሳሌት አሰጣጥ መንገድ መገንዘብ ያስፈልጋል።

# 3. የኮረም ወረዳ አካባቢያዊ ዳራ

## 3.1 ኮረም እና አካባቢዋ

ኮረም በደቡባዊ ዞን በትግራይ ክልል ውስጥ የምትገኝ ወረዳ ስትሆን ከአዲስ አባባ በስተ ሰሜን በኩል 619 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ይህች ከተማ በሰሜን እንዳ መኾኒ፣ በሰሜን ምስራቅ ራያ ዓዘቦ፣ በደቡብ ምስራቅ አላማጣ ፣ በምዕራብ ሰቆጣ ያዋስኗታል፡፡

የኮረም ጠቅላላ የህዝብ ብዛት 16,895 ሲሆን ከዚህም 7,135 /45.02 %/ ወንዶች 8,715 (54.98 %) ሴቶች ናቸው፡፡ ኮረም ከተማ 1,379 ሄክታር ያላት ስትሆን ከባሕር ወልል በላይ 2,400 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች ፡፡ አየር ንብረቱ ደጋ ሲሆን በአመት ሁለት ጊዜ የመከር ምርቶች ይመረቱባታል፡፡ ለመኖሪያ እና ለኢንቨ ስትመንት ምቹ ከተማ ናት፡፡( የኮረም ማዘጋጃ ቤት መዛግብት 2009)

## 3.2. ስያሜና አመሰራረት

ኮረም የሚለው ስያሜ የመጣው ኮር ከሚለው የአገውኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ፀሐይ ማለት ነው፡፡ ኮረም በከተማነት የተመሰረተችው በዋግሹም ብሩ ነው፡፡ (የኮረም ማዘጋጃ ቤት መዛግብት 2009)

## 3.3. በኮረም ከተማ የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች

ኮረም የተለያዩ የቱሪስት መስህቦች አላት፡፡ ከእነዚህም መካል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### 3.3.1.የተቀደሱ የጸበል ቦታዎች

የአቡነ ተክለ ሐይማኖት፣ የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ፣ የኪዳነ ምህረት፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የቅዱስ ሚካኤል እና የአማኑኤል የጸበል ቦታዎች የቱሪስት መስህብ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በምዕራብ ሐሸንጌ በምፍሳስ ባህሪ (ወዲ ሐያሎ) በኩል ደግሞ የአቡነ ገሪማ ጸበል ተጠቃሽ ነው፡፡ እነዚህም የጸበል ቦታዎች በብዙ ሰዎች ይጎበኛሉ፡፡ጎብኚዎቹም በሁለት ይከፈላሉ፡፡ አንደኛ በበሽታ እና በተለያዩ ችግሮች የተጠቁ ሰዎች ሲሆኑ ከከተማው የአንድ ሰዓት ተኩል የእግር ጉዞ በማድረግ ወደ ፀበል ቦታዎቹ በመሄድ ለሳምንት፣ለሁለት ሳምንትና ለወር በመቆየት ከበሽታችን እንፈወሳለን ብለው የሚያምኑ ሲሆኑ ሁለተኛ ወገን ደግሞ የጸበል ቦታዎቹን እንደ መዝናኛ በመጎብኘት እርካታ የሚያገኙ ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ የጸበል ቦታዎች በወረዳው እንደ ቱሪስት መስህብ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

### 3.3.2. የሼክ ቢላል የተቀደሰ ቦታ

የሼክ ቢላል የተቀደሰ ቦታ እየተባለ የሚጠራው ቦታ የኮረም እና የአካባቢው ህዝቦች ድርቅ፣ ተላላፊ በሽታዎችና ግጭቶች ሲኖሩ ለመጸለይ የሚጠቀሙበት ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም ታሪካዊ ቦታነቱን መሰረት በማድረግ ጎብኘዎች ጉብኝት ያካሂዱበታል፡፡

### 3.3.3. ታሪካዊ የጦር ሜዳ ቦታዎች

ለዞኑ የቱሪስት መስህብ ሁነው የሚያገለግሉ እንደ የአምባላጌ ጦርነት (1895) እና የማይጨው ጦርነት (1935) ታሪካዊ ቦታዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የማሽላታት በዓት(ዋሻ) የማይጨው ጦርነት በ1935 ዓ.ም በተካሄደ ወቅት አፄ ኃይለ ስላሴ ከጣሊያን የአየር ድብደባ ለመዳን ሲሉ የተጠጉበት በዓት ነው፡፡ በዚህ በዓት የአካባቢው ህዝቦች ከብቶቻቸውን አስጠልለውበታል። ቦታው በከብቶች ማገጃነት በመቆሸሹ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከማሽላታት ዋሻ(በዓት) ወደ ዋሻ(በዓቲ) ሐያሎ ሄዱ። ከዚህም በተጨማሪ በዓቲ ወደሳይ(ዋሻ) አፄ ኃይለ ስላሴ ከጣሊያን የአየር ድብደባ ለማዳን የተጠጉበት ሌላው በዓት ነው፡፡ ይህም በዓት ከኮረም 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ለወረዳው የቱሪስት መስህብ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በሶፍያ ተራራ በፋላ አካባቢ የሚገኝ ሌላው ተጠቃሽ የቱረስት መስህብ ማር.ያም በዓት ነው፡፡ ይህ በዓት 50 ሜትር ቁመት እና 18 ሜትር ጥልቀት አለው ፡፡

### 3.3.4.የአሮጌ ኮረም መሰረት

ይህ የአሮጌ ኮረም መሰረት ከተማዋ ስትቆረቆር የነበረውን ገፅታ የሚያመላክት በመሆኑ በቱሪስት መስህብነት የሚጠቀስ ቦታ ነው፡፡ አሮጌ ኮረም በዋግሽም ብሩ የተመሰረተ ሲሆን የድሮ ነገስታት መኖሪያን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሰዎች ታሪካዊ ዳራውን መሰረት በማድረግ ወደ ቦታው እየሄዱ ጉብኝት ያካሂዳሉ፡፡

### 3.3.5. የሆላ ፏፏቴ

በኮረም ከተማ ሌላው ተጠቃሽ የቱሪስት መስህብ የሆላ ፏፏቴ ነው፡፡ የሆላ ፏፏቴ በአጼ ኃይለስላሴ በዓት እና በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ይገኛል፡፡ ከከተማው የ15 ደቂቃ የእግር መንገድ የሚያስኬድ ሲሆን እጅግ የሚማርክ ፏፏቴ ያለው በመሆኑ ቱሪስቶች፣ የአካባቢው ሰዎች እና ሙሽሮች ወደ ፏፏቴው በመሄድ ፎቶ ይነሳሉ፡፡

### 3.3.6. ምፍሳስ ባሕሪ (ወዲ ሐያሎ)

ይህ ታሪካዊ ቦታ የአክሱማዊት ስልጣኔ እና የክርስትና መስፋፋትን የሚያወሳ ታሪክ የያዘ ቦታ ነው። ይኸውም አንደኛ የአክሱማውያን የቤት ህንፃ አሰራር ቅሪቶች እና የአክሱማውያን ቤተክርስቲያን ህንጻ አሰራር የሚያመላክት ዋሻ ነው። በመሆኑም ሰዎች የዋሻውን ታሪካዊ ዳራ መሰረት በማድረግ ጉብኝት ያካሂዳሉ።

### 3.3.7. ትኹል እምኒ

ትኹል እምኒ በትግርኛ ቋንቋ የቆመ ድንጋይ ማለት ነው። ይህም ቦታ ወምበረት እየተባለ በሚጠራ አካባቢ ከኮረም በደቡብ ምዕራብ በኩል ይገኛል። የድንጋዩ ከለር ቀይ በመሆኑ በአካባቢው ካሉት ድንጋዮች የተለየ ነው። ድንጋዩ ዓዲ ደቂ ሐያሎ ወይም ምፍሳስ ባሕሪ ( ሐሸንጌ አካባቢ) ከሚገኘው ድንጋይ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የትኹል እምኒ ግን በቁመት ረጅም ነው። ትኹል እምኒ ከሐሸንጌ ሐይቅ አፈ-ታሪክ ጋር ተያያዥነት አለው። እንደ አከባቢው አፈ-ታሪክ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሐያሎ ተነስታ ሐሸንጌ ወደ ሚባለው አካባቢ በመሄድ እንዲያስተናግዱት ተማፀነች። የሐሸንጌ ሰዎች ግን በእንግድነት ሊስተናግዱት ቀርቶ የነበራትን የወርቅ ጫማ በመስረቅ እና በመዘባበት ሸኟት። በዚህ ጊዜ ድንግል ማርያም ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ታቅፋ ስለነበር ትኹል እምኒ ከሚባለው ቦታ ስትደርስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ሁኔታው ተቆጥቶ ሐሸንጌን ገለበጠው። አካባቢውም ወደ ሐይቅ ተለወጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሐሸንጌ ሐይቅ እየተባለ ይጠራል። ትኹል አምኒ የተባለበት ምክንያት እመቤታችን ስለቆመችበት ነው። ትኹል እምኒ ዓዲ ደውታ በመባልም ይጠራል።

### 3.3.8. የሐውሰዋ ተራራ

ይህ ተራራ ሌላው የኮረም ወረዳ የቱሪስት መስህብ በመሆን ያገለግላል። ምክንያቱም ተራራው ላይ በመውጣት የኮረምን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በሚገባ ለማወቅ እና በከተማ የሚገኙ አካባቢዎችን ለመርዳት ያስችላል፡

## 3.4 ማኅበራዊ ሁኔታ

### 3.4.1.ጋብቻ

ከኮረም ከተማ ነዋሪዎች ለጥናቱ ከተወሰደው ናሙና 2,338 አባላት ውስጥ 62.3% ያገቡ ሲሆኑ 37.7 % ደግሞ ያላገቡ ናቸው። (Own Survey, Korem March, 2009)።

### 3.4.2. የብሔር ስርጭት

የኮረም ከተማ ነዋሪዎች ከጠቅላላው 16,895 ሕዝቦች መካከል 12,412 (73.4%) ትግራዎት ሲሆኑ 21.4% አማራ፣ 5% አገው እና የቀሩት ደግሞ ደግሞ ኦሮሞ እና ኤርትራውያን ናቸው።(CSA,The 1994 PHC of Ethiopia: Results for Tigray Region, V,I, Statistical Report,P.78.)።

### 3.4.3.ሐይማኖት

ከጠቅላላው 16,895 የኮረም ህዝብ 15,175(89.9%) የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ፣ 1,695(10.03%) ሙስሊም ሲሆን ሌሎች የቀሩት ደግሞ የፕሮቴስታንት እና የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ናቸው።(CSA, The 1994 GZC of Ethiopia Results for Tigray Region, V,I,statistical Report, P, 110.)

## 3.5. መሰረተ ልማት

ኮረም የፖስታ፣ የስልክ፣ የመንገድ፣ የኤሌክተሪክ፣ የትምህርት ቤት፣ የህክምና የውሃ አገልግሎት መሰረተ ልማቶች ተጠቃሚ ናት። (Korem Town Municipality 2009.)።

### 3.5.1.ዘመናዊ ትምህርት

በኮረም 2 የአፀደ ህፃናት ትምህርት ቤት፣አንድ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት(1-4)፣ 1 መለስተኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት(5-8)፣1 ከፍተኛ ደረጃ (9-10)፣1 መሰናዶ ትምህርት ቤት (11-12)እና አንድ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ይገኛሉ።

46.4% የኮረም ህዝብ ያልተማሩ ሲሆኑ 52.9% ደግሞ ከመጻፍና ከማንበብ ጀምሮ እስከ ኮሌጅ የደረሱ ናቸው። ከእነዚህም 24.9% የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፣ 7.6% የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣4.7% TVET ኮሌጅ እንዲሁም 2.1% በ BA(BSC) ተመርቀዋል (own survey, korem march,2009) ።

### 3.5.2. ንግድ

ከኮረም ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው 783 የንግድ ፈቃድ ያላቸው ህጋውያን ነጋዴዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም በ7.65 ሚሊዮን ብር ካፒታል ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የኮረም ከተማ 56% በንግድ እንቅስቃሴ 20% ደግሞ በኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ የተሸፈነ ነው። ጠቅላላ ንግድ(total buiness) 19% እና የጅምላ ንግድ(Whole sales) 5% የተሸፈነ ነው (Korem Town Trade, Industry and Transport office 2009)፡፡

### 3.5.3. ኢንቨስትመንት

ከኮረም ከተማ ማዘጋጃ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያላክተው 58 ሰዎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን አጠቃላይ ካፒታላቸውም 79 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 41 ፕሮጀክቶች ጊዜያዊ (optional) ሲሆኑ 14 ፕሮጀክት ደግሞ ተግባራዊ ሁነዋል፡፡ በከተማው ከሚገኙ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች 20(34.5%) ሆቴሎች፣15(25.9%) ንግድ፣ 11 (19.0%) ፣ትራንስፖርት፤ 8(13.8%) አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ፣4(6.9%) ግብርና ይገኙባቸዋል (Korem Town Municipality 2009)፡፡

### 3.5.4. ጤና

ኮረም 1 መንግስታዊ ጤና ጣቢያ፣1 መለስተኛ ክሊኒክ፣ 1 የመንግስት መድሐኒት ቤት፣ 1 የግል መድሐኒት ቤት ፣ 1 በመሰራት ላይ ያ መለስተኛ ሆስፒታል አላት፡፡ ከዚህም ጋር 20 በተለያዩ ሙያዎች የተመረቁ የጤና ባለሙያዎች፣15 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣1 የጤና መኮንን ፣17 ነርሶች፣ 2 ላብራቶሪ ቴክኒሻን ይገኛሉ (korem town health office 2009)፡፡

## 3.6. የደብረ ገነት ኃያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን አመሰራረት እና እድገት

ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን ቀደም ብላ በአፄ ካሌብ እንደተተከለች (እንደ ተመሰረተች) ይነገራል፡፡የእመቤታችን ፅላት አፄ ካሌብ በዓቲ ማሽላታት ከሚባለው ቤተክርስቲያን አስርተው እንድትቀደስና እንድትወደስ አደረጉ፡፡በ9ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ዮዲት ጉዲት አብያተ-ክርስቲያናትን፣ ቅድሳት መጻሕፍትን፣ የአብያተ ክርስቲያናትን ቅርሳቅርሶች እያቃጠለች በነበረችበት ዘመን ይህች ፅላት በእግዚአብሔር ቸርነት ሳትቃጠል እንደቀረች ይነገራል (ወንጌሉ ዘወርቅ፣ አሰፋ ብርሃኑ 1993፣1፤አየለ ከልካይ ሚያዝያ17/09/ 2003 የተደረገ ቃለ መጠይቅ)

የእመቤታችን ፅላት በዓቲ ከሚባለው ቦታ የሚገኝ ትልቅ ዋሻ ሁና ለረጅም ዓመታት ባሕታውያንና መናንያን ሲቀድሷትና ሲያወድሷት ኖሩ፡፡ ከዚያ በኋላ የእመቤታችን ፅላት ከዋሻው አውጥተው አሁን ጊዮርጊስ ካለበት ቤተክርስቲያን አስገቧት፡፡ አሁን ጊዮርጊስ ያለበት ቤተክርስቲያን ዓዲጠሽና ይባል ነበር፡፡ እዚያ አካባቢ ዓሊ የሚባል እስላም ነበርና ክርስቲያኖች እመቤታችን በገደል መኖር ስለሌባት የዓሊን ቤት አስለቅቀን ጽላትዋ እናስገባ ተባብለው ተስማሙ፡፡ ዓሊ ይህን የክርስቲያኖች ውሳኔ ሰምቶ ወንድሙ ድሎን ክርስቲያኖች የማርያም ጽላት ከእኔ ቤት ሊያስገቡ እንዳሰቡ ሰምቻለሁና ቤቴን ጠብቅ ብሎት ወደ ሌላ ስራ ሄደ፡፡ክርስትያኖችም የማርያምን ጽላት ከበዓቲ ማሽላታት ወስደው ወደ ዓሊ ቤት አስገቧት፡፡ ዓሊ በርሃ ውሎ ማታ ሲገባ ከቤቱ ታቦት ገብቶ አገኘና ሊገባም ቢል ፅላትዋ አላስገባም አለችው።

ዓሊም በሁኔታው ተናዶ ድሎን ሊገድለው ጨቤ ወረወረ፣ ድሎ ግን ከተወረወረው ጩቤ አመለጠና ወደ አላማጣ አቀና። በዚያም መንደር መሰረተ።በአላማጣ እስከ አሁን ድረስ የድሎ መንደር የሚባል አለ (ወንጌሉ ዘወርቅ፣የካቲት19፣1989፤አሰፋ ብርሃኑ 1993፣1፤አየለ ከልካይ ሚያዚያ 17/092003 የተደረገ ቃለ መጠይቅ)

ይህች ቤተ ክርስቲያን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግራኝ መሐመድ አብያተ ክርስትያናት እንደ ዩዲት ጉዲት ሲያቃጥልና መጻሕፍት ሲበረብር የማርያም ጽላት አልቃጠል አለችው።በዚህ ጊዜ በተአምሯ ተገርሞ ይህች ሐያል ታቦት ናት ብሎ ተናገረ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ አካባቢው ኃያሎ ተብሎ ተጠራ፡፡ እንደ አካባቢው ሰዎች ትረካ ጽላቷ ብዙ ተአምራትን እያደረገች እስከ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ደረሰች፡፡ አፄ ምኒሊክ የጣልያን ወረራ ለመከላከል ወደ ዓድዋ ሲዘምቱ በዚች ቦታ ላይ አረፉ። የሕዝቡን ንቃት አይተው ይህች ቦታ ማን ትባላለች ብለው ሲጠይቁ ኃያሎ በማለት መለሱላቸው። አፄ ምኒሊክም ድሉ የእኛ ነው ብለው ተስፋ አደረጉ፡፡ በመቀጠልም አጼ ምኒሊክ “እመቤቴ ሆይ ድል አድርጌ ስመለስ እደብርሻለሁ” ብለው ተሳሉ፡፡ ጉዛቸውን ጨርሰው ዓድዋ በደረሱ ጊዜ የካቲት 23, 1988 ዓ.ም ድል አደረጉ፡፡

አጼ ምኒሊክ ዓድዋ ላይ ድል ተቀዳጅተው ከተመለሱ በኃላ በማይጨው፣ ጨርጨር አድርገው አዲስ አበባ ገቡ፡፡ በዘመኑ ለነበሩ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ኃያሎ ማርያም ለምትባል ቤተክርስትያን ዓድዋ ድል አድርጌ ስመለስ እደብርሻለሁ ብዬ ተስዬአለሁና ይደብሩልኝ ብለው መልእክት ላኩባቸው። ጳጳሱም ወደ ኃያሎ በመሄድ

ድንኳን ዘርግተው የሐያሎን ባላባት ጥሩልኝ አሉ። በዚህ ጊዜ አለቃ ወጋሕታ ተጠሩ። አንተ የኃያሎ ባላባት ከሆንክስ ዳር ድንበር ንገረኝ፤ ይህች ቤተክርስቲያን ልደብራት ነው አሉ። አለቃ ወጋሕታ ማይዘሩት፣ ጋንዳ ጫፍ፣ ፣ ጨሏቅ፣ መንጫቅ ባህር፣ መሳኑ ብለው ነገሯቸው ። አቡነ ጴጥሮስም በ100 ቀሳውስት፣ በ30 ቆሞሳት " ዳርዋ እሳት መሐልዋ ገነት ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም" ተብላ በምስሌነ ተቆጣጣሪነት፣ ንጉስ ወይም ዋግሹም የሾመው ድንግል መነኩሴ፣ መምህር እና አፈመምህር ብቻ ትተዳደር። ከዚያ ውጭ ማንም ሰው እንዳያስተዳድራት በህዳር 21 ቀን 1988 ዓ.ም ደበሯት። ይህችው ደብር "ዳርዋ እሳት መሀሏ ገነት" ተብላ ከተደበረችበት ጊዜ ጀምሮ ቀደም ብሎ በነበረው ስርዓት ሰው ነፍስ አጥፍቶ ወይም ሌላ ወንጀል ሰርቶ ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ ደወል ከደወለ ማንም እንዳይነካው የሚል ህግ ነበራት። (ወንጌሉ ዘወርቅ፣የካቲት19፣1989፤ አሰፋ ብርሃኑ 1993፣1፤አየለ ከልካይ ሚያዚያ 17/092003 የተደረገ ቃለ መጠይቅ)።

ሐያሎ ማርያም በሰሜን ከጨለቆት ስላሴ፣ በደቡብ ደግሞ መርጦ ኢየሱስ ከሚባሉ ትላልቅ አድባራት ትመደባለች።ይህም በወንጌሉ ዘወርቅ የካቲት 19, 1989 በጽሑፍ ላይ ተፅፎ ይገኛል።

አፄ ምኒሊክ ቤተ ክርስቲያኗን ሲደብሩ ለቤተ ክርስቲያኗ መተዳደሪ የሚሆን ጋሻ መሬት ሰጥተዋት ነበር። በደርግ ጊዜ የተወሰነ መሬቷ ተወስዶ የተወሰነ ቢቀርም በአሁኑ ወቅት ግን ምንም ዓይነት ጋሻ መሬት የሚባል መተዳደሪያ የላትም።

አጼ ምኒሊክ በደቡብ ጨለቆት እስከ ሚባል ቦታ ድረስ ግማሹ የደብረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ግዛትና ግማሹ ደግሞ የአባ ኪሮስ ግዛት እስከሆነው ድረስ፤ በሰሜን በኩል ማይዘሩት፣ በምዕራብ በኩል ደግሞ ወንበረት፤ በምስራቅ በኩል ዳዮ እስከሚባሉ ቦታዎች ድረስ አዋሳኝ አድርገው ግዛቷ እንደደበሯት የጽሑፍ የመረጃዎች ያመለክታሉ።(ወንጌሉ ዘወርቅ፣የካቲት19፣1989፤አሰፋ ብርሃኑ 1993፣1)።

የሐያሎ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የለመኗት የማትነሳ፣ የተናገሯት የማትረሳ ከመሆኗ የተነሳ "አይረፈዳ ማርያም" (የማይረፍድባት ማርያም) እየተባለች ትጠራ ነበር። ይህች ተአምረኛ ቤተ ክርስቲያን አጼ ኃይለ ስላሴ በጣልያን ወረራ ጊዜ ከነበረው የቦንብ ድብደባ ለማምለጥ ለአንድ ወር ያህል የተደበቁባት ናት። በጊዜው በነበረው የማይጨው ጦርነት ምክንያት ጣልያኖች በተከታታይ ቦንብ ቢያፈነዱም ቤተ ክርስቲያኗ ሆነ አጼዱ ምንም ሳይነኩ በመቅረታቸው አጼ ኃይለ ስላሴ እጅግ እንደተገረሙ ይነገራል(ወንጌሉ ዘወርቅ፣የካቲት19፣1989፤አሰፋ ብርሃኑ 1993፣1፤አየለ ከልካይ ሚያዚያ 17/092003 የተደረገ ቃለ መጠይቅ)

ሐያሎ ማርያም ጥቅምት 14 ቀን 1947 ዓ.ም ተከተመች፡፡ ይህም ቦታ ከ 1928-1935 ካቶሊካውያን ይቀደሱበት እንደነበረ ይነገራል። ጣልያኖች ከለቀቁ በኋላ ተዘግቶ ይቀመጥ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ኮረም ከተማ መስፋፋት ጀመረ። የኮረም ከተማ ከተስፋፋ በኋላ ሕዝቡ ገጠር (ሐያሎ) ሂደን አንቀበርም፤ስለዚህ የስላሴ ታቦት እንተክላለን በማለት የከተማ ሰዎች ተንቀሳቀሱ፡፡ በኃላም በፈቃዳችን ታቦት ከምንተክል ይልቅ ከሐያሎዎች ጋር ተስማምተን እነሱ የፈቀዱት ታቦት እንተከል በሚል ሐሳብ ተስማሙ። በዚህም ደጃች አለማየሁ፣ ፊታውራሪ አየለ አምባው (የፍርድ ቤት ዳኛ)፣ ፊታውራሪ ደጃች ንጉሴ፣ አራምሮ ቡግሳ፣ መሰለ መኮንን፣ መሰለ ታዬ፣ ከበደ በለጠ ተመርጠው ወደ ሐያሎዎች በመሄድ እናንተ ፈቅዳችሁ ታቦት ስጡን ብለው ተማጸኗቸው። ሐያሎዎችም የማርያም ጽላት እዚህ ብትሆን ትርጉም የለውም እና ወደ ከተማ ትሂድ፣ ጊዮርጊስ ግን እዚህ ይቅር በማለት የእመቤታችን ታቦት እንዲወስዱ ፈቀዱላቸው፡፡ የማርያም ጽላት ጥቅምት 14 ቀን 1947 ዓ.ም ከዓዲ ጠሸነ ከተማ ተተከለች፡፡

ይህች ቤተክርስቲያን በድንግል መነኩሴ ብቻ እንድትተዳደር የተፈቀደ በመሆኑ ባለ ህግ ካህን አያስተዳድራትም፡፡ አንድ ወቅት አለቃ ስመኝ፣ አለቃ ወጋሕታ፣ አለቃ አብርሃ፣ አለቃ ረዳ ቤተ ክርስትያኗን ለማስተዳደር ሲነሱ ግራዝማች ከልካይ ይህች ቤተ ክርስቲያን በድንግል መነኩሴ የምትተዳደር በመሆኗ እናንተ ማስተዳደር አትችሉም በማለት ከልክለዋቸዋል፡፡ በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ በድንግል መነኩሴ ደብር አለቃነት ፣ በአንድ ቄሰ ገበዝ፣ በአንድ ሰበካ ጉባኤ የምትተዳደር ደብር ናት፡፡ ይህች ደብር በአሁኑ ወቅት ከ70 በላይ ካህናትና 3 አብያተ ክርስቲናት ማለትም የመድኃኔ ዓለም፣ የአቡነ አረጋዊ እና የጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያናት በስሯ ታስተዳድራለች፡፡ እነዚህም አብያተ ክርስቲናት በአንድ ሰበካ ጉባኤ ስር በመሆን የሚቀደሱና የሚወደሱ ናቸው፡፡( አሰፋ ብርሃኑ፣ ወንጌሉ ዘወርቅ የካቲት 19,19890 ፣ ከአቶ አየለ ከልካይ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 15/09/2003)፡፡

## 4. የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በኮረም

ጥናቱ የተከናወነው በኮረም በሚገኙ የሐያሎ ማርያም እና የቅዱስ ጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያናት ነው፡፡ በመሆኑ በአብያተ ክርስቲያናቱ የተከናወነው የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ቅደም ተከተላዊ ገለጻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1. የበዓለ ትንሣኤ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ

የትንሣኤ ክብረ በዓል ለማክበር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሥርዓቶች ይከናወናሉ፡፡ በዚህ ክፍል ከዋዜማው (11 ሰዓት) ጀምሮ እስከ ሌሊቱ 9 ሰዓት የተከናወነውን ሥርዓተ ማኅሌት እንቃኛለን፡፡

#### 4.1.1. የትንሣኤ ዋዜማ ክዋኔ

የትንሣኤ ዋዜማ የተጀመረው ቅዳሜ ማታ ከምሽቱ 11 ሰዓት ሲሆን ሥርዓቱም ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ተከናውኗል፡፡

ካህናቱ አራቱ ወንጌላት (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሐንስ) በቅደም ተከተል አነበቡ፡፡ ከዚያም መዝሙረ ዳዊት ተጸለየ፡፡ በመቀጠልም ውዳሴ ማርያም በህብረት ጸለዩ፡፡ካህናቱ ሐይማኖታዊ ሥርዓቱን ሲያከናውኑ ምዕመናን በጽሞና ይከታተሉ ነበር፡፡ በመቀጠል ካህኑ የዮሐንስ ራዕይ አነበቡ፡፡ ከዚያም ላሀ ማርያም ከግብረ ሕማማት ተነበበ፡፡ በመቀጠልም አምስቱ አዕማደ ምስጢር ለህዝበ ክርስቲያን ተነገሩ፡ ፡ በዚህ ሁኔታ ሥርዓተ ዋዜማው ተጠናቀቀ፡

#### 4.1.2. የሌሊት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ

የተጋብኦ ደወል ከምሽቱ 1 ሰዓት ተደወለ፡፡ ካህኑ አቡነ ዘበሰማያት ጸለዩ፡፡ ከዚያም ጸሎተ ሐይማኖት ተደገመ፡፡ ከዚያም ካህኑ ጸሎተ አኩቴት "እስርቆት"፣ በእንተ ሰላም፣ በእንተ ማኅበር፣ በእንተ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ በእንተ እለ ያበውዑ(መባ ስላቀረቡ ሰዎች) ጸለዩ፡፡ በመቀጠልም እግዚኦ መሃረነ ("ኑዛዜ") ተሰጠ፡፡ በመቀጠልም መሪው "ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ማርያም እምነ ናስተበቁዓኪ" ብሎ አዜመ፡፡ ከዚያም ካህናቱ "እምዓርቄ ነዓዊ" ብለው በህብረት አዜሙ፡፡ በመቀጠል "ተፈስሒ ማርያም" በሕብረት ተዜመ፡፡ በመቀጠል መሪው "ተሰመይኪ ፍቅርተ" ብሎ በዜማ መራ፡፡ ካህናቱም ተቀብለው "ወበእንተዚ ናዓብየኪ ኩልነ" ብለው በህብረት ዘለቁት፡፡

ከዚያም ተመሪው "ታቦት" ብሎ እስከ መጨረሻው ዘለቀ፡፡ ካህናቱም "መቅደስ" ብለው ጀምረው እስከ "በትረ አሮን" የየራሳቸው አዜሙ፡፡ ከዚያም መሪው "ለኪ ይደሉ" ብሎ በዜማ ዘለቀ፡፡ ካህናቱ "ወበእንተዝ"ን በህብረት ዘመሙ፡፡ ከዚያም "ጸሎታ ለማርያም ወስእለታ ያድህነነ እመዓተ ወልዳ" ከተባለ በኋላ እስከ "ጸሎታ ለማርያም ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ" በህብረት ተዘመመ፡፡ ከዚያም ተአምረ ማርያምና ተአምረ ኢየሱስ በቀሳውስቱ ተነበበ፡፡ በመቀጠልም ዲያቆኑ ከመዝሙረ ዳዊት "ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመዘንቃህ እምንዋም ወከመ ኃያል ወኅዳገ

ወይን ወቀተሎ ጸሮ በድኅሬሁ" (እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ የወይን ስካርም እንደተወው ጀግና ተነሣ! ጠላቱንም አሳድዶ ደመሰሰው) መዝ 77÷25 የሚል ምስባክ ሰበከ። ካህኑ ወንጌል ቅዱስ ዘዜነው ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር ካሉ በኋላ ማቴ 28÷1-19 ፣ ማር16÷ 1-20 ሉቃ 24÷1-12 ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦችን አነበቡ።

ከዚያም መሪጌታው ከዲያቆኑ መስቀል ተቀብለው "ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ዜማ ግበሩ በዓለ በትፍስሕት እስከ አቅርንቲሁ ለምስዋዕ" በማለት አርያሙን መሩ። ካህናቱም ተቀብለው ዘለቁት። በመቀጠልም "ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ ክርስቶስ እሙታን ቀደሳ ወአክበራ እምኩሎን መዋዕል ዓልዓላ አማን ተንሥአ እምነ ሙታን"። (ዛሬ በዚህች ሰንበተ ክርስቲያን ደስታ ሆነ፣ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነስቷልና እርሷንም ከዕለታት ሁሉ ይልቅ ቀደሳት! አከበራትም! ከፍ ከፍ አደረጋት! አዎን በእውነት ከሙታን ተለይቶ ተነሳ! ብሎ መራ። ተመሪው ከመሪው ተቀብሎ ዮም ፍሥሐ ኮነ አለ። ከዚያም ቀለሙ በግራና በቀኝ ተነሳ። ከዚያ በህብረት ተዘመመ። ከዚያም ወደ ጽፋቱ ገቡ። ጽፋቱ ካለቀ በኋላ የምልጣኑ አንሺ በቁም ጸንጽለው "ትንሣኤከ ለእለ አመነ ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ" (ትንሣኤህን ለአመነ ለእኛ ብርሃንህን ላክልን) የሚለው ወረብ ወረቡ። በመቀጠል መረግዱ አመርግደው ወደ ጽፋቱ ገቡ።

ማኅሌታውያን መዘምራን ወረቡ በጸናጽልና በከበሮ አጅበው ሁሉም ክርስቲያኖች የጧፍ መብራት ይዘው እያጨበጨቡና እልል እያሉ 3ት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዑደት አደረጉ ። ዑደቱ ካለቀ በኋላ እስመ ለዓለሙ ተጸፋ።

ቀጥሎም "ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ይእቲ ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ" (ይህች እናታችን ማርያም ናት፤ የጌታችንም እናት ናት) የሚለው የአቋቋም ሂደቱን ጠብቆ ተከናወነ። ከዚያም "ሥርዓ ለነ ሰንበተ ለእረፍተ ዚአነ ፍስሐ ወሰላም ለእለ አመነ" (ዕለተ ሰንበትን ለዕረፍት አዘጋጀልን፤ ለእኛ ለምናምነውም ደስታና ሰላም ሰጠን) የሚል ወረብ ተወረበ። ወረቡ የአቋቋም ሂደቱን ተከትሎ ከተከናወነ በኋላ ወደ ኪዳን ገቡ። ኪዳኑ ካበቃ በኋላ ቄሱ መስቀል ይዞው ልብሰ ተክህኖአቸውን እንደለበሰ "**ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን አሉ።** ከዚያም ካህናቱና ምዕመናኑ የመቅደስ መስቀሉን እየተሳለሙ በቃል ወደሚለዋወጡት የምስራች አዋጅ ቀጠሉ።

| **በግዕዝ** | **በአማርኛ** |
| --- | --- |
| ካህን፡- ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን | ካህን፡- ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ነሳ |

| | |
|---|---|
| ምዕመናን፡- በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን | ምዕመናን፡- በታላቅ ኃይልና ስልጣን |
| ካህን፡- ዐሰሮ ለሰይጣን | ካህን፡- ሰይጣንን አሰረው |
| ምዕመን፡- አግአዞ ለአዳም | ምዕመናን፡- አዳምን ልጅ ነጻ አወጣው |
| ካህን፡- ሰላም | ካህን ፡- ሰላም |
| ካህን፡- እምይእዜሰ | ካህን፡- ከዛሬ ጀምሮ |
| ምዕመናን፡- ኮነ ፍስሐ ወሰላም | ምዕመናን፡- ደስታና ሰላም ሆነ |

በመቀጠልም መሪው "እግዚኦ ጸወነ ኮንከነ"ን መራ፡፡ አንሺ ስላለው ቀለሙ በግራና በቀኝ እየተነሳ የአቋቋም ሥርዓቱን ጠብቆ ተከናወነ፡፡ ከዚያም መሪው "ሃሌ ሉያ ይትፌሣሕ ሰማይ" ብሎ መዝሙሩን መራ፡፡ የተመራው መዝሙር የአቋቋም ሥርዓቱን ጠብቆ ከተከናወነ በኋላ "ሰላም" ተጸፍቶ ቅዳሴ ተገባ፡፡ ስርዓተ ቅዳሴው ከተከናወነ በኋላ መሪጌታው የዕለቱ ዝማሬ "በግዕ ንጹሕ ተጠብሐ" ብሎ አዜመ፡፡ በመቀጠል መሪጌታው የዕጣነ ሞገር ቅኔ ተቀኙ፡፡ ቅኔው ከተሸበሸበና ከተዘመረ በኋላ ዲያቆኑ "ነአኩቶ" ብሎ አዜመ፡፡ ካህናቱም በቤተ-መቅደስ በር ቆመው እያሉ ውዳሴ ማርያም በአንድ ካህን ታደለ፡፡ ከዚያም አቡነ ዘበሰማያት ተብሎ የማሳሪጊያ ጸሎት ተጸለየ፡፡ ከዚያም ሠርሖተ ህዝብ ሆነ፡፡ ሁሉም ክርስቲያኖች እንኳን ለበዓለ ፋሲካ (ትንሣኤ) አደረሰህ! አደረሰሽ! እየተባባሉ ወደየቤታቸው ሄዱ፡፡ በዚህ ሁኔታ የበዓለ ትንሣኤ ሥርዓተ ማኅሌት ተከናወነ፡፡



የኮረም ሐያሎ ማርያም ቤተ ክርስቲያን



በኮረም ሐያሎ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንቱ ሥርዓተማኅሌት ሲያከናውኑ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

## 4.2. የሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ

የሚያዚያ ጊዮርጊስ ክብረ በዓል ለማክበር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዋዜማው የተለያዩ ሐይማኖታዊ ተግባራት ተከናውነዋል። በመሆኑ ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ንግስ ድረስ የተከናወኑት የሥርዓተማኅሌትተግባራት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.2.1. የዋዜማው ክዋኔ

በዋዜማው ዕለት የሚያዚያ ጊዮርጊስ በዓል ለማክበር ካህናቱና ህዝበ ክርስቲያኑ በቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ተሰበሰቡ። ልክ ከቀኑ 8፡10 ሲሆን የተ.ጋብኦ ደውል ተደወለ።ካህናቱና ህዝበ ክርስቲያኑም ቦታ ቦታቸውን ያዙ። በመቀጠል ካህኑ በስመ አብ ብለው ጸሎት አደረሱ።

ከዚያ በመቀጠል ቅዱስ ያሬድ የደረሰው "አንቀጸ ብርሃን" የሚባለው የማርያም ምስጋና ተደገመ። ከዚያም ካህኑ ቅዱስ ብለው በአራራይ ዜማ ኪዳኑን አስጀመሩ። ካህናቱና ህዝበ ክርስቲያኑም ከካህኑ ተቀብለው "ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ሐያል ቅዱስ ሕያው ዘኢ.ይመውት" በማለት በህብረት አዜሙ።

የኪዳኑ ጸሎት እንዳበቃ መሪጌታው "ዝንቱስ ብእሲ መስተጋድል ኮከበ ክብር ዘዓቢየ ኃይለ ይገብር" ብለው ዋዜማውን ቃኙ። የተቃኘው ዋዜማ በአንድ መሪ ተመራ። በመቀጠልም ምልጣኑን መሪና ተመሪው አመለጠኑት። አንሺዎች ማንሻውን በግራና በቀኝ አነሱ። ከዚያ ዋዜማው በቁም ተባለ። ተመሪው ተቀብሎ ምልጣኑ ተጸፋ። ከዚያ በመቀጠል ካህኑ መስተበቁዕ (ልመና፣ጸሎት) በእንተ እለይነግዱ (መንገድ ስለሄዱ ሰዎች) አሉ። ከዚያም

"ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ" (ምድር ሁሉ የእግዚአብሔር ናት) መዝ 23÷1 ተመራ፡ ፡ አንሺዎች ቀለሙን አነሱ። ከዚያም መዘምራኑ በዜማ እንደዘለቁት ወድያውኑ የሰማዕቱ ክብር የሚያሞግስ "ዋዜማ" ተቀኘ። የአቋቋም ሂደቱን ጠብቆ ተከናወነ። በመቀጠል ካህኑ (ቄሱ) መስተበቁዕ (ልመና፣ ጸሎት) በእንተ ዝናማት (ስለዝናም መዝነብ ፀሎት) አደረሱ፡ ፡ ከዚያ መሪው "እግዚአብሔር ነግሠ ስብሐቲሁ ለብሰ" (መዝ 92 140፣፣1) (እግዚአብሔር ነገሰ ምስጋናም ለበሰ) የሚለው "ምዕራፍ" ከተሰኘው የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በዜማ አዜሙ። ከዚያም ሁለተኛ ዋዜማ ቅኔ ተደረገ። ቅኔውም የአቋቋም ሂደቱን ጠብቆ ከተከናወነ በኋላ ካህኑ መስተበቁዕ (ልመና፣ ጸሎት) በእንተ ንጉሥን ጸለዩ። ከዚያ

በመቀጠል "እግዚኦ ጸራኅኩ ኃቤከ" (አቤቱ ወደ አንተ ጮህኩ) መዝተመራ። ምርሐቱ በዜማ ከተዘለቀ በኋላ ሦስተኛ ዋዜማ ተባለ።

ሶስተኛ ዋዜማ የአቋቋም ሂደቱን ጠብቆ ተከናወነ። ከዚያ በመቀጠል ካህኑ (ቄሱ) ሊጦን ዘሰርክ (የማታ ምስጋና) "አምላክነ ዘዴበ ኪሩቤል ትነብር" (በኪሩቤል ላይ አድረህ የምትኖር አምላካችን) የሚለው ምስጋና በዜማ አደረሱ። ከዚያ በመቀጠል ስላሴ ቅኔ ደረሰ። ዲያቆኑ ሃሌ ሉያ ብሎ ምስባክ ሰበከ። ካህኑም ጸጋሁ ለእግዚአብሔር የሐሉ ምስሌክሙ ብለው ኪዳን አደረሱ። ከዚያ በኋላ ሥርዓተ ማኅሌቱ "ሰላም" ተጸፍቶ ተጠናቀቀ። ከዚያ ውዳሴ ማርያም ተጸለየ። በዚህ ሁኔታ ስርዓተ ዋዜማው ከተጠናቀቀ በኋላ ካህናቱ ወደተዘጋጀው ምርፋቅ ሂዱ።

### 4.2.2. ድህረ ዋዜማ (የሌሊት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ)

ካህናቱ የዋዜማ ስርዓት አልቆ መጠነኛ እረፍት ካደረጉ በኋላ የተጋብኦ ደወል ተደወለ። የተጋብኦ ደውል የተደወለው ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ሲሆን ካህናቱም በቅኔ ማሕሌቱ ቦታ ቦታቸውን በመያዝ ቆሙ። ከዚያ መቋሚያ ታደለ። በመቀጠል ቄሱ አስርቆት አደረሱ። በመሪውን ወገን "ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሰዓል በእንቲአነ ወቅዱስ ገብርኤል አዕርግ ጸሎተነ" (የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለኛ ለምን ቅዱስ ገብርኤልም ጸሎችንን አሳርግልን) የሚለው መቅድመ ማሕሌት በግራና በቀኝ በመቀባበል በዜማ ተዜመ። ከዚያም መረጌታው "ሰምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ወይብፃሕ ቅድሜከ ገዐርየ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ወኢትሚጥ ገጸከ እምነየ" (አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ ቅድመ ዓለም የነበርክ አሁንም ያለህ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖርና ጩኸቴ በፊትህ ይድረስ ፊትህም ከእኔ አትመለስ) መዝ 101÷1 የሚለው ከዳዊት መዝሙር የተወሰደው ቀለም በመርጌታው ተመራ። በመቀጠል ተመሪና አንሺ ስላለው ማሕሌታውያኑ በግራና በቀኝ በቁም ዜማ በህብረት በመቀባበል አዜሙት። ከዚያ በመቀጠል "ስቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኩሎ ዓለመ በአሐቲ ቃል" (በአንዲት ቃል ዓለምን ሁሉ የፈጠረ ፈፅሞ የተመሰገነ ነው) የሚለው ዜማ በቁም ተጸነጸለ።

ከዚያ ካህናቱ ዳዊት ነቢይ በከመ ጸለየ ብለው "ነግሡን" ቀጠሉ። ከነግሡ "ሰላም ለኩልያቲክሙ እለ እሩያን በአካል" የሚለው ተጸነጸለ። በመቀጠል ካህናቱ ሰላም ለክሙ ሚካኤል ወገብርኤል ሱራፌል ወኪሩቤል ብለው በዜማ አዜሙ። ከዚያም ሰላም ለዝክረ ስምኪ ዘመንክር ጣዕሙ ተጸነጸለ። ከዚያ የዕለቱን ነግሥ "በሰፈልያ ወበመዝረብ አዕጽምቲከ ሰቡር" የሚለው የቅዱስ ጊዮርጊስ ነግሥ ተጸነጸለ። ከዚያ በመቀጠል ለእለቱ የተመረጡ መልኮች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ተጸኔለ። መርጌታው ሃሌ ሉያ ብሎ

አንገርጋሪው መራ፡፡ ከዚያ በመቀጠል "ይእቲ ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ" የሚለው መዝሙር ልክ እንደ ትንሣኤው የአቋቋም ሂደቱን ጠብቆ ተዘመረ፡፡ ከዚያ "ሰላም" ተጸፋ፡፡ ከዚያ ካህናቱ ልክ እንደትንሣኤ ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ብለው እያወጁ ቅዳሴ ገቡ፡፡ ከዚያ ዲያቆኑ ምስባክ ሰበከ፡፡ ካህኑም ዕለቱን የሚመለከት ወንጌል አነበቡ፡፡ ዲያቆኑ ጸልዩ ካለ በኃላ ክብር ይእቲ ተባለ፡፡ ከዚያ ስብሐዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ እስከ መጨረሻው ተከናወነ፡፡ ከዚያ "ዕጣነ ሞገር" ደረሰ፡፡

### 4.2.3. የዓውደ ምህረት ክዋኔ

ቅዳሴ ካበቃ በኋላ ታቦቱ በመዘምራን፣ ካህናት፣ ዲያቆናትና ሰንበት ተማሪዎች ታጅቦ ወደ ዓውደ ምህረቱ ወጣ፡፡ ከዚያ ሊቃውንቱ "አቡን" አዜሙ፡፡ታቦቱ በዓውደ ምህረቱ እንደቆመ መዘምራንና ካህናት " ጸለየ ጊዮርጊስ" የሚለውን ወረብ ወረቡ፡፡ ተሸበሸበ፡፡ ከዚያ በመቀጠል የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች "ደም ወሐሊብ እምነ ክሳዱ ፈልፈለ" የሚለውን ወረብ አስረገጡ፡፡ ወረቡ ከተዘመረ በኋላ "በነገስታትህ ፊት እመሰክራለሁ" በሚል ርዕስ ለ30 ደቂቃ በመምህር ዮሐንስ ግርማይ ትምህርት ተሰጠ፡፡ ትምህርቱ ካለቀ በኋላ 3ት ጊዜ ዑደት ተደርጎ ታቦተ ህጉ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ፡፡ ከዚያ ሊቃውንቱ ወደ ደጀ ሰላም፣ ምዕመናኑ ወደ ተዘጋጀው ጸበል ጸዲቅ ሄዱ፡፡

የከተማው ህዝበ ክርስቲያን ጸበል ጸዲቁን ከቀመሱ በኃላ ወደየቤታቸው ሄዱ፡፡ የአከባቢው(የገጠሩ) ክርስቲያኖች ወደየሰንበቴያቸው ሄዱ፡፡ የሰንበቴው ፕሮግራም ካለቀ በኋላ ሁሉም ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ተጠናቀቀ፡፡



የኮረም ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን



በኮረም ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንቱ ስርዓተ ማኅሌቱን ሲያከናውኑ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

## 5. የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ፣ ደረጃዎች፣ የንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና፤ተግባራት ትንተና

### 5.1 የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ባህርያት

ሥርዓተ ማኅሌት እንደ አንድ የስነ ጥበብ ዘርፍ የራሱ የሆነ ክዋኔ እንዳለውና ክዋኔው በአብያተ ክርስቲያናት ሊከወን እንደሚችል በ 4.1 እና 4.2 ተገልጿል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔን ፎክሎራዊ ባህርያት እንመለከታለን፡፡

ማኅሌት የራሱ የአከዋወን ስርዓት እና ባህርያት አሉት፡፡ ክዋኔው እና ባሕርያቱ ደግሞ ፎክሎራዊ ገጽታ ይንጸባረቅባቸዋል።

የፎክሎር የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ (Performance Theory) ሲጠና፡- የመከወኛ ጊዜ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ አውድ፣ ድርሰት፣ የክዋኔ መሪዎች፣ የክዋኔ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልጉ በምዕራፍ ሁለት 2.2.7.2 ላይ አመልክተናል፡፡ በዚህ ክፍል እነዚህ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ባሕርያት ከመስክ (Field) ከተገኙት መረጃዎች በመነሳት እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

#### 5.1.1 የሥርዓተ ማኅሌት የመከወኛ ጊዜ

ሥርዓተ ማኅሌት በቤተ ክርስቲያን ፣በቅኔ ማሕሌት ውስጥ፣ በንግስ ጊዜ(በዓውደ ምህረት) ከቤተክርስቲያን ውጪ በከተራ (በበዓለ ጥምቀት) በሜዳ ላይ ይከወናል፡፡ ክዋኔው በጊዜና በቦታ የተወሰነ ነው፡፡በመሆኑም በዘፈቀደ ሊከወን አይችልም፡፡

ስለ ሥርዓተ ማኅሌት የመከወኛ ጊዜና ቦታ መምህር ዮሐንስ ግርማይ የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል፡፡

> *ሥርዓተ ማኅሌት በዋናነት በሶስት ይመደባል፡፡ ከእነዚህ ሶስት ዓይነት የአገልግሎት ሥርዓቶች አይወጣም። እነዚህም የእሁድ(ሰንበት) ሥርዓተ ማኅሌት፣ የክብረ በዓል (የዓመት ንግስ) እና የወርኃ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት ናቸው፡፡ ሥርዓተ ማኅሌት ከእነዚህ ባይወጣም በዓመት አንድ ጊዜ ከቤተክርስቲያን ውጭ በሜዳ ላይ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው በከተራ ወይም በጥምቀት በዓል ብቻ ነው፡፡ በእሁድ (ሰንበት) የሚቆመው መዝሙር ሲሆን በወርኃ በዓል ደግሞ የወሩን በዓል ማለት በወሩ የሚከበረው ሰማዕት፣ ጻድቅ መልአክ መሰረት በማድረግ ነው። በወርኃ በዓል ሊቃውንት እየፈጠሩ ካልሆነ በቀር የወንበር ወረብ የለውም፡፡ ክብረ በዓል ግን የራሱ የሆኑ ወረቦች አሉ፡፡ እንግዲህ እንደ ዓይነታቸው የአገልግሎታው ደረጃ እና የመቅረብያ ምክንያታቸው ይለያያል፡፡ ለምሳሌ፡- የትንሳኤ ክብረ በዓል ብንወስድ ከሁሉም ይለያል፡፡ ሌላው ክብረ በዓል ዑደቱ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ነው። ትንሳኤ ግን ዑደቱ በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ (ሚያዚያ17/09/ 2003÷ካሴት ቁጥር 5÷side 1) ፡፡*

❖ በጥናቱ ጽሑፍ ውስጥ "ካሴት ቁጥር" እየተባለ የተጠቀሰው የቴፕ ካሴት ነው፡፡

የሥርዓት ማኅሌት የመከወኛ ምክንያትና የመከወኛ ጊዜያት የተለያዩ ናቸው፡፡ እንደመከወኛ ጊዜያቱ ይዘቱም የተለያየ ነው፡፡ የበዓለ ትንሳኤ ሥርዓተ ማኅሌት ዋናው ይዘቱ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ማብሰር ነው፡፡ በመሆኑም ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ሌሊቱ የሚቆመው ስርዓተ ማሕሌት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን መነሳቱ በማሰብ ሲሆን የሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት ደግሞ የቅዱስ ጊዮርጊስ መከራና ስቃይ፣ያሳለፋቸውና የፈጸማቸው የሰማዕትነት ተጋድሎዎች እንዲሁም የተቀበለው የክብር(የድል) አክሊል የሚያስታውሰ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌት የራሱ የሆነ የመከወኛ ምክንያት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

አዋኚው ሥርዓተ ማኅሌት የራሱ የመከወኛ ምክንያት እንዳለው በበዓለ ትንሣኤ እና በሚያዚያ ጊዮርጊስ በአካል በመገኘት ማስተዋል ችሏል፡፡



የበዓለ ትንሳኤ ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ



የሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

### 5.1.2 የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኝ

በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኝ የሚባለው ሥርዓተ ክዋኔን የሚተገብር ነው፡፡በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ሥርዓቱን የሚመሩ፣የሚዘምሩ፣ የሚያከናውኑ በአጠቃላይ ማኅሌታውያን የሚባሉ ቢሆኑም ድርሻቸው የተለያየ ነው፡፡ የማኅሌታውያንን ድርሻ መምህር ዳንኤል አየነው እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

ዋናው የሥርዓተ ማኅሌት መሪ መሪጌታ ይባላል። ከዚያም በቀኝ በኩል ቀለሙን የሚያነሳ ቀኝ ጌታ፣ በግራ በኩል ቀለሙን የሚያነሳ ደግሞ ግራ ጌታ ይባላል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌትም አላቸው። መሪጌታው በዕለተ ዓርብ የተሰቀለው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ቀኝ ጌታ በቀኝ በኩል የተሰቀለው (ጥጦስ) ምሳሌ ነው። ግራ ጌታው ደግሞ በግራ በኩል የተሰቀለው (ዳክረስ) ምሳሌ ነው። ስለዚህ መሪጌታው፣ ግራ ጌታው እና ቀኝ ጌታው በስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ድርሻቸው የተለየ ነው። (ሚ.ያዚ.ያ 18/09/ 2003÷ካሴት ቁጥር 7÷side 2)

በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት መሪጌታው በቅኔ ማኅሌቱ መሐል በመሆን የዕለቱን ቀለም የሚመራ ሲሆን የተመራውን ቀለም ደግሞ በቀኝ በኩል ያለው ቀኝ ጌታ ያነሳዋል። ከዚያም በግራ በኩል ያለው ግራ ጌታ ቀለሙን ያነሳል። በመጨረሻ ሁሉም መዘምራን በህብረት ዜማውን ያዜማሉ። ለምሳሌ፡- በበዓለ ትንሣኤ በተቆመው ሥርዓተ ማኅሌት "ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ ክርስቶስ እሙታን ቀደሳ ወአክበራ እምኩሎን መዋዕል ዓልዓላ አማን ተንሥአ እምነ ሙታን" (ዛሬ በዚህች ሰንበተ ክርስቲያን ደስታ ሆነ። ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነስቷልና። እርሷንም ከዕለታት ሁሉ ይልቅ ቀደሳት፣ አከበራትም፣ ከፍ ከፍ አደረጋት፣ አዎን በእውነት ከሙታን ተለይቶ ተነሳ) በማለት መሪው መሪጌታ የመራ ሲሆን ይህንን ከመሪው ተቀብለው ቀኝ ጌታ እና ግራ ጌታ ቀለሙን አንስተዋል። ከዚያ በኋላ መዘምራኑ በህብረት በመሆን "ዮም ፍስሐ ኮነ" በማለት ሙሉውን ወረብ ወርበውታል። ስለዚህ በሥርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ሁሉም የየራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የመሪጌታው ድርሻ የጎላ የሚሆነው ድጓውን በደንብ ጠንቅቆ ስለሚያውቅና የሙያው ባለቤት በመሆኑ ነው።

በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት መሪጌታ፣ቀኝ ጌታ፣ እና ግራ ጌታ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ አብዛኞዎቹ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች የተስማሙባቸው ቢሆኑም ተምሳሌታቸው ግን ከአንዱ መምህር ወደ ሌላው መምህር መጠነኛ ልዩነት አለው።

በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት የመምህራን ድርሻ የጎላ የሚሆነው የተሳሳተውን ስለሚያርሙ እና የገደለውን ስለሚያስተካክሉ ነው።



መምህር ዳንኤል አየነው በበዓለ ትንሳኤ ስርዓተ ማህሌቱን ሲመሩ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

በአጠቃላይ ከጽሑፉ የተገኙ መረጃዎች ሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በሥርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ጊዜ ድርሻ ያላቸው አካላት መሪጌታ፣ ቀኝ ጌታ፣ ግራ ጌታ እና መዘምራን ቢሆኑም በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተግባራዊ የሚሆነው ግን ሥርዓተ ማኅሌቱ በመሪጌታው ሲመራ ነው፡፡ በመሆኑም በስርዓተ ማሕሌት ዋነኛ ከዋኝ (Performer) ተደርጎ የሚወሰደው መሪጌታው ነው፡፡ መሪጌታው ሥርዓተ ማኅሌቱን የሚመራው በድጓው የተጻፈውን ቀለም መሰረት በማድረግ ሲሆን ከበዓሉ በፊት የዕለቱን ቀለም በማውጣት ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በማሕሌት ክዋኔ የመሪጌታው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

5.1.3 የሥርዓተ ማኅሌት ታዳምያን

በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ታዳሚያን የሚባሉት ህዝበ ክርስቲያን ሲሆኑ መሰረታዊ የሥርዓቱ ማኅሌት እውቀት ባይኖራቸውም የሃይማኖቱ ተከታዮች በመሆናቸው ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ምዕመናን በክብረ በዓል፣ በወርኃ በዓልና በእሁድ በቤተክርስቲያን የሥርዓተ ማኅሌት ተሳታፊ ቢሆኑም ዋናው ጎልቶ የሚታይ ድርሻቸው ግን የግል ጸሎት መጸለይ ነው፡፡

መምህር ብርሃነ ሕይወት በጽሐ የምእመናን ተሳትፎ በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

> *"ሊቃውንቱ ስርዓተ ማሕሌቱን ሲቆሙ አንክሮ ያደርጋሉ፣ በወረብ ጊዜ ደግሞ በተለይ እናቶች በእልልታና በጭብጨባ ያጅባሉ፡፡ በእርግጥ በወረብ ጊዜ ያለ እናቶች እልልታና ጭብጨባ ማሕሌት አይደምቅም"( 20/09/2003÷ካሴት ቁጥር 4÷side 1)፡፡*

በተመሳሳይ መልኩ መምህር ዳንኤል አየነው የምዕመናንን ድርሻ በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል።

*ምዕመናን የሐይማኖት ዜግነት ስላላቸው ዜግነታቸው መሰረት በማድረግ በእልልታና በጭብጨባ ያመሰግናሉ፡፡ አይደለም በስርዓተ ማሕሌት አገልግሎት እልል ያለ፣ የዘመረ ይቅርና፣ በጥምቀት ጊዜ የዘፈነ እንኳ ዋጋ አለው፣ ማሕሌተ ስጋዊ ነውና፡፡ ምዕመናን የሐይማኖት ዜግነት ስላላቸው ቁጥራቸው ከካህናት ተርታ ነው፡፡ ጌታም እኮ! በመዋዕለ ስብከቱ ሐዋርያት፣ አርድእት እና ቅዱሳት አንእስት አለየም፡፡ ከሁሉም ወገን የራሱ ቤተሰብ አደረጋቸው እንጂ ስለዚህ ምዕመናንም ባላቸው ችሎታ እንዲያመሰግኑ ቤተ ክርስቲያን ታዛለች (ሚየያዚያ 18/09/ 2003÷ካሴት ቁጥር 7÷side 2) ፡፡*

በበዓለ ትንሳኤ እና በሚያዚያ ጊዮርጊስ በተደረገው ምልከታ የምዕመናን ድርሻ የግል ጸሎት መጸለይ፣ እልል ማለትና ማጨብጨብ እንዲሁም በስርዓተ ክዋኔው አንክሮ ማድረግ እንደሆነ አጥኚው ማስተዋል ችሏል፡፡ በፎክሎር ስርዓተ ክዋኔ እያንዳንዱ ቅንጣት ተሳትፎ ዋጋ አላት፡፡ በመሆኑም በስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ የምዕመናን ድርሻ የጎላ ነው ባይባልም የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እንዳለ ግን በነበረው የበዓለ ትንሳኤ እና የሚያዝያ ጊዮርጊስ የክብረ በዓል ስርዓተ ማህሌት ተስተውሏል፡፡

“እልልታ ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ ቅዱስ ዳዊት እልልታ የሚያውቅ ህዝብ ምስጉን ነው ብሏልና፣ ስለዚህ የምዕመናን እልልታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ መሰረት ያለው ነው”፡፡መዝ 77÷20

በአጠቃላይ ከጽሑፉም ሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች መረዳት የሚቻለው ምዕመናን በስርዓተ ማሕሌት የተወሰነ ድርሻ ቢኖራቸውም ድርሻቸው ግን የፈቃድ እንጂ የግዴታ አለመሆኑን ነው፡፡



የስርዓተ ማሕሌት ታዳምያን ሕዝበ ክርስቲያን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

### 5.1.4 የሥርዓተ ማኀሌት አውድ

አውድ አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን የክዋኔው ጊዜና ቦታ (መቼት)፣ የአከዋወኑ ሂደት (Process)፣ የክዋኔው ድባብ፣ ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እንደሚያጠቃልል በምዕራፍ ሁለት 2.2.7.2.4 ባለው ርዕስ ስር አመልክተናል፡፡ የፎክሎር ምሁራን አውድን ተጨባጭና ማህበራዊ በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡

### I.የሥርዓተ ማኅሌት ተጨባጭ አውድ

ሥርዓተ ማኅሌት የሚከወንበት የራሱ የሆነ አውድ አለው ሲባል ተጨባጭ አውዱን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በመሆኑም ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ተጨባጭ አውድ የሚባለው ስርዓተ ማሕሌቱ የሚከወንበትን ቤተክርስቲያን፣ ለሥርዓተ ማኅሌቱ ክዋኔ የሚውሉ ንዋያተ ማሕሌት (ከበሮ፣መቋሚያ፣ ጸናጽል) እንዲሁም ካህናቱና ህዝበ ክርስቲያኑ በወረቡ ጊዜ የሚያሳዩትን መንፈሳዊ ዝማሜ የሚያጠቃልል ነው፡፡

በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በተጨባጭ የምናስተውላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ይህንን አስመልክተው መልአከ ሕይወት አበራ አወቀ የሚከተለውን ሃሳብ አብራርተዋል። ሥርዓተ ማኅሌት የሚከናወነው ከከተራ በዓል (ጥምቀት) በቀር በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ ለዚህ ክዋኔ የሚያስፈልጉ ንዋያተ ማኅሌት (መቋሚያ፣ ጸናጽል፣ ከበሮ፣ ድጓ፣ ፆመድጓ፣ዝማሬ መዋስዕት፣ካባ፣ ጥንግ ድርብ ናቸው። እነዚህም በተጨባጭ በአይናችን የምናስተውላቸው ናቸው(ሚያዝያ 21/09/ 2003÷ ካሴት ቁጥር 3÷side1) ፡፡

ከመልአከ ሕይወት አበራ ገለጻ የምንገነዘበው ለሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት በቅድሚያ የሚያስፈልጉ ድጓ፣ ከበሮ፣ መቋሚያና ጸናጽል የማይቀሩ መሆናቸውን ነው። ስለዚህ ማኅሌት ያለ ንዋያተ መዝሙር አይከናወንም፡፡ በፎክሎር ሥርዓተ ክዋኔ ሲጠና ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችም ይጠናሉ፡፡ በመሆኑም በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በተጨባጭ የምናያቸው ንዋያተ ማኅሌት፣ አገልጋይ መዘምራን እና ክዋኔውን የሚያደምቁ ምዕመናን ናቸው፡፡ እነዚህም የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ተጨባጭ አውድ የሚያመላክቱ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡



የሥርዓተ ማሕሌት ተጨባጭ አውድ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

### II.የሥርዓተ ማኅሌት ማህበራዊ አውድ

ስርዓተ ማሕሌት ሲከወን ማሕሌታውያን፣ ካህናት፣ ዲያቆናትና ህዝበ ክርስቲያን የሚሳተፉ ሲሆን እነዚህም በሐይማኖታዊ እውቀት፣ በማሕበራዊ ደረጃ፣ በሚለብሱት ልብስ፣ በጎሳ ፣በቀለም፣ በጾታ የተለያዩ ናቸው፡፡ ሁሉም አንድ የሚያደርጋቸው ለምስጋና፣ ለጸሎት ቤተክርስቲያን መገኘታቸው ነው፡፡

በስርዓተ ማሕሌት አገልግሎት ድርሻ ያላቸው አካላት በእውቀት፣ በእድሜ፣ በጾታ፣ በአስተሳሰብ ሊለያዩ እንደሚችሉ ሊቀ ትጉሃን ጸዳል ካሳው የሚከተለውን ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

> *በስርዓተ ማሕሌት ዋናው የሚመሰገነው እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔርን ለማመስገን ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡ ደግሞ ካህናት፣ መዘምራን፣ምዕመናን የተለያየ ክህሎት፣ ትምህርት፣ ሙያ፣ ስራ ያላቸው ናቸው፡፡*
> *ለምሳሌ፡- መምህራንን ብንወስድ የድጓ፣የዝማሬ መዋስዕት፣የቅኔ ፣ የአቋቋም፣ የመጻሕፍት መምህራን ይኖራሉ፡፡ እነዚህ መምህራን በቋንቋም ኦሮምኛ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ፣ ወዘተ.. ቋንቋ የሚናገሩ፣ ከቤተክርስቲያን ትምህርት በተጨማሪ በሌላ ሙያ በመምህርነት፣በግብርና፣ በህክምና የሚሰሩ ይኖራሉ፡፡ ምዕመናን ብንወስድ መምህር፣ ሐኪም፣ የግብርና ባለሙያ ወዘተ... ልዩ ልዩ ትምህርትና ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡ በእድሜ ደረጃ ብንወስድ ወጣት፣ አዋቂ፣ ሽማግሌ፣ አሮጊት ወዘተ.. ይኖራሉ፡፡ (ሚያዚያ 20/09/2003÷ካሴት ቁጥር 10÷side 2)፡፡*

ፎክሎር በዕድሜ፣ በጾታ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በጎሳ የተለያዩ ሰዎች አንድ የሚሆኑበት የጥናት መስክ ነው፡፡ በመሆኑም በስርዓተ ማሕሌት ያሉትን ልዩነቶች ማስተዋል የክዋኔውን ማህበራዊ አውድ (social context) በአግባቡ እንድንገነዘብ ያስችለናል፡፡ አጥኚው በመስክ ወቅት የስርዓተ ማሕሌት ተሳታፊዎች ከተለያየ ማሕበራዊ አውድ እንደመጡ አስተውሏል፡፡



በተለያየ ማሕበራዊ ደረጃ ያሉ የስርዓተ ማኅሌት ተሳታፊዎችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

በአጠቃላይ ከጽሑፍም ሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች የሚያመላክቱት የማሕሌት ስርዓተ ክዋኔ ተሳታፊዎች የተለያየ ማህበራዊ ዳራ ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡

### 5.1.5. የሥርዓተ ማኅሌት ድርሰት

ድርሰት የምስጋና ቃል፣ መልክ፣ ሰላምታ፣ ግጥም፣እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት በ2.2.7.2.5 ተገልጿል።

በስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ድርሰት የሚባለው እለቱን የሚመለከት ዜማ የሚዜምበት ሲሆን ይህም ድጓውንና ዚቁን መሰረት በማድረግ የሚቀርብ ነው፡፡ ስለዚህ ማሕሌታውያን በበዓለ ትንሳኤም ይሁን በሚያዝያ ጊዮርጊስ የሚቆመው ቀለም አስቀድሞው ከድጓው ይመለከታሉ፡፡ በበዓለ ትንሳኤ የተቆመው ስርዓተ ማሕሌት ለሚያዝያ ጊዮርጊስ ከተቆመው ስርዓተ ማሕሌት የተለየ ያደረገውም ድርሰቱና ይዘቱ መለያየቱ ነው፡፡

አጥኚው በበዓለ ትንሳኤ ሆነ በሚያዝያ ጊዮርጊስ ስርዓተ ማሕሌት ባደረገው ምልከታ መሪጌታው ለእለቱ የሚስማማ ቀለም ድጓውን መሰረት በማድረግ እንደሚያቀርብ አስተውሏል፡፡

የበዓለ ትንሳኤንና የሚያዝያ ጊዮርጊስን ሥርዓተ ማኅሌት ቁመት በተመለከተ መምህር ይባቤ አድሂና የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል።

> *የትንሳኤ ስርዓተ ማሕሌት ሆነ የሚያዝያ ጊዮርጊስ ስርዓተ ማሕሌት ለመቆም መሰረት የምናደርገው ድጓውን ነው፡፡ የትንሳኤ ሥርዓተ ማኅሌት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መቃብር መነሳት መሰረት በማድረግ "ክርስቶስ ተንሥአ እም ሙታን ሞተ ወኬዶ ለሞት ለእለ ውስተ መቃብር ወሀበ ሕይወተ ዘለዓለም ዕረፍተ" (ክርስቶስ ሞተ፣ሞትንም ረገጠው በመቃብር ላሉትም የዘዓለም እረፍት የሆነውን ሕይወት ሰጣቸው) እያልን እናዜማለን፡፡ የጊዮርጊስ ደግሞ "ዝንቱሰ ብእሲ መስተጋድል ኮከበ ክብር ዘዓብየ ኃይለ ይገብር" (ይህ ተጋዳይ የክብር ኮከብ ዓብይ ሐይል ያለው እና ተአምር ሰሪ ነው) የሚለውን ከድጓ እንቃኛለን፡፡ ስለዚህ የዜማው መሰረት የቅዱስ ያሬድ የድጓ ድርሰት ነው፡፡ ማንኛውም ዜማ ከቅዱስ ያሬድ ድጓ አይወጣም። (ሚያዝያ 19/09/2003÷ ካሴት ቁጥር 8÷side 1)፡፡*

ከመምህር ይባቤ መገንዘብ የሚቻለው የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የቅዱስ ያሬድ ድጓ እና ዚቅ መሰረት ተደርጎ የሚከወን ቢሆንም በየዓመቱ እና በየጊዜያቱ ግን ነባሩን ዜማ መሰረት በማድረግ የሚፈጠሩ ወረቦች መኖራቸውን ነው፡፡ በተለይ ከዜማው በኋላ እንደ ወቅቱ፣ እንደ ህዝበ ክርስቲያኑ እና ሊቃውንቱ ተሳትፎ አዳዲስ ቅኔዎች ይቀኛሉ፡፡ ቅኔዎቹ በባለሙያ የሚቀርቡ ሲሆን ቅኔውን የሚያቀርበው ባለቅኔ አዳዲስ ቃላትን፣ ሐረጋትን እና ዓረፍተ ነገሮችን ሊፈጥር ይችላል፡፡ የቅኔ ባለሙያ እና ለብዙ ዓመታት ወንበር ዘርግተው እያስተማሩ ያሉ መምህር ዮሐንስ ግርማይ በክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት የሚቀርበውን ቅኔ በተመለከተ የሚከተለውን ሐሳብ ሰጥተዋል፡፡

*ቅኔው በፈ.ቃደኝነት የሚቀርብ ሲሆን እንደየ ሊቃውንቱ እውቀት፣ ክህሎት እና ሙያ አቀራረቡም ይለያያል። በእርግጥ የራሱ የሆነ የአቀናኛት ስልት እንዳለው እና ከመሰረታዊው የቅኔ ስልት እንደማይወጣ ሁሉም መምህራን ይገነዘቡታል። ይህ ማለት ግን ፈጠራ አይታከልበትም ማለት አይደለም።ቅኔ ፈጠራ ነውና። ዜማ ከድጓ ድርሰት እንደማይወጣ ሁሉ ቅኔም ከመሰረታዊ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አይወጣም፡ ቅኔ ፈጠራ ነው የሚባለው የቃላት፣ የሐረጋት እና የዓረፍተ ነገር ልዩነት ስለሚያመጣ እንጂ መሰረታዊ ለዛው ግን አይለቅም። (ሚያዝያ 17/09/2003÷ካሴት ቁጥር 5÷side2)።*

እንደ መምህር ዮሐንስ አገላለጽ ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ድጓ መሰረታዊ መሆኑን ነው። በመሆኑም የሥርዓተ ማኅሌት መዘምራን ማኅሌትን ሲከውኑ መጠነኛ ፈጠራ ሊያደርጉ ይችላሉ እንጂ ከድጓው እና ከዚቁ ግን ሊወጡ እንደማይችሉ መገንዘብ ይቻላል። በአጠቃላይ ድጓ የተባለው የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሰረታዊ መሆኑን ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች መገንዘብ ይቻላል::

#### 5.1.6 የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሪዎች

የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ሲከወን ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ታቦተ ንግሱ ድረስ ያለው ሂደት በበላይነት የሚመሩ መምህራን አሉ። የመምህራኑ ድርሻ የዕለቱን ቀለም መምራት ብቻ ሳይሆን የተሳሳተውን ማረም፣ የጎደለውን ማስተካከል እንዲሁም ሥርዓተ ክዋኔውን በተፈቀደለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናወን ማድረግ ነው። ስለዚህ መምህራን የስርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሪዎች ናቸው። ሥርዓተ ማኅሌቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ የሚያስፈልጉ ቀለሞችን በመምረጥ፣ ወረቦችን በማዘጋጀት፣ በየመሐሉ ቅኔ የሚቀኙ መምህራንን በመጋበዝ፣ ወረብ ሲወረብ በየመሐሉ የሚያስረግጡ ካህናትን በመምረጥ ሥርዓተ ክዋኔው በሚገባ እንዲከናወን ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። መምህራን የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሪዎች ሊሆኑ የቻሉት ስርዓቱን እስከ ማስረጃው ጠንቅቀው ስለሚያውቁና በሙያ ዘርፉ በቂ እውቀት ስላላቸው ነው። ከመምህራን በተጨማሪ በስርዓተ ማኅሌት ክዋኔ "ቀኝ ጌታ"፣ "ግራ ጌታ" እንዲሁም ያላስመሰከሩ መዘምራን ሥርዓተ ማኅሌቱን በመምራትና ክዋኔውን አግባብነት እንዲኖረው በማድረግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መሪዎችን እና ሚናቸውን መምህር ዳንኤል አየነው እንደሚከተለው ገልጸውታል።

*ሥርዓተ ማኅሌት ለመምራት መሰረቱ ድጓ ነው። የድጓው ባለሙያ ደግሞ መምህሩ(መሪጌታው)ነው። ከመሪጌታው በተጨማሪ "ቀኝ ጌታ" እና "ግራ ጌታ" የማኅሌቱን ክዋኔ መንገድ በማስያዝ እና በመጠቆም በኩል የተወሰነ ድርሻ አላቸው፡ ፡ ይህ ስርዓት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌት አለው። መሪው መሪጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ተመሪው ደግሞ የቅዱሳን ሐዋርያት ምሳሌ ነው። ቀኝ ጌታው በዕለተ ዓርብ ጌታ ሲሰቀል በቀኝ የተሰቀለው ፈያታዊ ዘየማን(ጥጦስ) ምሳሌ*

*ሲሆን ግራ ጌታው ደግሞ በግራ በኩል የተሰቀለው ፈያታዊ ዘፀጋም(ዳክርስ ምሳሌ ነው)፡፡ (ሚ.ያዝ.የ18/09/2003÷ካሴት ቁጥር 7÷side 2)፡፡*

በበዓለ ትንሣኤ ሆነ በሚያዝያ ጊዮርጊስ ክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ያለውን ሥርዓተ ክዋኔ በመምራትና በማስተባበር መምህራን ድርሻቸው ከፍተኛ እንደነበር አጥኚው አስተውሏል።



*መምህር ዮሐንስ ግርማይ የስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ሲመሩ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ*

### 5.1.7 የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ማዕቀፍ

የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ከዋዜማ ጀምሮ እስከ ንግስ ያለው ሥርዓተ ክዋኔ የሚያጠቃልል ሲሆን የወርሐ በዓል ደግሞ ወሩን ጠብቆ ከሌሊቱ 8 ሰዓት እስከጧት ብቻ ይከወናል፡፡ የእሑዱ ሥርዓተ ማኅሌት የሚቆመው መዝሙር ብቻ ሲሆን የአከዋወን ሥርዓቱም ከክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት የተለየ ነው፡፡ ይህም የሚያመላክተን በሥርዓተ ማኅሌት ዓይነቶች መካከል ያለው የክዋኔ ማዕቀፍ ልዩነት ነው፡፡ በመሆኑም በክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌቱ የደመቀ የመዘምራን እና የምዕመናን ተሳትፎም የጎላ ነው፡፡ የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት በወንበር የተዘጋጀ ወረብ ሲኖራቸው የወርሐ በዓል ግን በሊቃውንቱ የሚፈጠር የፈጠራ ወረብ ካልሆነ በቀር የወንበር ወረብ የላቸውም፡፡ ይህ በራሱ ለሁለቱም የሥርዓተ ማኅሌት ዓይነቶች የክዋኔ ማዕቀፍ የተለየ እንደሆነ በተጨባጭ የሚያመላክት ነው፡፡

መሪጌታ ተክለብርሃን የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ማዕቀፍን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት እንደ ዓይነቱ የተለያየ ነው፡፡ ዓይነቱ ሲለያይ በዕለቱ የሚቆመው ቀለምም ይለያያል፡፡ የክብረ በዓሉን ሥርዓተ ማኅሌት ለወርኃ በዓሉ፣ የወርኃ በዓሉን ስርዓተ ማሕሌት ለእሑድ ሰጥቶ መቆም አይቻልም ፡፡ ይህ ነው የየራሱ የአከዋወን ስልት(ማዕቀፍ) የሚያሰኘው፡፡ ለምሳሌ፡- የበዓለ ትንሳኤ ስርዓተ ማሕሌት ይዘቱ የምስራች ሲሆን "ዮም ፍስ ኮነ (ዛሬ ደስታ ሆነ) በማለት ይቆማል፡፡ የሚያዚያ ጊዮርጊስ የወሰድን እንደሆነም ይዘቱ የሰማዕቱ ጊዮርጊስ በዓለ ዕረፍት በመሆኑ "ደም ወማይ እምነ ክሳዱ*

*ፈልፈለ" (ደምና ውሃ ከአንገቱ ፈሰሰ) በማለት ሰማዕቱ ሲሰዋ የነበረውን ሁኔታ እያስታወስን እንቆማለን። ስለዚህ ሁለቱም በይዘትም በአከዋወን ሂደትም የተለያዩ ናቸው ማለት ነው። ከአከዋወን ይትበሃላቸው ወጡ ማለት ሰርዓተ ክዋኔው ተበላሸ ማለት ነው፡ (ሚያዚያ 9/09/2003÷ካሴት ቁጥር 8÷side 1)፡ ፡*

በአጠቃላይ ሥርዓተ ማኅሌት የክዋኔ ማዕቀፍ መጀመርያ (beginning)፣ መካከል(middle) እና መጨረሻ (ending) ያለው ነው። ስለዚህ ከተቀነበበለት የአከዋወን ስልትና ይትበሃል አይወጣም ማለት ነው። ክዋኔው ውጤታማ የሚሆነውም በተፈቀደለት ማዕቀፍ ሲከወን ብቻ ነው።

## 5.2. የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች እና ተምሳሌታዊ ውክልናቸው

የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ውጤታማ የሚሆነው ደረጃዎቹ ቅደም ተከተል ተዋረዳቸውን ጠብቀው ሲከናወኑ ነው። የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ሥርዓተ ክዋኔውን በማከናወን ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ የሚሆነው የራሳቸው የሆነ ትዕምርታዊ ውክልና ስላላቸው ነው።

የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች እርስ በርስ የተቆራኙ ከመሆናቸው የተነሳ በመካከላቸው ያለው ልዩነት የጎላ አይደለም። ከዚህ በመቀጠል የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ተምሳሌታዊ(ትዕምርታዊ) ውክልና ከመስክ ከተገኘው መረጃ በመነሳት እንደሚከተለው ይተነተናሉ።

### 5.2.1 መቃኘት

በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መቃኘት የመጀመሪያ ደረጃ ነው። መቃኘት ማለት ለመዘምራን፣ለካህናት ቃለ እግዚአብሔሩን ማሳየት፣ ማመላከት ማለት ነው። ይህ ደግሞ አይሁድ ጌታን ለመያዝ ይሁዳን አመልካች አድርገው ለመፈለጋቸው ምሳሌ ነው። ይሁዳም ብር ከሰጣችሁኝ ጌታን አሳያችኋለሁ ብሎ ከአይሁድ ጋር የተስማማበት ነው (ማቴ23፣12-20)።

በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት መቃኘት የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው ለዕለቱ የሚያስፈልገውን ቀለም ድጓውን መሰረት በማድረግ ስለሚዘጋጅ ነው። በመሆኑም መሪጌታው የድጓ ባለሙያ በመሆኑ ዕለቱን የሚመለከት ቀለም ለሊላው ያቀብላል። መዘምራኑም ከመሪጌታው ተቀብለው መዝሙሩን ይዘምሩታል። መቃኘት የሚባለውም ይህ ሂደት ነው።

መምህር ዮሐንስ ግርማይ ስለ መቃኘት ተምሳሌታዊ ውክልና የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*አይሁድ ጌታን ለመስቀል በማን በኩል ብንይዘው ያዋጣል በማለት ካሰቡ በኋላ ይሁዳን መረጡ። አበው ሲተርቱ የአገሩን በሬ በአገሩ ሰርዶ ይላሉ። ይሁዳም ጌታ*

*ካደረበት እያደረ ከዋለበት እየዋለ የእጁን ተአምራት፣ የቃሉን ትምህርት ያውቅ ነበርና በይሁዳ በኩል ሄዱ ። ይሁዳም እኔ በመጀመሪያ ሄጄ እግሩን የምስመው እርሱ ጌታ ነው አላቸው። እና መቃኘት ተምሳሌታዊ ውክልናው ይህ ነው። በሥርዓተ ማኅሌት መቃኘት ቀዳሚ የሆነው ከዚህ በመነጨ ምክንያት ነው። (ሚያዝያ 17/09/2003፣ ካሴት ቁጥር ፣5÷side 1)::*

አጥኚው በበዓለ ትንሳኤና በሚያዝያ ጊዮርጊስ ሥርዓተ ማኅሌት የዕለቱን ቀለም የቃኘው መሪጌታው ሲሆን የተቃኘውን ቀለም ተቀብለው መዘምራን እንደሚዘምሩ አስተውሏል።

ከመስክ የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው መቃኘት[13] በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የመጀመርያ ደረጃ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌታም አለው።

### 5.2.2 መቀበል

አንድ ተማሪ ካልሆነም የዜማ አዋቂ መምህር ድጓውን መሰረት በማድረግ የዕለቱን ቀለም ይቃኛል። ከዚያ መዘምራኑ ከቃኚው ተቀብለው ቀለሙን ይወጡታል። ይህም የአይሁድ ጭፍሮች ጌታን ከይሁዳ ተረክበው ለመስቀል መወሰናቸዉን የሚያመላክት ነው። በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የተቃኘውን ቀለም የሚቀበሉት መዘምራን ናቸው። መዘምራኑም ጌታ ሆይ ንጹህ አምላክ ሁነህ እያለህ የአይሁድ ጭፍሮች በአንተ የሞት ፍርድ ወሰኑብህ እያሉ የጌታን ነገረ መስቀል እያስታወሱ ይቀበላሉ። ቀለሙም እንደ ዕለቱ ይለያያል። <u>ለምሳሌ</u> የትንሣኤ በዓል የጌታ መነሳት የምስራች የሚነገርበት በመሆኑ "ዮም ፍሥሐ ኮነ" (ዛሬ ደስታ ሆነ) ብሎ መሪው ከመራ በኋላ ተቀባዮች መዘምራንም "ዮም ፍስሐ ኮነ" (ዛሬ ደስታ ሆነ) በማለት ዜማውን በመቀባበል ያዜሙታል።

መምህር ዮሐንስ ግርማይ መቀበል ምንድን ነው? እንዴትስ ይከናወናል? ምን ዓይነት ተምሳሌትስ አለው? የሚሉ ጥያቄዎችን እንደሚከተለው አብራርተዋል።

*መሪው ሞተ ክርስቶስን የሚያረዳ ሲሆን መዘምራኑም ደግሞ ሞተ ክርስቶስን የመቀበላቸው ምሳሌ ነው። ይህም ክርስቶስ ለዓለም ድህነት ሲል ሞቷል፣ በሞቱም ሞትን ሽሯል እያለ መሪው አዋጅ ሲናገር መዘምራኑም የመሪውን ቃል በመቀበል አማን በአማን (እውነት በእውነት) እያሉ ዜማውን ያዜማሉ። <u>ለምሳሌ</u> ከበዓለ ትንሣኤ ቀለም አንዱን ብንወስድ "ዮም ፍሥሐ ኮነ" በማለት መሪጌታው የክርስቶስን መነሣት*

[13]መምህር ዳንኤል አየነው መቃኘት በመሪጌታው አማካይነት የተመራውን ቀለም በህብረት መዘምራኑ መዘመር ማለት ነው። "ከይሁዳ ጋር ተያያዥነት አለው። ይሁዳ አምላኩን ለመሸጥ ባለመወላወሉ ከአይሁድ ጋር ተስማማ። አይሁድም ኢየሱስን ማን ያሳየናል? እንዴትስ እንያዘው? ብለው ሲመካከሩ፣ ይሁዳ እኔ አሳያችሁአለሁ አላቸው። አይሁድም ኢየሱስን ለመያዝ ይሁዳን አመላካች አደረጉት። እንግዲህ በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ቀለሙ የሚቃኘው ከዚህ ምስጢር በመነጨ ነው።"( ሚያዚያ 18/09/2003፣ ካሴት ቁጥር፣7÷side 1)::

*ያበስራል። መዘምራኑም የመሪጌታውን ምርሐት ተከትለው የምስራቹን በህብረት በዝማሬ ይዘምሩታል፡፡ (ሚያዝያ17/09/2003፣ካሴት ቁጥር ፣5÷side 2)::*

በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ መቀበል የመዘምራኑ ድርሻ ቢሆንም የሞተ ወልደ እግዚአብሔር ምስጢር የጋራ በመሆኑ ሊቃውንቱ ሲዘምሩ ምዕመናኑ በአንክሮ ያጤናሉ፡፡ መዘምራኑ የምስራቹን ሲያበስሩ ምዕመናኑ የምስራቹ ተሳታፊ በመሆናቸው በእልልታና በጭብጨባ ደስታቸውን ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ መቀበል ስብሐተ እግዚአብሔርን ከመሪው ተቀብሎ በአግባቡ መዘመር ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌት ያለው ነው።



ተመሪው ከመምህር ዮሐንስ ግርማይ በእለቱ የተመራውን ቃለ እግዚአብሔር ሲቀበል የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

### 5.2.3 መምራት

ይህ የስርዓተ ማሕሌት ሦስተኛ የክዋኔ ደረጃ ሲሆን መምራት ማለትም የዕለቱን ቀለም በቅድሚያ በዜማ ማቀበል ማለት ነው፡፡

መሪ ማለት "ዜማን ለተመሪው እየነገሩ እንዲያዜም የሚያደርግ ነው" (አማርኛ መዝገበ ቃላት 1993፡43)፡፡

በስርዓተ ማሕሌት አገልግሎት ቃለ እግዚአብሔሩን የሚመራ መርጌታ (መምህር) ነው፡፡ ቃለ እግዚአብሔሩን የሚመራው በባለሙያ በመሆኑ የራሱ የሆነ ተምሳሌታዊ ውክልና አለው፡፡

በስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ መሪው ቃለ እግዚአብሔሩን ይመራል፡፡ ተመሪውም ቃለ እግዚአብሔሩን በአግባቡ ይመራል፡፡ ይህም ሊቀ ካህናቱ ሐና ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲይዙት ጭፍሮችን የመላኩ ምሳሌ ነው፡፡ (ማህበረ ቅዱሳን 1993፡9)

መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገ/ጊዮርጊስ የመሪው ተምሳሌት እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡ መሪ የዮሐንስ መጥምቅ ምሳሌ ነው፡፡ መሪ ሆኖ የክርስቶስን መምጣት እየገለጸ ወንጌልን ያስተማረ ዮሐንስ መጥምቅ ነው፡፡ ዮሐንስ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ከዮሐንስ ስብከቱን ተቀብሎ ወንጌል ያስተማረ ክርስቶስ ነውና፡፡ በመሪ ገጽ ዜማውን የዘለቁ መዘምራን የአርድእተ ዮሐንስ (የዮሐንስ ተከታዮች) ምሳሌ ናቸው፡፡ መምህራቸው ዮሐንስ ያስተማራቸውን ትምህርት አምነው ክርስቶስን ተቀብለዋልና፡፡ ከአንሺ ገጽ ተቀብለው ዜማውን የሚዘልቁት የአርድእተ ክርስቶስ (የክርስቶስ ተከታዮች) ምሳሌ ናቸው፡፡ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ያስተማሩት ትምህርተ ክርስቶስ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳልና፡፡ በመጨረሻ ዜማውን በህብረት ማድረሳቸው መላእክትና ሰዎች በጎለ እንስሳ የተወለደውን ሕጻን ክርስቶስን በኅብረት የማመስገናቸው ምሳሌ ነው( 1997፡ 95)።

በአጠቃላይ የስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ የሚመራ መሪጌታው ሲሆን ሂደቱም መምራት ይባላል፡፡ መሪው የጲላጦስ፣ የሊቃ ካህናቱ ሐና እና የመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌ ተደርጎ ይወስዳል፡፡ ይህም ተምሳሌታዊ ውክልና ስርዓተ ክዋኔውን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ሲሆን ምንጩም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች መገንዘብ ይቻላል፡



መምህር ዮሐንስ ግርማይ የዕለቱን ቃለ እግዚአብሔር ለሚመራው ዲያቆን ሲመሩ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

### 5.2.4 መመራት

መመራት በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ አራተኛ ደረጃ የያዘ ሲሆን ይህ ሥርዓተ ክዋኔ በመሪና በተመሪ መካከል የሚከወን ነው፡፡ መመራት ማለትም ቃለ እግዚአብሔርን ከመሪው መቀበል ማለት ነው፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ተመሪ “መሪው ቀደም እያለ የሚናገረውን ዜማ ወይም ቅኔ የሚያዜም መዘምር” በማለት ይበይነዋል (1993፡46)፡፡

በሥርዓተ ማኅሌት መምራትና መመራት[14] ሂደት አንሺዎች አሉ። ይህም በግራ በኩል ቀለሙን የሚያነሳ ግራ ጌታ እና በቀኝ በኩል ቀለሙን የሚያነሳ ቀኝ ጌታ ናቸው። መምህር ዳንኤል አየነው ስለ መሪ ተመሪ እና አንሺ እንደሚከተለው አብርርተዋል።

"መዘምራኑ የመሪውን ቃል ማንሳታቸው ክርስቶስን በየተራ በመቀባበል የፈረዱበት የቀያፋ፣ የጲላጦስና የሄሮድስ ምሳሌ ነው። በመጨረሻም ቃለ እግዚአብሔሩ ለመሪው ይመልስና በመሪው ያልቃል። ይህም ነገረ መስቀሉ በሊቀ ካህናቱ ሐና የመፈጸሙ (የመደምደሙ) ምሳሌ ነው።" (ሚያዝያ18/09/ 2003፣ ካሴት ቁጥር፣7÷side 1)::

መሪጌታ ልሳነ ወርቅ በበኩላቸው ስለ መሪ፣ ተመሪ እንዲሁም ንሺ በተመለከተ የሚከተለውን ሐሳብ አስፍረዋል።

"ቅዱስ ያሬድ የመላእክትን ሥርዓት አይቶ መጣ ሱራፌል በየአሉበት ያታ በትክክል ቆመው ከመካከላቸው አንዱ በመራቸው ተከትለው በአንድ ቃል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር እያሉ ሲያመሰግኑ በማየቱ ያጠናው ማሕሌታቸው በአንድ መሪ መነሻ በአንድ መሪ መድረሻ እየተመራ እግዚአብሔር እንዲመሰገንበት የሰራው ስርዓት ነው።" (1997፡107)።

በአጠቃላይ መምራት በመሪው ወገን ወደ ተመሪው ቃለ እግዚአብሔርን ማስተላለፍ ሲሆን ይኸውም ተመሪው የዕለቱን ቃለ እግዚአብሔር ከመሪው ተቀብሎ ለመዘምራኑ ማቀበል ነው። ይህም የአይሁድ ጭፍሮች በተሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው መጀመሪያ ከሊቀ ካህናቱ ሐና ፊት ለማቅረባቸው ምሳሌ ነው(ዮሐ 18÷13):: መዘምራኑ ከግራና ከቀኝ የመሪውን ቃል ማንሳታቸው ጌታን በየተራ ተቀብለው የፈረዱበት የቀያፋ፣ የጲላጦስና የሔሮድስ ምሳሌ ነው። ሉቃ (23÷27፣ ዮሐ 28÷24) በመጨረሻም ቃለ እግዚአብሔር ወደ መሪው ተመልሶ በመሪው ማለቁ ነገረ መስቀሉ በሊቀካህናቱ ሐና ተፈፅሟልና ለዚያ ምሳሌ እንዲሆን ነው።
ከጽሑፍም ሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች የሚያረጋግጡት ይህንኑ ነው።

---

[14] የመሪውና የተመሪውን ተምሳሌታዊ ውክልና በተመለከተ መምህር ዮሐንስ ግርማይ የሚከተለውን ሐሳብ ገልጸዋል።
*ማኅሌት ሥርዓተ አገልግሎቱ እንዲቀላጠፍ እና ሥርዓት እንዲኖረው መሪ እንዳለው ሁሉ ቃለ እግዚአብሔሩን የሚቀበል ተመሪም አለው። ተምሳሌቱ፡ መሪውና ተመሪው አርጂና ተረጂ ናቸው። መሪው ሞተ ክርስቶስን ይናገራል። ተመሪው ደግሞ ሞተ ክርስቶስን ሰምቶ ተረድቶ የማዘኑና የማልቀሱ ምሳሌ ነው። ይህም ጌታ ከሃና ወደ ቀያፋ፣ ከቀያፋ ወደ ሃና የመመላለሱ ምሳሌ ነው። መልእክት አመላላሾቹ ተመሪዎች ናቸው (ሚያዝያ 17/09/2003፣ ካሴት ቁጥር ፣5÷side 1)::*



ተመሪው የዕለቱን ቃለ እግዚአብሔር  ከመሪው መምህር

5.2.5 ዝማሜ

ይህ በአምስተኛ ደረጃ የሚከወን የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ሲሆን ዝማሜ የሚለው ቃል "ዘመ፤ዘመመ ከሚለው የግዕዝ ቋንቋ የተወረሰ ሲሆን ትርጉሙም መዝመም ወይም ማጋደል ማለት ነው፡፡ ዝማሜ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ የሚሰጠው ፍቺ የቀለም አባባል ነው፡፡"ሥርግው ሐብለ ስላሴ አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበቃላት (1994÷223)፡፡

ከዝማሜ በፊት ቁም ዜማው በሕብረት ከተዘለቀ በኋላ  የድጓው መጀመሪያ ክፍል ይመራል፡፡ መሪ እየመራ ተመሪ እየተመራ ይባላል፤ ቀጥሎም መዘምራኑ በህብረት መቋሚያውን  ወደ ቀኝና ወደ ግራ ወደፊትና ወደኋላ  እየወዘወዙ አልፎ አልፎም መሬቱን እየመቱ  የሚከወን ነው፡፡ የዚህ ምሳሌ መሪው የይሁዳ፤ ተመሪው የቀያፋ ምሳሌ ሆኖ ይሁዳ ኢየሱስ ካለበት ቦታ መርቼ እወስዳችኋለሁ ብሎ ለሊቀ ካህናቱ ለቀያፍ መንገሩንና  ቀያፋም እሺ ብሎ  በነገሩ መስማማቱን ያመለክታል (ሉቃ 22÷3-6) ከምራት በኋላ መዘምራኑ በህብረት መዝመማቸው ይሁዳ በተናገረው ነገር ተስማምተው ዱላ በመያዝና በመደንፋት ጌታ ወደነበረበት ወደ ጌቴ ሴማኒ መሄዳቸውን ያመለክታል (ማቴ 26÷47)፡፡

የመቋሚያው ውዝዋዜና አመታት ጌታን አንዱ  ወደፊት ሌላኛው  ወደኋላ  አንዱ ወደ ቀኝ ሌላኛው ወደ ግራ እየገፈተሩ በያዙት ዱላም እየደበደቡ ማንገላታታቸውን ያመለክታል፤ ዝማሜ  ከተዘለቀ በኋላ  መሪ እየመራ ተመሪ እየተመራ  ምልጣኑን እስከ ጫፍ ድረስ ይመራል፡፡ ጫፍ ላይ ሁለት ጊዜ በህብረት ይዘመማል፤ ቀጥሎ ግራና ቀኝ ይነሳል፤ "ምልጣኑም"  ተደጋግሞ ይዘመማል፤ የዚህም  ምሳሌ ይሁዳ አይሁድን  መርቶ ወስዶ ጌታን  ካስያዛቸው  በኋላ በየተራ  ወደ ሐናና ወደ ቀያፋ ሲያመላልሱት ማደራቸውን በዚህ ጊዜ ሁለት ሰዎች ሊቃነ ካህናቱን ለመደገፍ በጌታ ላይ በሐሰት

መመስከራቸውን እንደዚሁም ወታደሮች በየመንገዱ ደጋግመው ማንገላታታቸውን ያመለክታል (ዮሐ 18÷24 ማቴ 26÷ 61-68)።

መምህር ዳንኤል አየነው ዝማሜ የሚከናወነው በመቋሚያና በጽናጽል ሲሆን ተምሳሌታዊ ውክልናም አለው።

> *ተምሳሌቱም ማንሻው መመርገዱ ለጌታ የተረፈው መከራ ለሐዋርያት መትረፉ ለማጠየቅ ነው። መቋሚያውና ጸናጽሉ ከላይ ወደታች ማውረዳቸው ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ለመውረዱ ምሳሌ ሲሆን ጸናጽልና መቋሚያው ወደ ትከሻቸው ማውጣታቸው ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማየ ሰማያት የመውጣቱ ምሳሌ ነው። መቋሚያውና ጸናጽሉ ወደፊትና ወደኋላ ማወዛወዛቸው ደግሞ ጌታ በአይሁድ እጅ የደረሰበት መከራ ምሳሌ ነው። (ሚያዝያ18/09/2003፣ ካሴት ቁጥር፣7÷side 1) በማለት ገልጸዋል::*

መምህር ዮሐንስ ግርማይ የዝማሜን ተምሳሌት በተመለከተ የሚከተለውን ሐሳብ ገልጸዋል፡

> *በመቋሚያው ወደፊትና ወደኋላ መዝመማቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ወደ ቀያፋ፣ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ የመመላለሱና የመውደቁ ምሳሌ ሲሆን በመቋሚያ መሬቱን መምታታቸው አይሁድ የጌታን ራስ በዘንግ የመምታታቸው ምሳሌ ነው። አይሁድ ጌታችንን ከሐና ወደ ቀያፋ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ሲያመላልሱት "መኑ ኰርኦከ ተነበይለነ?" (ማነው የኮረኮመህ እስቲ እወቅልን?) እያሉ በዘንግ እራስ እራሱን ደብድበውታልና ኩርዓተ ርዕሱን ለማስታወስ ነው። ይህም በወንጌለ ማቴዎስ ምዕራፍ 26÷ ቁጥር 6 ይገኛል (ሚያዝያ 17/09/2003/ ካሴት ቁጥር 5፣side 1) በማለት አስረድተዋል።*

መቋሚያው እንደ ማማተብ አድርገው ከትከሻቸው አውርደው ከመሬት ላይ ማሳረፋቸው ክርስቶስ መስቀል ተሸክሞ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ ድረስ ሲጓዝ ከድካሙ የተነሳ ከመሬት ያሳርፈው ነበርና ይህንን ለመመሰል ነው። ከትከሻቸው አውርደው ለሌላ መስጠታቸው ክርስቶስ መስቀል ተሸክሞ ከመንገላታቱ ብዛት የተነሳ በደከመው ጊዜ "ያሰብነው ነገር ሳይደርስ ፈጽሞ እንዳይሞትብን" በማለት አይሁድ መስቀሉን ለሌላ ሰው የማሸከማቸው ምሳሌ ነው (ሐመር 6ኛ ዓመት ቁጥር 2)።

መሪጌታ ልሳነ ወርቅ በበኩላቸው መዘምራኑ ከመቋሚያቸው ጋር ወደፊት መዝመማቸው እና እንደገና መልሰው ከቀኝ ወደግራ መዝመማቸው አራቱን አቅጣጫ (ሰሜን፣ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ) ለመመሰል ነው። ምስጢሩም ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱም ማእዘን ባሉት ፍጥረታት የሚመሰገን መሆኑንና ከፍ ከፍ የሚል እንደሆነ የሚናገር ትምህርት ያለው ነው። መቋሚያቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው መልሰው መሬት በማሳረፍ መደሰቅ፣ እንደገና ወደ ላይ ማድረጋቸው የእግዚአብሔር በሰማይ ሕያው ሆኖ መኖሩን ሲያመላክት ወደታች መመለሳቸው ደግሞ የአምላኪዎቹ በፍርሃት፣ በመገዛት ራስን ዝቅ ማድረግን ያጠይቃል (1997÷XXIX) ብለዋል።

በአጠቃላይ ከጽሑፍ ሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ዝማሜ[15] በመቋሚያ እና በጸናጽል ታጅቦ በመዘምራን የሚከወን ስርዓት ሲሆን የራሱ ተምሳሌታዊ ውክልና አለው፡፡ ተምሳሌታዊ ውክልናውን በተመለከተ የተሰጡት ተምሳሌቶች ከመምህር ወደ መምህር መጠነኛ ልዩነት ቢኖራቸውም መሰረታዊ ተምሳሌቱ ግን የሁሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። የተፈጠረው መጠነኛ ልዩነትም ከእውቀት፣ ከአተረጓጎምና ከሙያ አንጻር በመነጨ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ በቤተክርስቲያን የሚዘመሙ ዝማሜዎች ሥርዓተ ክዋኔያቸው በጠበቀ መልኩ እንደሚከወኑ ያሳያል፡፡

በቤተ-ክርስቲያን የሚዘመሙ ዝማሜዎች ዋዜማ፣ አንገርጋሪ፣ አቡን፣ ቅኔ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕት፣ እስመ ለአለም መዝሙር ሲሆኑ እነዚህም እንደ ዘማሪያኑ ብዛት እንደ ቤተክርስቲያኑ ስፋት እና ጥበት በህብረት ወይም ደግሞ ግራና ቀኝ እየተከፈለ የሚዘመሩ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡



መዘምራኑ በበዓለ ትንሳኤ ዝማሜ ሲያከናውኑ የሚያሳይ ፎቶግራፍ

15 ሊቀ ትጉሃን ሞላ ስለ ዝማሜ ተምሳሌታዊ ውክልና ሲገልጹ

*በማጋዳል(በማጋደም) በቀስታ ወደታች ወደላይ ጫፉን በማዝመም መዘመራቸው ለክርስቶስ መራራ የሰፍነግ ሐሞት "እንካ ጠጣ" እያሉ አይሁድ ሲያቀርቡለት የነበረ ምሳሌ ነው፡፡ መዘምራኑ መቋሚያቸውን በኃይል ወደላይ እና ወደታች መወርወራቸው ክርስቶስ ከሰማይ ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከስጋዋ ስጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡ አንድም ከግራ ወደ ቀኝ ማድረጋቸው በምድር ላይ በመዋዕለ ሥጋዌ 33 ዓመት ከ3 ወር ተመላልሶ ማስተማሩን ለማጠየቅ ሲሆን መቋሚያው መላልሰው ወደ ላይ ማድረጋቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተግባረ ምድርን ፈጽሞ ወደ ሰማይ የማረጉን ምሳሌ ነው (ሚያዝያ 19/09/2003፣ የካሴት ቁጥር፣1÷side 1)::*

### 5.2.6 ንዑስ መረግድ

ይህ ስድስተኛ ደረጃ ክፍለ ማሕሌት መዘምራን ቆመው ጸናጽሉን ላይና ታች እየጣሉና ከበሮ እየመቱ የሚሉት ነው። የዚህ ምሳሌ አይሁድ ሲነጋ ጌታን ይዘው በጲላጦስ ፊት ለፍርድ ማቆማቸውን ለማጠየቅ ነው (ማቴ 27÷11)።

ንዑስ መረግድ የዕለቱ ቀለም ሙሉ ዜማ ከተባለ በኋላ የሚከናወን ስርዓተ ማሕሌት ነው። ይህም በከበሮ እና በጸናጽል ታጅቦ የሚባል ሲሆን በግራ ሁለት ጊዜ ከተቆረቆረ በኋላ በቀኝ በኩል ይመታል። ከዚያም ቀለሙ ይመለስና ማንሻው ይባላል። ማንሻው ምን ጊዜም በቁም ጸናጽል ነው የሚባለው ከዚያ ከበሮው ሲደረብ በመረግድ ሁለት ይባላል።በዚህ ሁኔታ ሁለተኛ መልክ ይጠናቀቅ እና ሦሥተኛ መልክ ይጀመራል። ይህም መልክ በቁም ይባላል። በቁሙ ከተዘለቀ በኃላ ይመረገዳል። ከዚያም ቀለሙ ይመለስና ማንሻው ይባላል። በዚህ ጊዜ ካህኑ እጣን ያጥናሉ።ንዑስ መረገድ ሲከናወን ካህናትና ዲያቆናት በማዕጠንት ያገለግላሉ። በዚህም ካህኑ ትልቅ የእንጨት መስቀል ትከሻቸው ላይ ተሸክመው በግራ እጃቸው ጽንሐውን በመያዝ ሲያጥኑ ዲያቆኑ ደግሞ በግራ እጁ ጧፍ ይዞ ካህኑ ጋር ይከተላል። በእርግጥ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ዲያቆናትና ካህናት በማዕጠንቱ ይሳተፋሉ። ይህ ግን እንደ አገልጋዮቹ ብዛት እና እንደ ቤተክርስቲያኑ ስፋት ይወሰናል።

መምህር ዮሐንስ ግርማይ የንዑስ መረግድን ተምሳሌትበተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

> *ንዑስ መረግድ ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ እጅ ተይዞ በንጉሱ ጲላጦስ መቅረቡ የሚያጠይቅ ነው። በዚህም ወቅት በርባን ይፈታልን፣ ክርስቶስ ይሰቀልልን እያሉ ይጩጩሁ ነበር። አንዳዶቹም አንተኑ ንጉሰ እስራኤል? (የእስራኤል ንጉስ አንተ ነህን?) እያሉ ያሾፉበት ነበር። ስለዚህ ተምሳሌቱ ይህ ነው። ንዑስ መረግድ ረጋ ተብሎ መቅርቆና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጲላጦስ ፊት ቀርቦ አይሁድ ሲዘባበቱበት ምንም መልስ ያለመስጠቱ ምሳሌ ነው (ሚያዚያ 17/09/2003፣ ካሴት ቁጥር፣5÷side 2)::*

ንዑስ መረግድ በከበሮው አመታትም ሆነ በጸናጽል አወራረድ ብዙ መራቀቅ የሌለበት ሆኖ በቀላሉ ጥሬውን ዜማ፣ ቁሙን መስሎ የሚዘመር ነው (ሥርግው ሐብለ ስላሴ፤ አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት 1994÷16)።

በተመሳሳይ መልኩ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ንዑስ መረግድ የሚባለው መዝሙርም ይሁን ምልጣን በዘንግ ዝማሜውን ከጨረሱ በኃላ በጸናጽል እና በከበሮ በንዑስ አመታት የሚዘመር ነው። እርሱንም ከመጽፊያው ጀምሮ በአመላለስ ይዘመርና በኃላ ወደ ዓቢይ

መረግድ ያገባዋል ። ንዑስ የተባለበትም በከበሮው አመታትም ሆነ በጸናጽል አወራረድ ብዙ መራቀቅ የሌለበት ሆኖ በቀላሉ ጥሬውን ዜማ፣ ቁሙን መስሎ የሚዘመር ነው(1963፣103)።

ከላይ ከተገለጹት የጽሑፍ ሆነ የመስክ መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው ንዑስ መረግድ ከሌሎች የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች በቀላሉ የሚከወን እና ብዙም መራቀቅ የማይታይበት ሲሆን አከዋወኑም በከበሮ እና በጸናጽል ብቻ ነው። በዚህ ሥርዓት ክዋኔ ከበሮው ቁጭ ተብሎ የሚመታ ሲሆን መዝሙሩ ግን ተቆሞ የሚዘመር ነው። በመሆኑም ከመዘምራኑ በተጨማሪ የካህናትና የዲያቆናት ተሳትፎ ጎልቶ የሚታይበት የማህሌት ክፍል ነው።

## 5.2.7 ዓቢይ መረግድ

ይህ የማሕሌት ክፍል ከንዑስ መረግዱ በኋላ የሚከወን ሲሆን ፈጠን እና ሞቅ ባለ የከበሮ አመታት የሚባል ነው። ይህኛው በዜማው፣ በከበሮው አመታትም ሆነ በጸናጽል አጣጣሉ የተለየ መልክ ያለው ነው። የአካል ንቅናቄ (እንቅስቃሴ) የሚያስከትል ሲሆን ወደ ቀኝና ወደ ግራ በመንቀሳቀስ ይከወናል። የጸናጽሉ አጣጣልም እንደ ከበሮው ፈጠን ያለ ነው። የዚህ ምሳሌ ጲላጦስ ጌታ እንዲገረፍ በፍጥነት ውሳኔ መስጠቱን፣ወታደሮቹም ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየገፈተሩ ወደ መግረፍያ ቦታ የመውሰዳቸውን፣ ሕዝቡም በችኮላ በሞት መወገድ አለበት እያሉ ከፍተኛ ጩኸት የመጮኃቸው ምሳሌ ነው። ግርፋቱም በኦሪት ከታዘዘው ሕግና ደንብ ውጭ እጽፍ ድርብ እያደረጉ ጌታን የመግረፋቸው ምሳሌ ነው (ማህበረ ቅዱሣን 1993፣9)።

መምህር ብርሃነ ሕይወት በጽሐ የዓቢይ መረግድን ተምሳሌታዊ ውክልና በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

"የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንገላታት ምሳሌ ነው። አይሁድ በሕጋቸው የገረፉት አይሰቅሉትም፣ የሚሰቅሉት ከሆነ ደግሞ አይገርፉትም ነበር። ሆኖም ግን ይህ ህግ ለጌታ አልሰራም፣ እንድያውም ግርፋቱን ረጋ ብለው ከጀመሩ በኋላ 40 ለመግረፍ ቁጥር ተሳሳትን እየተባባሉ 6666 ጊዜ ገርፈውታል። የከበሮ ሆነ የጸናጽሉ ፍጥነት የጌታ ግርፋት ተምሳሌት ነው።" (ሚያዝያ 20/09/÷2003፣ ካሴት ቁጥር 4፣side 1)

በአጠቃላይ በዓቢይ መረግድ ሥርዓተ ክዋኔ ከበሮው በፍጥነት የሚመታ ሲሆን የሚመታው ሰፊው የከበሮ ክፍል ነው። ስለዚህ አቢይ መረግድ በከበሮው እና በጸናጽሉ ፍጥነት የሚዘመር ነው። በዚህ ወቅት የመዘምራኑ የአካል እንቅስቃሴም ፈጣን ሲሆን ተምሳሌታዊ ውክልናው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀል ጋር የተያያዘ ነው።

### 5.2.8 ጽፋት[16]

ይህ የማኅሌት ክፍል ጸናጽሉም ሆነ ከበሮው በፍጥነት እየተመታ የሚዘመርበት ክፍል ነው። በእርግጥ የቃሉ ትርጉም ከግሱ የተገኘ ነው። ጸፍዐ በጥፊ መታ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ በጥፊ መምታት ማለት ነው።

ሊቀ ትጉሃን ጸዳል ካሳው የጽፋትን ሥርዓት ክዋኔ እና ተምሳሌታዊ ውክልና እንደሚከተለው አብራርተዋል።

"ጽፋት መዝሙሩ ከተዘመረ በኋላ መዘምራኑ ከበሮውም ሆነ ጸናጽሉ እያፋጠኑ የሚዘምሩበት ክፍል ነው። ይህም አይሁድ የጌታን ፊት በጨርቅ ሸፍነው ደጋግመው በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው። አይሁድ ሲዘባበቱ ማን መታህ ይሉት ነበር።" (ሚያዝያ 19/09/2003፣ የካሴት ቁጥር፣10÷side 1)::

ጽፋት ከአመላለስ (ምልስ ወረብ) ጋር ቃለ እግዚአብሔሩን በዜማ እያፋጠነ በከበሮ እና በጸናጽል መዘመር ነው (ሐመር መጽሔት 1986÷ ቁጥር 7)።

በአጠቃላይ ጽፋት እንደሌሎቹ የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች በከበሮ እና በጸናጽል ታጅቦ የሚዘመር ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሌት አለው። ከሌሎች የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች የሚለየው ግን ጽፋት ከአመላለስ (ምልስ ወረብ) ጋር የሚባል መሆኑ ነው።

### 5.2.9. ድርብ ጽፋት

ይህ ክፍለ ማኅሌት በጸናጽልና በዜማ ቃና ከተራው ጽፋት በከበሮ አመታት ለየት አድርጎ በጸናጽል ብቻ መዘመር ነው። ምሳሌው አይሁድ ጌታን ደጋግመው በጥፊ እንደመቱት ለማሰብ ነው (ማሕበረ ቅዱሳን ፣ 1993፣9)።

መምህር ዳንኤል አየነው ስለ ድርብ ጽፋት ተምሳሌታዊ ውክልና እንደሚከተለው አብራርተዋል።

በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት መረግዱ ከተመረገደ በኋላ በከበሮ ይፀፏል። ከዚያ በመቀጠል ጽፋቱ ድርብ ይሆናል። ድርብ ጽፋት ሲባል ሁለት ጊዜ ተመላልሶ መጸፋቱ

---

[16] በተመሳሳይ መልኩ መምህር ዮሐንስ ግርማይ መዝሙሩ ከተዘመረ በኃላ ወደ ታች ይሄዳል። ከዚያ ከበሮው ይቆረቆር እና ይጸፋል። ተቆርቁሮ መጸፋቱ ቤተ አይሁድ ጌታን ገርፈውት ዝም ያለማለታቸው ምሳሌ፣በህጋቸው የተገረፈ አይሰቀልም፣ የተሰቀለ አይገረፍም ጌታ ግን ገርፈው ሰቀሉት፡ "ቁርቋሮውና ጽፋቱ መደራረቡ ጌታ ገርፈው እንደገና የመስቀላቸው ምሳሌ ነው። የከበሮው እና የጸናጽሉ ፍጥነት ደግሞ ቤተ አይሁድ ያለማቋረጥ የጌታን ፊት በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው።" (ሚያዝያ 18÷2003፣ ካሴት ቁጥር፣5÷side 2)::

አመላካች ነው። በእርግጥ ጽፋቱ ሶስት ጊዜ ሲሆን ከበሮ ይቆረቆራል ይጸፋል፣ ይቆረቆራል ይጸፋል፤ይቆረቆራል ይጸፋል። ይህ ድግግሞሽ ቤተ አይሁድ ጌታን ያለ ምንም ማመንታት በተደጋጋሚ በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው (ሚያዝያ 18/09/÷2003፣ የካሴት ቁጥር፣7÷side 1)::

በአጠቃላይ ድርብ ጽፋት እንደ ሌሎች የማሕሌት ዓይነቶች በጸናጽልና በከበሮ የሚዘመር ሲሆን በተደጋጋሚ ማለት ከበሮው እስከ ሶስት ጊዜ በመቆርቆርና በመጽፋት የሚከወን መሆኑ ከሌሎች የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ልዩ ያደርገዋል። ተምሳሌታዊ ውክልናውም አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተደጋጋሚ የመምታታቸው ምሳሌ እንደሆነ ከተገለጹት የጽሁፍ እና የመስክ መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል።

### 5.2.10. የጭብጨባ ጽፋት

ይህ የመጨረሻ የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃ ሲሆን አከዋወኑም ፍጥነት የተሞላበት ነው። የጭብጨባ ጽፋት ከተራው ጽፋት ጋር በአጣጣሉና በመጠኑ ፈጠን ፈጠን አድርጎ በጸናጽል ፈንታ እያጨበጨቡ በከበሮ መዘመር ነው። ምሳሌው አይሁድ ጌታን በጥፊ ደጋግመው መምታታቸውን ለማጠየቅ ነው (ማህበረ ቅዱሳን 1993፣9)።


ሊቀት ጉሃ ፀዳል ካሳው የጭብጨባ ጽፋትን በተመለከተ የሚከተለውን ሐሳብ ገልጸዋል። "ሥርዓተ ማኅሌት ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ሲከወን ሂደቱ ጠብቆ ነው። ስለሆነም የጭብጨባ ጽፋት የማህሌት የመጨረሻ ክፍል ነው። እስከ አሁን ሥርዓተ ማኅሌት ሲከወን በከበሮና በጸናጽል ታጅቦ ነው። በዚህ ክፍል ግን በጸናጽል ፈንታ የእጅ ጭብጨባ ይደረጋል። ይህ ጭብጨባ በመዘምራኑ ብቻ ሳይሆን በምዕመናን ጭምር ነው። ይህም የጌታ መመታት ምሳሌ ነው።" (ሚያዝያ 19/09/2003፣ ካሴት ቁጥር፣10÷side 2)::

የጭብጨባ ጽፋት እንደ አንድ የስርዓተ ማሕሌት ደረጃ የራሱ ክዋኔ ያለው ሲሆን ከሌሎች ለየት የሚያደርገው የመዘምራን እና የምዕመናን የእጅ ጭብጨባ የሚከናወንበት በመሆኑ ነው።

በአጠቃላይ የስርዓተ ማሕሌት ደረጃዎች አስር እንደሆኑ ይነገራል። መምህር ዮሐንስ ግርማይ አስር የመሆናቸው ምክንያት እንሚከተለው አብራርተዋል።

> *የስርዓተ ማሕሌት ደረጃዎች አስር መሆቸው። "ወበአሰርቱ አውታሪሁ መዝሙረ ማሕሌት ወመሰንቆ እዜምር ለከ" (አስር አውታር ባለው በገና እዘምርልሃለሁ") ብሎ ቅዱስ ዳዊት ትንቢት ተናግሯል። የዳዊት በገና አስር አውታር እንዳለው ሁሉ የማሕሌት ደረጃዎችም ከዚህ በመነጨ አስር ናቸው።አንድም ስለ አሰርቱ (10ቱ) ማዕረገ ፃድቃን ሲያስረዳ ነው። እያንዳንዳቸውም ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው። (ሚያዚያ 17/09/2003፥ካሴት ቁጥር 5፥ Side 2)::*

የክብረ በዓል ስርዓተ ማሕሌት ከሌሎች የማሕሌት ዓይነቶች ልዩ የሚያደርገው አንዱ ዋዜማው ነው፡፡ በዋዜማው የዕለቱ ቀለም ከድጓው በመምረጥ የሚከወን ሲሆን ቀለሙ በአግባቡ ተመርግዶና የማንሻው ቀለም እንደ ደንቡ(ስርዓቱ) ተጸፍቶ ካበቃ በኋላ በመዘምራን የሚከናወኑ ሦስት አገልግሎቶች አሉ፡፡ እነዚህም አመላለስ፣ ወረብ እና አጽሕሶ ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓተ አገልግሎቶች የራሳቸው ተምሳሌታዊ ውክልና ያላቸው በመሆናቸው ከዚህ በታች በቅደም ተከተል እንመለከታቸዋለን፡፡



መዘምራኑ በሚያዝያ ጊዮርጊስ ስርአተ ማሕሌት ክዋኔ ሲያጨበጭቡ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

### ሀ. አመላለስ

አመላለስ[17] በአንድ ወይም በሁለት ወይም በሶስት መዘምራን ጣዕመ ልሳን በቀስታ በማስረዘም እያለዘቡ በማመላለስ ወደ ፍጥነት መሄድ ማለት ነው፡፡ የከበሮውም አመታት የጣዕመ ልሳኑን ርዝመትና እጥረት ተከትሎ ይሄዳል (ማህበረ ቅዱሳን 1999፣ 10)፡፡

---

[17] በተመሳሳይ መልኩ ሊቀ ትጉሃን ፀዳል ካሳው ስለ አመላለስ ስርዓተ ክዋኔ የሚከተለውን ሐሳብ ሰጥተዋል፡፡

*አመላለስ በማህሌት ክዋኔ ውስጥ የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን አብዛኛው ጊዜ ለወረብና ለአጽሕሶ እንደመነሻ ወይም እንደ መድረሻ ነው፡፡ መረግዱ ከተመረገደ በኋላ በጥፋት አፍጥኑ የተባለውን ድርሰት በተቀነባበረና በሚማርክ ዜማ ያዜማሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሁሉም መዘምራን ካዜሙት በኋላ ከበሮ የሚመቱ አገልጋዮች ይመረጣሉ፡፡ በመቀጠልም ጸናጽል ለሁሉም ይታደላል፡፡ መዘምራን በፊትና በኋላ በመሆን ይዘምራሉ፡፡ ከበሮ የሚመቱ አገልጋዮችም ከመዘምራኑ ፊትና ኋላ ይሰለፋሉ፡፡ ከዚያም በመቀጠል የክዋኔው ስርዓት በከበሮ እና በጸናጽል ታጅቦ ይከወናል፡፡ ካህናቱ እና መዘምራኑም አንድ ጊዜ ወደ ግራ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ቀኝ ይዘማሉ፡፡ ወደ ላይና ወደታች ቀና ጎምበስ በማለት ዝማሬውን ይዘምራሉ (ሚያዝያ 18/9/2003፣ ካሴት ቁጥር፣10÷side 2)::*

መዘምራን ጣዕመ ልሳን የሚዘመረው ዝማሬ አመላለስ ወይም ለዘብ ይባላል"(1981፣ 260)።

መምህር ዮሐንስ ግርማይ የአመላለስ ተምሳሌታዊ ውክልና በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል፡-

> *አመላለስ መቋሚያውን በትክሻ ላይ በመሸከምና በማስረገጥ፣ በጭብጨባና በእልልታ፣ መጀመርያ ዝግታ ባለው አመታት ተመላልሶ ኋላ የሚሸበሸብ ነው። ይህም ጲላጦስ ቀስ ብሎ አይሁድን በማሳመን ጌታን ሊያድን ፈልጎ መላልሶ ምን አደረገ እያለ መጠየቁን ያሳያል። ኋላ በሽብሻቦ መባሉ ግን ጲላጦስ በመጨረሻ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት ብሎ አሳልፎ መስጠቱንና ሕዝቡና ወታደሩ ደስ ብሎአቸው ተቻኩለው በእርግጫ እየተመቱ መስቀሉን አሸክመው ሊሰቅሉት ወደ ቀራንዮ መውሰዳቸውን የሚያመለክት ነው(ሚያዝያ 17/09/2003፣ የካሴት ቁጥር፣ 5÷side 2)::*

ሀብተማርያም ወርቅነህ "አመላለስ ማለት ወዝ ባለው ድምፅ ከመድፌያ ላይ መመለስ፣ እያመላለሱም ማዜም ማለት ነው፣ ለዘብ ባለ መልክ መጽፌያውን እየመላለሰ ያለዝበዋል ያዜመዋል፣ ስለዚህም መልስ በማለት ፈንታ ለዘብ የሚሉ አሉ፣ ለዘብ ባለ ድምጽ በሚያስደስት አኳሃን ይዘምሩታልና" (1963፣114) ።

በአጠቃላይ በለዘብ ጊዜ ካህናቱ እና መዘምራኑ እንደቤተክርስቲያኑ ስፋት እና እንደ ሊቃውንት ብዛት በቅኔ ማኅሌት የሚዘምሩት መዝሙር በማስረገጥ ሲሆን መዘምራኑ ሲያስረግጡም ቀለሙን መሰረት በማድረግ ከጸናጽሉ እና ከከበሮው ጋር እያዋሐዱ ነው። መዘምራኑ ሲያስረግጡ በእግራቸው መሬቱን መታ ያደርጉታል። መዘምራኑ ግራና ቀኝ በመሆን ያስረግጣሉ። ይህም የራሱ የሆነ ተምሳሌት ያለው ነው። መዘምራኑ ግራና ቀኝ ሆነው ማስረገጣቸው አይሁድ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው 340 ጊዜ የመርገጣቸው ምሳሌ ነው። አንድም በክርስቶስ ካሳ፣ መከራ፣ ስቅለትና ሞት ጠላት ዲያብሎስ ተረግጦ የመጣሉ ምሳሌ (ሐመር 1986፡ቁጥር 7)። በአጠቃላይ አመላለስ የኢየሱስ ክርስቶስን ነገረ መስቀል ተምሳሌታዊ ውክልና የያዘ ነው።

**ለ. ወረብ**

ወረብ[18] ማለት ቅብብሎሽ፣ ድግግሞሽ ማለት ነው። ይህም በመቀባበልና ደጋግሞ በመመላለስ የሚባል መሆኑን ይገልጻል። የወረብ አባባል እንደ አመላለስ መቋሚያን

---

[18] መምህር ዮሐንስ ግርማይ ወረብ በየትኛው የሥርዓተ ማኅሌት ዓይነትና መቼ ሊከወን እንደሚችል ምላሻቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል።
"ወረብ በሁሉም የሥርዓተ ማኅሌት አይነቶች የለም። በክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት ዕለቱን የሚመለከት ወረብ ያለ ሲሆን በወርኃ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት ግን ሊቃውንቱ እየፈጠሩ ካልሆነ በቀር በወንበር የተቀመጠ ወረብ የለም። የእሁድ ሥርዓተ ማኅሌት የሚቆመው መዝሙር በመሆኑ ወረብ የለውም" (ሚያዝያ 17/09/2003፣ ካሴት ቁጥር፣5÷side 1)::

በትክሻ ላይ በመሸከም፣ በማስረገጥ በጭብጨባና በእልልታ የሚባል ነው፡፡ ምሳሌነቱም ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራኒዮ ሲጓዝ፣ የገሊላ ሴቶች ያለ ማቋረጥ እያለቀሱ መከተላቸውን አይሁድ ግን አሁንም ደጋግመው በእርግጫ እየተማቱ ደስ ብሎአቸው ሊሰቅሉት መስቀሉን አሸክመው ወደ ቀራኒዮ የመሄዳቸው ምሳሌ ነው (ሉቃ 23፡26-29)፤ በሌላም በኩል የአመላለሱና የወረብ አባባል ኃዘንና ደስታ የተቀላቀሉበት ገፅታ ያለው ነው፡፡ ኃዘኑ የመስቀል ምሳሌ የሆነው መቋሚያ መሸከም ሲሆን ደስታው ደግሞ ጭብጨባውና እልልታው ነው፤ ይህም የተፈጸመው ድርጊት አሳዛኝ ቢሆንም ድህነትን ያስገኘ በመሆኑ የምዕመናንን ደስታ ለመግለጽ የሚደረግ ነው፡፡

መምህር ዳንኤል አየነው የወረብን ስርዓተ ክዋኔ በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

> *ወረብ ምስጋና ሲሆን መዘምራኑና ምዕመናኑን አንድ የሚያደርግ ነው፡፡ ጣዕመ ዝማሬው ያለ ክበሮ እና ጸናጽል በግራና በቀኝ ከተመላለሰ (ንሺ) ከተደረገ በኋላ በመዘምራን አስረጋጮች ታጅቦ የሚከናወን ስርዓተ ክዋኔ ነው፡፡ ይህ በዝግታ የተጀመረ እንቅስቃሴ እየፈጠነ እና እየሞቀ ይሄድና ወደ ማሸብሸብ ይሄዳል፡፡ በወንበር የተቀመጠውን መሰረት በማድረግ እና ሌላም በመፍጠር ሊቃውንቱ ሲዘምሩ ምዕመናን በእልልታና ጭብጨባ ያጅባሉ በዚህ ሁኔታ ስርዓተ አገልግሎቱ ይከናወናል (ሚያዝያ 18/09/ 2003፣ ካሴት ቁጥር፣7÷side 2)::*

በአጠቃላይ ወረብ የመዘምራኑ እና የምዕመናኑ ተሳትፎ የሚጨምርበት ሥርዓተ ክዋኔ ሲሆን በተለይ ምዕመናን ሊቃውንቱ ሥርዓተ ማኅሌቱን ሲቆሙ ከሊቃውንቱ ጋር በእልልታና በጭብጨባ ይሳተፋሉ፡፡

### ሐ. አጽሕሶ

አጽሕሶ በጥንግ ድርብ ለባሾች እየታጀበ የሚዘመር የጣዕመ ዝማሬ እንቅስቃሴ ሲሆን ከወድያወዲህ እየተባለ በእግር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው (ማህበረ ቅዱሳን1993፡10)፡፡ አጽሐሶ የኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀሉ የሚታሰብበት እና ምስጢራዊ ትርጉም ያለው መሆኑን ጥዑመ ልሳን ካሳ እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

አጽሕሶ በምስጢር የተሞላ የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀሉን የሚያስታውስ እንጂ ለአይን ወይም ለተመልካች እንዲያስደስት ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ መዘምራኑ ወገባቸውን በቀሽ መሪ ታጥቀው ወደፊትና ወደኋላ እያሉ በእግርና በእጅ የሚፈጽሙት የአካል እንቅስቃሴ በምሳሌ ለማስረዳት ሲባል ነው፡፡ አጽሕሶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች መዳን ሲል በዕለተ ዓርብ የተቀበላቸውን ስቃዮች ዘርዝሮ የሚያስረዳ ተምሳሌታዊ ክዋኔ ነው፡፡ መዘምራኑ አንዱን ቀለም እየመላለሱ ማለታቸው አንዱን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘው አንድ ጊዜ ወደ ሐና፣ ሌላ

ጊዜ ከሐና ወደ ቀያፋ፣ ከቀያፋ ወደ ከተማው ገዥ ወደ ጲላጦስ፣ ወደ አውራጃው ገዥ ወደ ሔሮድስ ሲያመላልሱት ማደራቸውን ያመለክታል(1981፡262)፡፡

በአጽሕሶ ጊዜ መዘምራኑ መቋሚያቸውን ትክሻቸው ላይ አድርገው መሸከማቸው ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ የመጓዙ ምሳሌ ነው (ሉቃ 23፡22፤ ዮሐ 19፣17)፡፡ መዘምራኑ አንዳንድ ጊዜ እግራቸውን ወደ ላይ ብድግ እያደረጉ መርገጣቸው ጌታን ወደፊትና ወደኋላ እየጎተቱ ከመሬት እየጣሉ ለመርገጣቸው ምሳሌ ነው (ማህበረ ቅዱሳን 1993፡10)፡፡

በአንድ በኩል ያሉ አስረጋጮች ወደፊት ሲሄዱ በሌላ ወገን ያሉት ደግሞ ወደኋላ መመለሳቸው የአይሁድ ጭፍሮች በበዓላቸው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊይዙት ወደ አትክልቱ ስፍራ ወደ ጌቴ ሴማኒ ማንም ሳይነግረው እሱን ለመያዝ እንደመጡ አውቆ ወደ እነርሱ ወጥቶ "ማንን ትሻላችሁ አላቸው" እነርሱም "የናዝሬቱ ኢየሱስን" አሉት፤ እሱም እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ የቃሉ ግርማ አስፈርቷቸው ወደኋላ እየተፍገመገሙ በተደጋጋሚ ሶስት ጊዜ በምድር ላይ የመውደቃቸው ምሳሌ ነው (ማህበረ ቅዱሣን 1993፡10)፡፡

ከበሮው በዝግታና በኋላም በፍጥነት መመታቱ ነቢዩ ኢሳያስ "ጀርባዬን ለግርፋት ፊቴን ለጽፋት ሰጠሁ" ሲል ስለ ጌታ የተነበየው ትንቢት ይፈፀም ዘንድ ፊቱን በሻሽ ሸፍነው አምላክ ከሆንክ በጥፊ የመታህ ማነው ንገረን እያሉ መላልሰው በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው (ማህበረ ቅዱሣን 1993፡10)፡፡

መዘምራን መቋሚያቸውን ከትከሻቸው አውርደው ለሌላው ማቀበላቸው የጌታ መስቀል እርጥብና ከባድ ስለነበርና ድብደባ አብዝተውበት ስለነበር ሳይሰቅሉት እንዳይሞትባቸው ሲሉ አንድ መንገድ አላፊ (ስምዖን ቀሬናዊ የሚባል ሰው) አግኝተው የጌታን መስቀል ከትክሻው አውርደው እንዲሸከም የማስገደዳቸው ምሳሌ ነው (ማህበረ ቅዱሣን 1993፣10)፡፡

የክብረ በዓላት ሥርዓተ ዋዜማ አመላለስ፣ ወረብ እና አጽሕሶ የማይቀሩ ወሳኝ የስርዓቱ ክዋኔዎች በመሆናቸው እና የራሳቸው ተምሳሌታዊ ውክልና እንዳላቸው ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ውጤታማ የሚሆነው ከላይ የተዘረዘሩት የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ሲከወኑ ነው። በፎክሎር አንድ ሥርዓተ ክዋኔ ውጤታማ ነው የሚያሰኘው አጀማመሩ፣ ሂደቱ እና ፍጻሜው ተያያዥነት ሲኖረው ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ደረጃ(Step) በሥርዓተ ክዋኔው የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። ክዋኔ እንደ ወራጅ ውሃና እንደ ብረት ሰንሰለት ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ መከወን ግድ ይላል። ስርዓተ ክዋኔውን የሚከውኑ ከዋኞች እና ታዳምያንም ክዋኔው በሚፈቅደው ማዕቀፍ (Frame) ውስጥ መከወን ይኖርባቸዋል።

ሥርዓተ ክዋኔው ከተፈቀደው ማዕቀፍ ቢወጣ ሥርዓቱ ሊበላሽ እና ተምሳሌታዊ (ትዕምርታዊ) ውክልናውን ሊያጣ ይችላል። በመሆኑም የሥርዓተ ክዋኔው ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት መከወኑ ክዋኔውን ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል። ሥርዓተ ማኅሌትም እንደ አንድ ስነ ጥበብ የራሱ የሆነ የአከዋወን ስልትና ደረጃ ያለው በመሆኑ ሥርዓተ ክዋኔው በሚፈቅደው ማዕቀፍ (Frame) መሰረት ሲከወን ውጤታማ ይሆናል። ከጽሑፍም ሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች የሚያመላክቱትም ይህንን ነው።

## 5.3 የንዋያተ መዝሙራት ተምሳሌታዊ ውክልና

ሥርዓተ ማኅሌት ለመከወን ከበሮ፣መቋሚያ እና ጸናጽል እንደሚያስፈልጉ እና እነዚህም የራሳቸው ታሪካዊ አመጣጥ እንዳላቸው በምዕራፍ 2.2.9.1 ተመልክተናል። በዚህ ክፍል እነዚህ ንዋያተ መዝሙራት ያላቸው ተምሳሌታዊ ውክልና ምን እንደሆነ እንመለከታለን።

በፎክሎር እያንዳንዱ ቁስ የራሱ የሆነ ውክልና አለው። የቁሱን ውክልና ማወቅና መገንዘብ ካልተቻለ ፎክሎራዊ ገጽታውን መረዳት አይቻልም። ቁሶች የፎክሎርን ገጽታ አመላካች በመሆናቸው ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ውክልና ሊይዙ ይችላሉ። በሥርዓተ ማኅሌት እንደ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕት፣ ካባ፣ ላንቃ ፣ቀይ ሸመር ወዘተ የሚያስፈልጉ ቢሆኑም በዋናነት ግን ንዋያተ መዝሙራት (ከበሮ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል) ጉልህ ድርሻ አላቸው። ያለ እነሱ ሥርዓተ ማኅሌትን መከወን አይቻልም። ከዚህም የተነሳ ተምሳሌታዊ (ትዕምርታዊ) ውክልናቸው የጎላ ይሆናል። ቀጥሎ የንዋያተ መዝሙራት አሰራር እና ተምሳሌታዊ ውክልናቸውን እንቃኛለን።

### 5.3.1 ከበሮ

ከበሮ አንድም ከእንጨት፣ ከብር፣ ከነሀስ እና ከከብት ቆዳ የሚሰራ ሲሆን ዙሪያው ሱቲ (ጨርቅ) በማልበስ ላዩ በጥልፍልፍ ጠፍር የተጠፈረ ነው። ከበሮ በብሉይ እና በሐዲስ

ኪዳን አገልግሎት ይሰጣል (1ኛ ሳሙ 15÷20፡ 1ኛ ሳሙ 18÷6-7፤ 2ኛ ሳሙ 6÷5፤ መዝ 80÷2፤ መዝ 150÷4።

ከበሮ በአንዱ ሰፋ ያለ ሲሆን በሌላው ጎኑ ደግሞ ጠበብ ብሎ ሞላላ ቅርጽ ያለው ነው። በሁለቱ ጎኖች መካከል ቆዳው ይወጠርና በውስጡ ጠጠሮች ይሞላል። ከበሮ ስፋትና ክብደት ካላቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው። ከበሮ በሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ በዓቢይና ንዑስ መረግድ፤ በጽፋት እና ሽብሻቦ ጊዜ የሚያገለግል ሲሆን አመታቱም ቁጭ ተብሎ እና ተቁሞ ሊሆን ይችላል።

ከበሮ ቁጭ ብሎ (በቁምና በዐቢይ መረግድ ጊዜ) ወይም ቆመው (በሽብሸባ ጊዜ) ወይም ወዲህና ወድያ እየተመላለሱ ትክሻቸው ላይ በማንገት ሁለት ጊዜ በግራ እጅ ጠባቡ ጎን ተመትቶ ወድያው በማስከተል በቀኝ በኩል ይመታል። ሰፊው ክፍል በሙሉ በመዳፍ የሚመታ ሲሆን ጠባቡ ጎን በግራ እጅ አራቱ ጣቶች ነካ እየተደረገ በስሱ ይመታል። ሰፊው ክፍል ጠበቅ ተደርጎ በሐይል ሲመታ ጠባቡ ግን በስስ መልኩ በዝግታና በቀስታ ይመታል። ለማኅሌት የሚመታው ከበሮ ከሀገረሰባዊ ጭፈራና ሌሎች አጋጣሚዎች ጥቅም ላይ ከሚውሉት ከበሮዎች የተለየ ነው። ልሳነ ወርቅ ገ/ጊዮርጊስ (1997÷XXX-XXXI)።

መምህር ዮሐንስ ግርማ የከበሮን ተምሳሌት እንደሚከተለው አብራርተዋል።

> *ከበሮ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። የከበሮው ሰፊ ገጽ የመለኮት ስፍሁነት፣ ጠባብ ገጽ የስጋ ውሱንነት፤ ከበሮው የተጠፈረበት ጥልፍልፍ ጠፈር የጌታችን የግርፋቱ ሰንበር፤ ጨርቁ የመግነዙ፣ የከበሮው ማንገቻ ታስሮ የተጎተተበት ወይም ለተገረፈበት ጅራፍ ምሳሌ ነው። በውስጡ ያሉ ጠጠሮች አይሁድ ጌታን ሲገርፉት ገበጣ ለተጫወቱበት ጠጠር ምሳሌ ሲሆን ሁለቱ ሰፊው እና ጠባቡ ገጾች በአንድ ላይ መገኘታቸው ደግሞ የተዋህዶ ምሳሌ ነው። ከግራና ከቀኝ መመታቱም ጌታ በጥፊ የመመታቱ ምሳሌ (ሚያዝያ 17/09/2003/ 2003፣ካሴት ቁጥር፣5÷side 2)::*

ከላይ ከተገለጹት የመምህራን ሐሳብ መረዳት የሚቻለው ከበሮ[19] ሥርዓተ ማኅሌትን ለማከናወን ወሳኝ ከሆኑ ንዋያተ ማሕሌት ውስጥ አንዱ ሲሆን ተምሳሌታዊ ውክልናውም ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ጋር የተያያዘ ነው።

---

[19] የከበሮን ተምሳሌታዊ ውክልና ሊቀ ትጉሃን ሞላ ሐሳባቸውን እንደሚከተለው አብራርተዋል። "ከበሮ ተምሳሌቱ የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ድምፁ የደምጸ መላእክት ምሳሌ፤ ጠፈሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የታሰረበት ገመድ ምሳሌ፤ ከበሮ በፊትና በኋላ መመታቱ ቤተ አይሁድ "ተነበይለነ ክርስቶስ መኑ ጸፍዐከ መልታሕቴከ?" (እስኪ አሁን ትንቢት ተናገር ፊትህን የመታህ ማን ነው?) እያሉ በጥፊ የመምታታቸው ምሳሌ ነው።"(ሚያዝያ19/09/203፣ካሴት ቁጥር፣1÷side 1)::

ከጽሑፍ የተገኙ መረጃዎችም ከበሮ[20] ተምሳሌታዊ ውክልና እንዳለው ያስረዳሉ።

ከበሮ ከግራና ከቀኝ (በትንሹና በትልቁ በኩል) መመታቱ ጌታ በህጻናትና በትላልቅ ሰዎች በግራና በቀኝ መመታቱን ለማዘከር፣ ማንገቻው የተገረፈበት የጅራፍ፣ የጠፈሩ ጥልፍልፍ ሲገረፍ የወጣለት ሰንበር (ምልክት)፣ ቀይ ግምጃው ቀይ ከለሜዳ የመልበሱ፣ ውስጡ ባዶ መሆኑ የመቃብሩ ምሳሌ ነው (ዘ15÷20፤ መዝ 150÷4፤80÷2፣ 149÷3፤2ኛ ሳሙ 6÷5 (ማህበረ ቅዱሳን 1993፡10)።

ከበሮ ካለው ከፍተኛ የድምጽ አወጣጥ የተነሳ መዝሙርን ያደምቃል፣አእምሮን ይማርካል፣ የካህናቱም ሆነ የምዕመናኑን ቀልብ ይስባል።

በአጠቃላይ ከመስክም ሆነ ከጽሑፍ የተገኙት መረጃዎች የሚያመላክቱት ከበሮ ለስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ከሚውሉ ንዋያተ መዝሙራት አንዱ ሲሆን የራሱ የሆነ ተምሳሌታዊ ውክልና አለው። የከበሮ ተምሳሌታዊ ውክልና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተያያዙ ሲሆን ሁሉም የከበሮ ክፍሎች የኢየሱስ ክርስቶስ ነገሩ መስቀሉን አመላካች ናቸው። በመሆኑም በኦርቶዶክሳዊያን ዘንድ ከበሮ እንደ ማንኛውም ለጭፈራ የሚውል ቁስ ሳይሆን ሐይማኖታዊና መንፈሳዊ ትርጉም ያለው ተደርጎ ይታመናል። ከበሮ በስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ያለው አስተዋፅኦ(ፋይዳ) ከፍተኛ ነው። በፎክሎር ቁሶች የአንድ ህዝብ እምነት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ማህበራዊ ኑሮ አመላካች ናቸው። ከዚህ አንጻር ከበሮ

---

[20] ዘወንጌል ገ/ኪዳን እና ሌሎች የከበሮን ተምሳሌታዊ ውክልና እንደሚከተለው ያብራሩታል።
ከበሮ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን የከበሮው እንጨት የሚለብሰው ጨርቅ ጌታን አይሁድ በዕለተ ዓርብ ያለበሱት የከለሜዳ ምሳሌ ሲሆን በጨርቁ ላይ የሚታየው ግራና ቀኝ ያለው የከበሮውን አፎች ወጥሮ የያዘ ጠፍር በዕለተ ዓርብ ጌታ ሲገረፍ በሰውነቱ ላይ የታየው የሰንበር ምልክት ነው። በግራና በቀኝ የሚታዮት ትንሹና ትልቁ የከበሮውን አፎች ስንመለከት ትንሹ የትስብእት፣ ትልቁ ደግሞ የመለኮት ምሳሌዎች ናቸው። ትንሹን የከበሮው አፍ የስጋን ውሱንነት ሲገልጹ፣ ትልቁ ደግሞ የመለኮትን ስፍሁነትና ምሉዕነት ይገልጽልናል። ሁለቱ አፎቹ በጠፍሩ አማካይነት መያያዛቸው እና አንዱ ከበሮን ማስገኘታቸው መለኮትና ትስብእት፣በተዋሕዶ አንድ አምላክ መሆኑን ያስረዳናል። ጠፍሩም የተዋሕዶ ምሳሌ ነው። ከበሮውን ለማንጠልጠል የሚረዳን ገመድ ደግሞ ጌታ በዕለተ ዓርብ የተገረፈበት የጅራፍና የእንግሪግሪት የታሰረበት ገመድ ምሳሌ ነው። የከበሮው አመታትም መጀመሪያ ሲጀመር ዝግ ብሎ እየተቆጠረ ይጀመርና በኋላ እየፈጠነ እየፈጠነ በመሄድ ለመቁጠር በማይቻል ሁኔታ ምቱ እየተለወጠ ይሄዳል። ይህ የአመታት ስርዓት የጌታን በጥፊ መመታት ይገልጻል። አይሁድ በህጋቸው የሚሰቅሉትን አርባ አይገርፉትም፣ አርባ የሚገረፉትንም አይሰቅሉትም። ስለዚህ ጌታን ገርፈው ለመስቀል መጀመሪያ ግርፋቱን ሲጀምሩ አርባ እንዲሞላ እየቆጠሩ መግረፍ ጀምረው ነበር። በኋላም ቁጥሩን በማሳሳት እየተፈራረቁ ብዙ ገርፈውታል። ከዚያም መቁጠሩን ትተው በጣም ለቁጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ገርፈውት ስለነበር የከበሮው ምትም እየፈጠነ በመሄዱ ለቁጥር አስቸጋሪ የሆነበት ፍጥነት ላይ መድረሱ ይህንን የጌታን መመታት ለማስታወስ ነው። በወረብ መዝሙሩ በታላቅ ተመስጦ ለየት ባለ መንፈሳዊ ስሜት በሚዘመርበት ጊዜ ከበሮውን እየመቱ ዕንባቸውን እንደ ውሃ የሚያፈሱ አባቶች አሉ። ይህ የአባቶች ለቅሶ በዕለተ ዓርብ የጌታን ሕማምና መከራ እያዩ እያለቀሱ ይከተሉት ከነበሩት የገሊላ ሴቶች ጋር እንዲደመሩ ያደርጋቸዋል። ምሳሌውን አይተው አማናዊውን አስታውሰው አልቅሰዋልና (1996÷17-18)።

በኦርቶዶክሳውያን አማኞች ዘንድ መንፈሳዊና ሐይማኖታዊ ትርጉም ያለው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡



ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የሚውል ከበሮ

## 5.3.2 መቋሚያ

መቋሚያ ዘንጉ ከእንጨት፣መደገፊያው፤ ከብረት፣ ከእንጨት ከነሐስ እና ከወርቅ ሊሰራ ይችላል፡፡የመቋሚያው ራስ ቀርነ በግዕ (የበግ ቀንድ ቅርጽ) መሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ መሆኑን ይገልጻል(ዮሐ1÷29)፡፡

መቋሚያ ድምጽ አልባ ንዋየ መዝሙር ሲሆን አገልግሎቱም በዋናነት የዜማውን ሂደት እና ዝማሜ ለመምራት፣ ለማስረገጥ ፣ለምርኩዝነት ወይም ለድጋፍ የሚውል ነው፡፡

መምህር ዳንኤል አየነው "መቋሚያ በስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ ቀለምን ለመምራት እና ለመደገፊያነት ያገለግላል፡፡ሙሴ ባሕረ ኤርትራን በሐይለ እግዚአብሔር ከፍሎ ሕዝበ እስራኤልን በደረቅ ባሻገረ ጊዜ ተአምራት ያደረገበት በትር ምሳሌ ነው፡፡" (ሚያዝያ18/09/ 2003፣ ካሴት ቁጥር፣7÷side 2) በማለት ገልጸዋል::

ሊቀ ትጉሃን ፀዳል ካሳው የመቋሚያን ተምሳሌታዊ ውክልና በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል::

"መቋሚያ የጌታችን ምሳሌ ነው፡፡ መዘምራን በዝማሜ ጊዜ መቋሚያ መጠቀማቸው ቤተ አይሁድ መኑ ኰርዐከ ተነበይለነ ክርስቶስ? (እራስህን በዘንግ የመታህ ማንነው እስኪ ንገረን?) እያሉ በዘንግ እራስ እራሱን የመቀጥቀጣቸው ምሳሌ፡፡" (ሚያዝያ 19/09/2003፣ ካሴት ቁጥር፣10÷side 1) ፡፡ ከላይ ከተገለጹት የመስክ መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው መቋሚያ ቃለ እግዚአብሔር ለመምራት፣ ለመደገፊያነት እንዲሁም ለማስረገጥ የሚውል መሳሪያ ሲሆን ተምሳሌቱም ከኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀል ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡



ለስርዓተ ማሕሌት ክዋኔ የሚውል መቋሚያ

### 5.3.3. ጸናጽል

ጸናጽል ከወርቅ፣ ከብር፣ከነሐስ ወይም ከብረት የሚሰራ ንዋየ መዝሙር ነው፡፡ አሰራሩም ከግራና ከቀኝ ሁለት አምዶች፣ ከመሐል ሁለት ቀጫጭን ጋድሞች፣ ከአናቱ ላይ ቀስተ ደመና፣ መሐል ካሉት ሁለት ጋድሞች ላይ በአንደኛው ሶስት በሁለተኛው ሁለት ሻኩሪዎች ያሉት ሆኖ ከስር መጨበጫ (እጀታ) አሉት (2ኛ ዜና 29÷25፤2ኛ ዜና 5÷15፤2ኛ ሳሙ 6÷5)፡፡

የጸናጽልን ተምሳሌታዊ ውክልና በተመለከተ ቃለ መጠይቅ ካደረኩላቸው መምህራን አንዱ መምህር ዮሐንስ ግርማይ የሚከተለውን ሐሳብ ገልጸዋል።

> *ጸናጽል የራሱ የሆነ ተምሳሌት አለው። ሁለት ግንዶች ተደርጎ መሰራቱ አንዱ ሲስበው ሌላው ይጥለዋል፣ ሌላው ሲጥለው አንዱ ይሰበዋል ይኸውም ቤተ አይሁድ ጌታን ከዚያና ከዚህ፣ ወደኋላና ወደፊት የማንገላታታቸው እና የማጋጨታቸው ምሳሌ ነው፡፡ የጸናጽሉም ድምጽ እንደዚሁ ነው፡፡ ጸናጽል ከታች መያዣው አንድ ሆኖ ሁለት ባላ መኖሩ አምላክ አምላክነቱ ሳይለቅ ሰው የመሆኑ ምስጢር (ምሳሌ) ነው፡፡ በጸናጽሉ ውስጥ ቅጠሎቹ አምስት መሆናቸው ጌታ 5,500 ዘመን ሲፈጸም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው የመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡ አንድም ቅጠሎቹ አምስት መሆናቸው የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ነው፡፡ ጸናጽል ላይና ታች አንድ፤ጎንና ጎን አንድ መሆኑ እና በመሐል ደግሞ ክፍተት መኖሩ እስራኤላውያን ላዩ እንዳለ፣ ጎናጎኑ ውሃ፣ መሐሉ ክፍት ሆኖ ባህረ ኤርትራን የመሻገራቸው ምሳሌ ነው፡፡ አንድም ለብሉይና ለሐዲስ መሰረቱ ክርስቶስ መሆኑ ለማጠየቅ፣ አንድም ጸናጽል የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው (ሚያዝያ17/09/2003 ፣ካሴት ቁጥር፣5÷side 2)፡፡*

ሊቀ ትጉሃን ሞላ “ጸናጽል እግዚአብሔር የሚመሰገንበት መሣሪያ ነው፡፡ ምሳሌው የእመቤታችን የድንግል ማርያም ለቅሶ ሲሆን ዜማው ሐዘን ነው፡፡ አቋቋሙ የዜማ ማጣፈጫ ሐዘን ነው፡፡” (ሚያዝያ19/09/ 2003፣ ካሴት ቁጥር፣1÷side 1) በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት የመምህራን ሐሳብ መገንዘብ የሚቻለው ጸናጽል[21] ለሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ከሚያስፈልጉ ንዋያተ መዝሙር አንዱ ሲሆን ተምሳሌቱ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ከእናቱ ድንግል ማርያም ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን ነው፡፡ የጸናጽል ድምጽ አወጣጡ የማሕሌቱን ክዋኔ እንዲደምቅ ከማድረጉም በላይ የካህናቱ እና የምእመናኑን ቀልብ ይስባል፡፡ከዚህም በተጨማሪ መዝሙር ሲዘመር እና ሲሸበሸብ ለጆሮ ልዩ ስሜት የሚሰጥ በመሆኑ ኪነ-ጥበባዊነቱ የጎላ ነው፡፡ከላይ ከተገለጹት የመስክ ሆነ የጽሁፍ መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው ጸናጽል እግዚአብሔርን ለማመስገን እና የዜማውን እንቅስቃሴ እና ቀለም ለመምራት የሚያገለግል ሲሆን ከድንግል ማርያም እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በተያያዘ ተምሳሌታዊነቱ የጎላ መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው ንዋያተ መዝሙር ሥርዓተ ማኅሌትን ለመከወን በዋናነት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ሲሆኑ ሁሉም የየራሳቸው ተምሳሌታዊ ውክልና የያዙ ናቸው፡፡ በፎክሎር እያንዳንዱ ቁስ የሚወክለው ነገር አለ፡፡ ውክልናው ሐይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም ንዋያተ መዝሙራት ሐይማኖታዊ ውክልና አላቸው፡፡ በመሆኑም በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ለእግዚአብሔር ብቻ መገልገያ በመሆናቸው ተምሳሌታዊ ፋይዳቸው የጎላ ነው፡፡

## 5.4 የሥርዓተ ማኅሌት ተግባራት

ሥርዓተ ማኅሌት በመዘምራንና እና በምዕመናን ተሳትፎ የሚከወን መንፈሳዊ ስነ-ጥበብ ነው፡፡ ይህ ስነ-ጥበብ ደግሞ የራሱ ተግባራት አሉት። ሥርዓተ ማኅሌት ፎክሎራዊ ከሚያስብሉት ገጽታዎች ተግባራቱ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

---

[21] ዘወንጌል ገ/ኪዳንና ሌሎች ስለ ጸናጽል ተምሳሌታዊ ውክልና የሚከተለውን ሐሳብ አስፍረዋል፡፡
ጸናጽል የኪዳነ ኖህ ምሳሌ ነው፡፡ የጸናጽሉ ጫፍ ስንመለከት የቀስተ ደመና ቅርጽ ያለው ከሁለት ብረቶች የግራና ቀኝ ጫፍ ጋር የተያያዘ ብረት እናገኛለን፡፡ ይህ የቀስተ ደመና ቅርጽ ያለው ብረት ልዑል እግዚአብሔር ለኖህ ምድርን ዳግመኛ በንፍር ውሃ እንዳያጠፋት ቃል ሲገባለት የሰጠው የቃል ኪዳን ምልክት ምሳሌ ነው፡፡ በጸናጽሉ ላይ ያሉት አራት ዘንጎች የአራቱ ባህርያተ ስጋ (ውሃ፣ነፋስ፣ እሳት እና መሬት) ምሳሌዎች ሲሆኑ ድምጽ የሚያሰሙ ቅጠሎች ደግሞ የፍጥረተ ዓለም (የ22ቱ ስነ ፍጥረት) ምሳሌዎች ናቸው። በፀናጽል መዝሙር መዘመራችን ደግሞ አምላካችን ሆይ ለኖህ የገባህለትን ቃል ኪዳን አስበህ ማረን፣ ዘወትር ይቅርታህ ቸርነትህ ፈጥኖ ይደረግልን ብለን መለመናችን ነው፡፡

አንድም ጸናጽል አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያያት የወርቅ መሰላል ምሳሌ ነው። ዘፍ 28÷5-17፡፡ ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያያት ሰማይና ምድርን ሰውና እግዚአብሔርን ያገናኘኘችው አማናዊት ሰዋሰው ወርቅ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያየሽ የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ እንዲል አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም፣ ስለዚህ ጸናጽል የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በጸናጽሉ ግራና ቀኝ የሚታዩት ጋድሞች የመሳሰሉ መውጫና መውረጃ ምልክቶች ምሳሌ፣ በጋድሞቹ ላይ ተንጠልጥለው የሚታዮ ቅጠሎች በመሰላሉ ሲወጡና ሲወርዱ የነበሩት የቅዱሳን መላእክት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አንድም የግራና የቀኝ ዘንጎች (ቋሚዎች) የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ወይንም የፍቅረ እግዚአብሔር እና የፍቅረ ቢጽ ምሳሌዎች ሲሆኑ የተንጠለጠሉት ቅጠሎች ደግሞ የአዋልድ መጻህፍት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የቅጠሎቹ ብዛት አምስት ከሆነ የአምስቱ አዕማደ ምስጢራት፣ ስድስት ከሆነ የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ ነው፡፡ በጸናጽል መዘመራችን አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ በምሳሌ ያየሽ አማናዊት የወርቅ መሰላል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልመናችንን ወደ ልጅሽ መንበር አሳርጊልን ብለን መለመናችን ነው (1996፡20-22)፡፡

ፎክሎር የራሱ መሰረታዊ ተግባራት አሉት እነዚህም፡- የማስተማር፣ የመቆጣጠር፣ ባህልን የማቆየት፣የማምለጥ፣ ተግባራት ናቸው (Bascom 1986፣36፤ Sims እና Stephens 2005÷17 ፤Elliott Oring 1976÷63)::

ሥርዓተ ማኅሌትም የራሱ ተግባራት አሉት። የሥርዓተ ማኅሌትን ተግባራት በሁለት ወገን በመመደብ ማጥናት ይቻላል። አንደኛው በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት የመጡ ቀጥተኛ ተግባራት ሲሆኑ ሁለተኛው ሰበበ ማሕሌት (በተዘዋዋሪ) የመጡ የማሕሌት ተግባራት ናቸው።

### 5.4.1 ሐይማኖታዊ ተግባር

በክበረ በዓል የሚከናወን ሥርዓተ ማኅሌት የመከበር አላማውን መነሻ የሚያደርገው ሐይማኖታዊነቱን ነው። በመሆኑም ክብረ በዓሉ በካህናት፣ መዘምራን እና ምዕመናን ተሳታፊዎች በድምቀት ይከበራል። ምዕመናኑም ሆኑ መዘምራኑ እንቅልፍ አጥተው፣ የግል ሥራቸውን ትተው ሌሊቱን ሙሉ የሚቆሙት ማኅሌት ሐይማኖታዊ ፋይዳ ስላለው ነው።

የማኅሌት ሐይማኖታዊ ተግባርን በተመለከተ ቀሲስ ሐይሉ አምባየ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

> *በማኅሌት በቅድሚያ የሚመሰገነው እግዚአብሔር ሲሆን ቅዱሣን፣ ሰማዕታት፣ ፃድቃንም ይመሰገኑበታል። በዚህ ስርዓተ አገልግሎት ፍጹም መንፈሳዊ ሐሴትና ደስታ በማድረግ መዘምራን፣ ካህናትና ምዕመናን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። እግዚአብሔርን ማመስገን ደግሞ አንዱና ዋነኛ የሐይማኖት መገለጫ ነው። ሌላው ማኅሌት ሃይማኖታዊ ተግባር አለው የሚያሰኘው ለአገልግሎቱ የሚውሉ ንዋያተ መዝሙር ናቸው። ማሕሌት በረከተ ስጋና በረከተ ነፍስ የሚያስገኝ ነው። ይህም ሌላው ሐይማኖታዊ ተግባር ነው። ከሁሉም በላይ ግን የእምነቱ መስራችና ባለቤት የሚመሰገንበት መለኮታዊ ስራዎቹ የሚነገሩበት በመሆኑ ማኅሌት ሐይማኖታዊ ያሰኘዋል። በማኅሌት የነፍስ ስራ እንጂ የስጋ ስራ አይከናወንም የሐይማኖታዊ በዓላት አንዱ መገለጫ ደግሞ መንፈሳዊነት ነው (ሚያዝያ19/09/2003፣ ካሴት ቁጥር6፣side1)።*

ሥርዓተ ማኅሌት ሐይማኖታዊ ፋይዳ (ተግባር) አለው የሚያሰኘው የእምነቱ ተከታዮች ሥርዓተ አምልኳቸውን የሚፈጽሙበትና መንፈሳዊ ተግባራት የሚያከናውኑበት በመሆኑ ነው። ሥርዓተ ማኅሌት በክብረ በዓላት የሚከናወን በመሆኑ የክብረ በዓሉን ገጽታ ይይዛል። በዓላትም ደግሞ የእምነት መገለጫዎች ናቸው። ብርሃኑ አድማስ የበዓላትን አከባበር ሲገልጽ "በዓላት በመሰብሰብ፣ በመማር፣ የቅዱሳኑን ገድል በመስማት፣ በመመጽወት፣ በመጸለይ፣ መንፈሳዊ ደስታን በመደሰት የሚከበሩ ናቸው" (2002፣137) በማለት ገልጿል።

ምዕመናንም ሆነ ካህናት ነጭ ልብስ በመልበስ፣ የጸሎት መጻሕፍት፣ መቋሚያና መሰል መንፈሳዊ መሣሪያዎችን በመያዝ ሥርዓተ ማኅሌቱን ያከናውናሉ። በሥርዓተ ማኅሌቱ ውስጥ የሚተላለፉ መልእክቶች፣ የሚዘመሩ መዝሙሮች፣ የሚቆሙ መልክዓ መልኮች በአጠቃላይ ሐይማኖታዊ ይዘት ያላቸው እንደሆኑ መረዳት ይቻላል።

### 5.4.2 ማህበራዊ ተግባር

በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ምክንያት የማይተዋወቁ ምዕመናን ይተዋወቃሉ፣ ከዚህ በፊት በአንድ ያላገለገሉ ሊቃውንት በአንድነት ያገለግላሉ። ይህን ማህበራዊ መቀራረብ ያመጣው ደግሞ ሐይማኖት ነው። የፎክሎር ጥናት አንድ ገጽታው ሐይማኖት እና በሃይማኖት ሰበብ (ምክንያት) የሚፈጠሩትን ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳዎች መመርመር ነው። ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌት ለእምነቱ ተከታዮች ሐይማኖታዊ ተግባር አለው ይባል እንጂ በበዓሉ ምክንያት የሚፈጠሩ በርካታ ማህበራዊ ግንኙነቶችንም የያዘ ነው። ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌት ለማህበራዊ ግንኙነት መፈጠር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የጎላ ነው።

ስለ ሥርዓተ ማኅሌት ማህበራዊ ተግባር ቃለ መጠይቅ ያደረኩላቸው ወ/ሮ ዝማም ደምወዜ የሚከተለውን ሐሳብ ሰጥተዋል።

> *ምዕመናን ወደ ቤተክርስቲያን የምንገሰግሰው እግዚአብሔርን ለማመስገን እና ሐጢያታችንን እንዲሰረይልን ነው። ማሕሌት ደግሞ አገልግሎቱ እጅግ ደስ ይላል። ክብረ በዓል ሲሆን በተለይ የካህናቱ፣ የመዘምራኑ እና የምዕመናኑ ብዛት እንዲሁም እርስ በርስ ያለው መቀራረብ በጣም ጥሩ ነው። በስርዓተ አገልግሎቱ ለመሳተፍ ከመኝታችን የተነሳ ከዋዜማው ጀምሮ በጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን። በመንገድም እንደምን ዋልሽ? እንደምን አደርሽ? እንባባላለን፣ በቤተ ክርስቲያንም ቢሆን አብረን እንዘምራለን፣ አብረን እልል እንላለን። ጧት ታቦት ሲነግስ ደግሞ የበለጠ በጋራ በመሆን በደስታ በዓሉን እናከብራለን። ከንግሱ በኋላ ለምሳሌ ትናንት ሚያዝያ ጊዮርጊስ ነበር፤ የገጠሩ አካባቢ ክርስቲያኖች ጸበል ጸዲቅ አዘጋጅተው የከተማውን ህዝብ በሚገባ አስተናግደዋል። በዚህ ምክንያት የማንተዋወቅ ሰዎች ተዋውቀናል፣ ከመተዋወቅም አልፎ በደስታና በኃዘን እንድንጠያየቅ በር ይከፍታል። የዛሬ 4ት ዓመት የጊዮርጊስ በዓለ ንግስ ለማክበር ሄጄ በበዓሉ ምክንያት የተዋወቅኳቸው ሰዎች ዛሬ እጅግ ዝምድና ፈጥረን ቤተሰብ ሁነናል። ማሕሌት በስጋም በነፍስም ጥቅም አለው። ማህበራዊ ግንኙነት እንድንመሰረት፣እርስ በርስ እንድንረዳዳ ያደርገናል።አይደለም እኛ ኢትዮጵያውያን ይቅርና የውጭ ቱሪስቶች እንኳ በዓሉን ለማየት በመምጣታቸው ምክንያት ከኢትዮጵያውያን ጋር ይተዋወቃሉ( ሚያዝያ 24/09/2003፣ካሴት ቁጥር 10፣side1)።*

Jerome ክብረ በዓል በተመሳሳይ ሐይማኖት ያሉ ሰዎችን የጠበቀ መተሳሰር በመፍጠር ህብረት እንዲኖራቸው ያደርጋል(1972፡167) በማለት የገለጸው ሐሳብ የወ/ሮ ዝማም ሐሳብን ያጠናክራል። ስለዚህ በሥርዓተ ማኅሌት ምክንያት የተመሰረቱ ማህበራዊ ግንኙነቶች እያደጉና እየጠነከሩ ሲመጡ ይበልጥ እርስ በርስ በኃዘን፣ በደስታ፣ በሰርግ፣ በእርቅ፣ በሽምግልና የመቀራረብ፣ የመዋሃድ ዕድል ይፈጥራል። በአጠቃላይ ሥርዓተ

ማኅሌት በአንድ ሐይማኖት ያሉ ሰዎች ማህበራዊ ኑሮን እንዲመሰርቱ የሚያደርግ ስነ ጥበብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከመስክም ሆነ ከጽሑፍ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ተግባር የሚያረጋግጡ ናቸው። በመሆኑም ሥርዓተ ማኅሌት በአማኞቹ ዘንድ የእሴትና የስነ-ምግባር ልውውጥ እንዲያደርጉ በማገዝ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያሳድጋል።

አጥኚው በበዓለ ትንሳኤና በሚያዝያ ጊዮርጊስ ክብረ በዓላት ላይ ተገኝቶ እንዳስተዋለው በሥርዓተ ማኅሌት የተሳተፉ ክርስቲያኖች የተለያየ ቋንቋ፣ የተለያየ ባህል፣ የተለያየ የእድሜ ክልል እንዲሁም የተለያየ አካባቢ (ከገጠርና ከከተማ የመጡ) ሰዎች በጋራ ሲያገለግሉ፣አብረው ሲበሉ፣ አብረው ሲጠጡ፣ አብረው ሲወያዩ ተመልክቷል።

### 5.4.3. ባህላዊ ተግባር

ሥርዓተ ማኅሌት በቤተ ክርስቲያን በቅኔ ማሕሌት የሚከናወን አገልግሎት ነው። በክዋኔው የሚሳተፉ አካላት ደግሞ ከዋዜማው ጀምረው ነጭ ልብስ በመልበስ በቤተ ክርስቲያኑ ይሰበሰባሉ። በዕለቱ የተመረጠው ወረብ ሲወረብ ካህናት በማስረገጥ ምዕመናን በእልልታና በጭብጨባ ሥርዓቱን በደመቀ ሁኔታ ያከናውኑታል። ጭብጨባው፣ ሽብሸባው፣ እልልታው እና የከበሮው አመታት እጅግ ፍጥነት የተሞላ በመሆኑ ወደ እስክስታ ይጠጋል። እስክስታ መምታት ደግሞ ባህላዊ ገጽታ አለው። በበዓለ ትንሳኤም ሆነ በሚያዝያ ጊዮርጊስ አጥኚው ይህንን ተግባር አስተውሏል።

የሥርዓተ ማኅሌት ባህላዊ ፋይዳ በተመለከተ ቀሲስ ሐይሉ አምባዬ የሚከተለውን አብራርተዋል።

> *በጥምቀት የሚከወነው ማኅሌት ስሜታዊነት ይታይበታል። ታቦቱን በሥርዓት በማጀብ እግዚአብሔርን ማመስገን ሲገባ ክበር መነጣጠቅ፣ እስክስታ መምታት በካህናቱ ይታያሉ። የከበሮው አመታትም ከቤተ ክርስቲያን ወጣ እያለ ይሄድና ዓለማዊ(ስጋዊ) ይዘት ይይዛል። ማኅሌት ከዚህ አንጻር ካየነው ባህላዊ ይዘት አለው ልንል እንችላለን። በአለባበስም ከወሰድን ባህላዊነቱ ይጎላል። በተለይ በጥምቀት በዓል ብዙ ወንዶችም ሆነ ሴቶች ባህላዊ አልባሳት ለብሰው፣ ባህላዊ መሣሪያዎች ይዘው እና በባህላዊ አጊያያጥ አጊጠው ወደ ጥምቀተ ባህሩ ይመጣሉ (ሚያዝያሚያዚያ 19/09/2005፣ ካሴት ቁጥር 6፣side 1)።*

መርጌታ ንጉስ ሃፍቱ የማሕሌትን ባህላዊ ተግባር እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> *ለሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ከተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ሰዎች ይመጣሉ። እነዚህም ሰዎች በበዓለ ንግሱ የተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎች እና እንቅስቃሴዎች ያደርጋሉ። ለታቦቱ ይዘፍናሉ፣ ይጨፍራሉ። ባህላዊ እስክስታዎች ያቀርባሉ። ካህናትና መዘምራንም ቢሆኑ ዝማሬው እየደመቀ ሲሄድ ወደ ባህላዊ ዝማሜ ያዘነብላሉ። አንዳንድ መርጌታዎች ደግሞ በወረብ ጊዜ እስክስታ የሚያወርዱ አሉ። ማሕሌት ሐይማኖታዊ ገጽታ እንዳለው ሁሉ ባህላዊ ገጽታም አለው (ሚያዝያ-ሚያዚያ 21/09/2003፣ካሴት ቁጥር3፣side 1)።*

ከአቶ ንጉስ አገላለጽ መረዳት የሚቻለው በሥርዓተ ማኅሌት ክብረ በዓል ሰበብ ዘፈንና ጭፈራ መኖራቸውን ነው። እነዚህ ድርጊቶች ጎልተው የሚታዩት በታቦተ ንግሱ ወቅት ነው። ምዕመናን ለእነዚህ ባህላዊ ክዋኔዎች በእጅጉ የተጋለጡ ሲሆኑ ከመዘምራንም ይህንን ድርጊት የሚያከናውኑ እንዳሉ መረዳት ይቻላል።

በአጠቃላይ ማኅሌት መንፈሳዊ ዝማሬ እና ምስጋና ቢሆንም በሥርዓተ ክዋኔው ግን ባህላዊ ተግባራት ይታያሉ። ሀገረሰባዊ ጭፈራዎች፣ ውዝዋዜዎች፣ እስክስታዎች እና ዘፈኖች ይከናወናሉ። እነዚህ ደግሞ የፎክሎርን ባህላዊ ተግባር አመላካች ናቸው። የፎክሎር አንዱ የትኩረት አቅጣጫ በአንድ ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ የሚፈጸሙ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን፣ ዘፎኖች እና ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መመርመር ነው። ባህላዊ ጭፈራዎች፣ ዘፈኖችን እና እስክስታዎች ኪነ ጥበብን ከአንድ ዘመን ወደ ሌላ ዘመን ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ እንዲተላለፍ አሻራ ጥለው የሚያልፉ ናቸው። በሥርዓተ ማኅሌት ሰበብ ምክንያት የሚደረጉ ባህላዊ ጭፈራዎች ለኪነጥበቡ ማደግ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌት ባህላዊ ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

### 5.4.4 የማዝናናት ተግባር

ማዝናናት አንዱ የፎክሎር ተግባር ነው። ማዝናናትም በአንድ ሥርዓተ ክዋኔ ውስጥ እርካታ ማስገኘት ማለት ነው። የሥርዓተ ክዋኔው ተሳታፊዎች አእምሯዊ፣ ስጋዊ እና መንፈሳዊ ተዝናኖትን የሚያገኙበት ነው።

በማኅሌት መዘምራኑም ሆነ ምዕመናኑ እርካታ ያገኛሉ። ከደስታቸው ብዛት የተነሳ ላባቸው እስኪንጠፈጠፍ ድረስ እና እራሳቸውን እስኪስቱ ድረስ በመዝሙሩ ይመሰጣሉ፤ የቀረበው ቀለም ሲሸበሸብ ሁሉም በእጅ ያጨበጭባሉ፤ እልል ይላሉ። ስለዚህ ሥርዓቱ ደማቅ ይሆናል። ሁሉም በፍጹም ተመስጦ ሥርዓተ ክዋኔውን ያከናውናሉ።

የማኅሌትንየማዝናናት ተግባር በተመለከተ ወ/ሮ ዝማም ደምወዜ ሐሳባቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> *ከሁሉም ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች እጅግ ደስ የሚለኝ ኪዳን ነው። ይህም ጧት ጧት እንቅልፍ ሳይመጣኝ እንድጸልይ ስለሚደርገኝ ነው። ማኅሌት ግን ከኪዳን ይበልጣል። ምክንያቱም ኪዳን የግል እና የማህበር ጸሎት የሚደርስበት እንጂ መዝሙር የለውም። ማኅሌት ግን መዝሙር፣ ወረብ ስላለው ይማርካል። በተለይ ታቦት ሲነግስ የሚከናወነው ማኅሌት እጅግ ስለሚመስጥ ሀይወታችን አናውቀውም። እኔ በበኩሌ በዚያን ጊዜ እንዴት እንደማጨበጭብ እና እንዴት እንደምዘምር አላውቅም። በትልቅ ተመስጦና መንፈሳዊ እርካታ በመሆኑ ነፍሳችን ደስ ይላታል። አእምሯችን ደስ ይለዋል፣ ፍጹም እርካታ እናገኛለን። በነፍስም*

*በሲ.ጋም ከመደሰት የበለጠ መዝናናት ደግሞ የለም። ስለዚህ ማኅሌት ያዝናናል የሚል እምነት አለኝ (ሚያዝያ 21/09/2003፣ካሴት ቁጥር10፣side 1)።*

መምህር ብርሃነ ሕይወት በጽሐ በበኩላቸው የማሕሌትን የማዝናናት ተግባር አስመልክተው በቃለ መጠይቅ ወቅት የሚከተለውን ሐሳብ ሰጥተዋል።

*ማሕሌት ስብሐተ እግዚአብሔር ነው። ዓላማውም ምስጋና ነው። በምስጋና ወቅት የዕለቱን ቀለም መሰረት በማድረግ መዝሙር ይዘመራል፣ መዘምራኑ ያስረግጣሉ። በዚህ አገልግሎት ሊቃውንቱ በቃለ እግዚአብሔሩ ስለሚማረኩ ሰማይ የደረሱ እስኪመስላቸው ድረስ በአልእሎ ሀሊና ስብሐት እግዚአብሔሩን ያደርሳሉ። በወረብ ጊዜም ፍጹም ተመስጦ በተመላው መንፈስ ያስረግጣሉ። ከቀኝ ወደ ግራ ከፊት ወደ ኋላ እየተዘመመ ከበሮ እየመታ ጸናጽል እየተጸነጸለ እየተጨበጨበና እልል እየተባለ ስለሚዘመር ለህሊና ሆነ ለአእምሮ እርካታ ይሰጣል። በተለይ ምዕመናን ደስታቸውን እጽፍ ድርብ ይሆናል። ከካህናቱ ባላነሰ መጠን እያጨበጨቡ እና እልል እያሉ ይዘምራሉ። በማሕሌት ምዕመናን ስለሚማረኩ በኪዳን እና በቅዳሴ ከሚያደርጉት ተሳትፎ የበለጠ ቁጥራቸው ይጨምራል (ሚያዝያ 20/09/2003 ካሴት ቁጥር 4፣ side 1)።*

በአጠቃላይ ሥርዓተ ማኅሌት በዕለቱ ለሚሳተፉ ሊቃውንት እና ለምዕመናን መንፈሳዊ እርካታ በማጎናጸፍ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። የተዝናኖቱ ከፍተኛነት የሚመዘነው ተሳታፊዎቹ እራሳቸውን እስከማያውቁ እና ሰማይ የደረሱ እስኪመስላቸው ድረስ መመሰጣቸው ነው። በዚህም በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች የተጨናነቁ ሰዎች እርካታ ስለሚያገኙ ከጭንቀት ነፃ ይሆናሉ።

ከዚህ አንጻር ሲታይ ማሕሌት የማዝናናት[22] ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

## 5.4.5 ሃገራዊ ፋይዳ (ተግባር)

ሥርዓተ ማኅሌት ምስጋና፣ ጸሎትና ልመና ነው። በማኅሌት ስለ እንስሳት፣ እጽዋት፣ አራዊት ስለ ሀገር፣ ስለ መንግስት ወዘተ ይጸለያል። ሀገር ከጥፋት፣ ከመከራ እና ከችግር እንድትሰወር ማኅሌት የመለመኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

መምህር ዮሐንስ ግርማይ ስለ ማሕሌት ሀገራዊ ተግባር(ፋይዳ) እንደሚከተለው አብራርተዋል።

*ማኅሌት ጸሎት ነው። ለዚህ ምሳሌ በሰኔ ሚካኤል ዚቅ ላይ ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኑሃ ሰማይ ወስዕለተነ ከመ መዓዛ ሰናይ ( ሚካኤል ሆይ ጸሎታችንን ተቀበልልን*

---

[22] *መርጌታ ጥዑመ ልሳን ሞላ ስለ ማኅሌት የመዝናናት ተግባር እንሚከተለው አብራርተዋል። በማሕሌት የሊቃውንቱ እና የምዕመናኑ ተሳትፎ ብዙ ነው። መዝሙር ሲዘመር እና ሊቃውንቱ ሲያስረግጡ ወደ ገነት የገባን እስኪመስለን ድረስ እራሳችንን አናውቅም። እኔ በበኩሌ በርካታ ዓመታት በማኅሌት አገልግያለሁ፣ በአገልግሎቱ ሳልማረክና መንፈሳዊ እርካታ ሳላገኝ ያለፍኩበት ጊዜ የለም። ደስታዬ እጽፍ ድርብ ይሆናል።ማህሌት በነፍስም ሆነ በስጋ ደስታ ይሰጣል፣ ማለት እርካታ ያስገኛል። ምዕመናንም ተሳትፎአቸው ይጨምራል። በተለይ በትላልቅ ደብሮች ያለው አገልግሎት በጣም የሚማርክ ነው (ሚያዝያ18/09/2003/ ካሴት ቁጥር 7፣side 1) ።*

*ወደ ሰማይም አሳርግልን) የሚል አለ። ማኀሌት ጸሎት መሆኑ እዚህ ላይ መመልከት ይቻላል። ምክንያቱም ተወከፍ ማኀሌትን ሳይሆን ተወከፍ ጸሎተነ ነው ያሉት። በማኀሌት ህዝቡና ካህናቱ ተደጋግፈው ስለሚጸልዩ ሀገር ከመቅሰፍት፣ከመከራ እንድትሰወር ያደርጋል። በዚህም ማንኛውም ሰው ስለ ሀገሩ ማሰብ፣ መጨነቅ እና ማዘን ይለምዳል። ከዚህ በመነሳት ካህናቱም ሆነ ህዝበ ክርስቲያኑ ሀገራዊ አስተሳሰብ፣ሀገራዊ ፍቅር፣ ሀገራዊ ራዕይ ወዘተ እንዲኖራቸው ያደርጋል። የማሕሌት ስርዓት ተጀምሮ ሲከናወን ሰላም ይጸፋል። ይህም ቤተክርስቲያን የሰላም ባለቤት መሆኗ ለማመላከት ነው። አንድም የሀገርን ሰላም የምትሻ እንደሆነች ለማጠየቅ ነው (ሚያዝያ 17/09/2003/ ካሴት ቁጥር 5፣side 1)።*

ከመምህር ዮሐንስ ገለጻ መረዳት የሚቻለው በሥርዓተ ማኀሌት አገልግሎት ቤተክርስቲያን ሀገርን እንደ አንድ አጀንዳ አድርጋ የምታስበው መሆኑን ነው። ቤተክርስቲያን ስለ ሀገር ልማት፣ እድገት መልካም ምኞቷን እየገለጸች ሀገር ከችግር ከመከራ እንድትሰወር ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት እንዲሰፍን በማኀሌት አምላኳን ትለምናለች።

ቀሲስ ሐይሉ አምባዬ በበኩላቸው የማሕሌት ሀገራዊ ፋይዳ (ተግባር)ን በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል።

*ማኀሌት የራሱ የሆነ የአገልግሎት ሂደት አለው። ጸሎቷ ለማርያም ለነፍሳተ ሙታን፣ ጸሎታ ለማርያም ወስዕለታ ለህዝብ ክርስቲያን ከተባለ በኋላ ጸሎታ ለማርያም ወስዕለታ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ትዕቀባ እመዓተ ወልዳ (እመቤታችን ሀገራችንን ከመቅሰፍት ጠብቂልን) ይባላል። ስለዚህ በማሕሌት ስለ ሀገር ሰላም፣ ስለ ሀገር ፍቅር ይለመናል። ዲያቆኑ በእንተ ቅድሳት ሲያደርስም "በሀገራችን ፍጹም ሰላም እንዲኖር እንጸልያለን" ይላል። ስለዚህ ስለ ሀገር ሰላም፣ ስለ ሀገር ፍቅር መጸለይ አንዱ የማሕሌት ተግባር ነው። ይህ ደግሞ በሀገር ላይ የእኔነት ስሜት ከማሳደሩም በላይ ሀገርን የመውደድ፣ ስለ ሀገር የማሰብ፣ የመቆርቆር ዕድል ይፈጥራል። የሥርዓተ ማኀሌት አገልግሎት በትክክል የተረዳው ክርስቲያን ፍጹም ሀገር ወዳድ ይሆናል (ሚያዝያ19/09/2003 ቁጥር 6፣side1) ።*

ከላይ ከተገለጹት ሐሳቦች የምንገነዘበው በማኀሌት አገልግሎት ስለሀገር[23] ፍቅርና ሰላም የሚጸለይ ሲሆን ይህም ሀገር ከተፈጥሯዊ ሆነ ከሰው ሰራሽ አደጋ እንድትጠበቅ ነው። የሀገር ሰላም የህዝብ ሰላም፣ የቤተ ክርስቲያን ሰላም በመሆኑ ማኀሌቱ ሲፈጸም ሰላም ይጸፋል። ይህ ደግሞ ከሰላም የበለጠ ምንም ነገር እንደሌለ ያመለክታል። በማኀሌት

---

[23] መምህር ይባቤ አድሂና የማህሌት ሀገራዊ ተግባር(ፋይዳ) ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

*የማኀሌት ተግባር እግዚአብሔር ማመስገን ቢሆንም ምስጋናው እና ልመናው ስለ ሃገር ስለ ሰላምና ፍቅር፤ ስለሀገር በረከትና ረድኤት እየታሰበ ይከናወናል። ከመስተብቁዕ ሆነ ከያሬድ ዘይነግስ እንዲሁም መልክዓ ቁርባን ሃገር እየታሳበ ይፀለያል። ለምሳሌ፡- ባርካ ቁርቆስ ለዛቲ መካን እይምፃእ ሞተ ላህም ወኢአበረ እክል (ቁርቆስ ሆይ ይህችን ሀገር ባርካት የላም ምት እና የእህል ችግር እንዳይደርስባት ጠብቃት) የሚል ዚቅ እናገኛለን። ከዚህ የምንረዳው በማህሌት ስለ ሀገር ሰላም፣ ፍቅር የሚጸለይ መሆኑ ነው። የማኀሌት ሥርዓተ አገልግሎቱ ሲያልቅም በሰላም ይፀፋል። ስለ ሰላም ይሰበካል ማለት ነው (ሚያዝያ 19/09/2003፣ካሴት ቁጥር፣8፣side 2) ።*

የሚያገለግሉ ሰዎች ስለ ሃገራቸው በመጸለያቸው ምክንያት ሀገራዊ ራዕያቸውና ሀገር የመውደድ ፍላጎታቸው ይጨምራል። ከዚህ በተጨማሪ ስለሀገር መልካም ማሰብን እና መቆርቆርን አንዱ ግዴታቸው አድርገው በማሰብ በቤተክርስቲያን ማኅሌት በቆሙ ቁጥር ግዴታቸውን ይወጣሉ። በዓለማዊ አስተዳደር ሊያስፈጽሙ ያልቻሏቸውን ተፈጥሯዊ ጉዳዮች (ዝናብ፣ ሰላም ወዘተ..) በማኅሌት ያስፈጽማሉ።

በአጠቃላይ በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ስለ ሀገር ሰላም እና ፍቅር ይጸለያል። የጸሎቱ ዋና ዓላማ ሀገር ከጥፋትና ከመከራ እንድትሰወር ሰላምና ፍቅር በምድር እንዲሰፍን ለማድረግ ነው። ከዚህ አንጻር ማሕሌት ሀገራዊ ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

### 5.4.6. ኪነ ጥበባዊ ፋይዳ (ኪናዊ ተግባር)

ማሕሌት በከበሮ፣ በጸናጽልና በመቋሚያ ታጅቦ የሚቀርብ ስነ-ጥበብ ነው። ይህም በዜማ የሚዜም በመሆኑ የራሱ የዜማ ምልክቶች እና ስልቶች አሉት። ያሬድ ዜማ ሲደርስ በ 22 ስነ ፍጥረት ምሳሌ ነው።የዜማ ምልክቶቹ ደግሞ 10 ናቸው። ማሕሌትም ከእነዚህ ጉዳዮች የራቀ አይደለም።

ሥርዓተ ማኅሌት ምት ያለው ነው። ክዋኔውም ምቱን መሰረት በማድረግ በንዋያተ መዝሙራት (ከበሮ ጸናጽል እና መቋሚያ) ታጅቦ የሚቀርብ ነው። ዝማሬውን ለመዘመር ምቱን የጠበቀ መሆን አለበት። ምቱ ካልተጠበቀ ደግሞ ዜማው ይሰበራል።ዜማው የተሰባበረ ከሆነ ደግሞ ሥርዓተ ክዋኔው የተበላሸ ይሆናል። ስለዚህ ምትን ጠብቆ በመዘመር ሥርዓተ ክዋኔውን ማቀናጀት የሚያስችል ማኅሌት ለባህላዊም ሆነ ለዘመናዊ ሙዚቃ የበኩሉን ድርሻ እንዳበረከተ መገንዘብ ይቻላል።

መምህር ዳንኤል አየነው ማኅሌት ለኪነ ጥበብ ያለውን ድርሻ በተመለከተ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

> *ማኅሌት በሁለት መክፈል ይቻላል። ማኅሌተ መንፈሳዊ እና ማኅሌተ ሥጋዌ። መንፈሳዊ የሚባለው በዜማ በቤተክርስቲያን የሚዘመር ሲሆን ማኅሌተ ስጋዊ የምንለው ደግሞ በምዕመናን በጥምቀት እና መስል በዓላት ባህላዊ ልብስ በመልበስ እና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በመያዝ የሚዜም ነው። ለባህላዊ ዜማ መሰረቱ ያሬድ ነው። ዜማ የያሬድ ውጤት በመሆኑ ማንኛውም ባህላዊ እና ዘመናዊ ዘፋኝ ስልቱን፣ የዜማ አወጣጡ እና አወራረዱን ውዝዋዜው (እንቅስቃሴው) የወሰደው ከያሬድ ነው።በያሬድ በኩል በቤተ ክርስቲያን የተጀመረ ዜማ እያደገና እየሰፋ ዛሬ የምናየው ጥበብ ደርሷል። " ትውልድ ይሐልፍ ትውልድ ይመጽዕ" (ትውልድ ያልፋል ትውልድ ይተካል) ነውና አንዱ ከሌላው እየወሰደ የሚጨመረውን እየጨመረ የሚቀነሰውን እየቀነሰ ኪነ ጥበቡ አድጓል (ሚያዝያ 18/09/2003 ካሴት ቁጥር 7 )።*

በአጠቃላይ ማኅሌት አንዱ ስነ ጥበብ በመሆኑ ምት ለመጠበቅ፣ የድምጽ አወጣጥ አወራረድ (tone)፣ የከበሮ አመታት፣ የጸናጽል አያያዝ ፣ አለባበስ (clothing)፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች (musical instruments) አጠቃቀም፣ የዳንስ (dance) እንቅስቃሴ ክህሎት የሚያዳብር ነው። ይህ ደግሞ ለዘመናዊ ሆነ ለባህላዊ የሙዚቃ እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል።

### 5.4.7 የማስተማር ተግባር

ከዋዜማው ጀምሮ የሚቆመው ማኅሌት ይዘቱ ትምህርት አዘል ነው። የበዓለ ትንሣኤ ሥርዓተ ማኅሌት ብንወስድ ኢየሱስ ክርስቶስ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱ ይሰብካል። የሚያዝያ ጊዮርጊስ ስርዓተ ማኅሌትም ብንመለከት የሰማዕቱ ጊዮርጊስ ተጋድሎ መሰረት በማድረግ ይቆማል። ሰማዕቱ ጊዮርጊስ በወጣትነት ዕድሜው ስልጣን ሀብት፣ ንብረት፣ ምቾትና ድሎት ይቅርብኝ ብሎ ስለ ክርስቶስ እና መንግሰተ ሰማያት የተጋደለውን ተጋድሎ እና ያገኘውን የመጨረሻ የድል አክሊል ይሰብካል። ጊዮርጊስን እንደ ጀግና (Hero) በመቁጠር መዘምራንም ሆነ ምዕመናን የእሱን ጽናት፣ድፍረት ብርታት እና ሐይማኖታዊ ትጋት እንዲኖራቸው እያሰቡ ሥርዓተ ክዋኔውን በትጋት ያከናውናሉ። በዚህም የሥርዓቱ ተሳታፊዎች መንፈሳዊ እና ስጋዊ እውቀት ያገኛሉ።

መሪጌታ ተክለ ብርሃን የማኅሌትን የማስተማር ተግባር እንደሚከተለው አብራርተዋል::

> *ማኅሌት በመሰረቱ ምስጋና ነው። ትምህርትም አለው። የማኅሌት ትምህርት የዕለቱን ቀለም መሰረት ያደረገ ነው። ለምሳሌ አሁን ያከበርነው ሚያዝያ ጊዮርጊስ ብንወስድ ሥርዓተ ማኅሌቱ ስንቆም የጊዮርጊስ ተጋድሎ፣ ስቃይ፣ እያሰብን እና ስለ ክብሩ እያስታወስን በዓሉን አክብረነዋል ። ይህ ደግሞ ጽናትን፣ ጥንካሬን፣ ፍቅረ እግዚአብሔርን ያስተምራል። በዚህ ዓለም ሰው ሲኖር በስራው ታታሪ፣ በሚገጥሙት ችግሮች ታጋሽ እና ለቤተሰቡ፣ ለወገኑ፣ ለጎረቤቱ እንዲሁም ለሀገሩ በቅንነት የሚያገለግል መሆን አለበት።ማኅሌት እያንዳንዱ ነገር ፈልፍለን ካወጣነው መዝሙር ብቻ ሳይሆን በርካታ ትምህርቶች ያያዘ ነው (ሚያዝያ24/09/2003 ካሴት ቁጥር 8 side 2)::*

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም" በሚል የታተመው መጽሐፍ የማኅሌትን አስተማሪነት እንደሚከተለው ተብራርቷል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሰረት ከዓመት እስከ ዓመት ለሚከናወነው ማንኛውም ሥርዓተ ጸሎት ዋናው መሪው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ነው። ማሕሌቱ፣ ቅዳሴው፣ፍትሐቱ፣ ጥምቀተ ክርስትናው ወዘተ ሁሉ በዜማው መሪነት የሚከናወኑ ናቸው። የዘመናቱ አከፋፈልም ሆነ በየዘመናቱ መከናወን ያለባቸው የጸሎት ክንውኖች የሚመሩት በዚህ የዜማ መጽሐፍ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ድርሰቱ ራሱ

በዋነኛነት ጸሎትን በብዛት የያዘ ነው። ከዚህም ሌላ የስነ ምግባር ትምህርት፣ የምስጋናና የንስሐ ትምህርትን ያጠቃለለ በመሆኑ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ የሚሰጠው ጥቅም ከፍ ያለነው (2000፣127)።

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ በተጨማሪ ማኅሌት እርስበርስ መዋደድን እንደሚያስተምር ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። "ንጹም ጸመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ እስመ ከማሁ አዘዘነ" የሚለው መዝሙር እርስ በርስ መዋደድን የሚያስተምር ነው።

ከመስክም ሆነ ከጽሑፍ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ማኅሌት ቅንነትን፣ ፍቅርን፣ መከባበርን፣ ትእግስትን እና ተስፋ አለመቁረጥን የመሳሰሉ ስነ ምግባር ነክ ጉዳዮችን በማስተማር[24] ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል። ሰዎች መልካም ስነምግባር የተላበሱና የሞራል ጥንካሬ ያላቸው እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡ ፡ከዚህ አንጻር ማኅሌት የማስተማር ተግባር አለው።

## 5.4.8 የማጠናከር ተግባር

ሰዎች ራሳቸውን፣ አካባቢያቸውን፣ ቁሳዊ እናመንፈሳዊ ዓለማቸውን፣ ማሕበራዊ ድርጅታቸውን በፎክሎር አማካይነት ያጠናክራሉ። ይህን የሚያደርጉት ሥርዓተ ክዋኔው ቀጣይነት እንዲኖረው ነው።

ማኅሌት ከተጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ሳያቋርጥ እየተከወነ ያለ ስነ ጥበብ ነው። ይህ ስነጥበብ ለሀገርና ለወገን ስነ ምግባርን በማስተማር፣ ማሕበራዊ ኑሮን በመመስረት፣ ሐይማኖትን በማጠንከር፣ ባህላዊ እሴትን በማጎልበት፣ ኪነጥበብን በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ከዚህ በፊት ተገልጿል። እነዚህ በርካታ ጥቅሞች ያሉት ሥርዓተ አገልግሎት ደግሞ ቤተክርስቲያን፣ ሊቃውንት እና ህዝበ ክርስቲያን ሥርዓተ ክዋኔውን ሳይለቅ እንዲቀጥል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ። ማጠናከር ማለትም ያለውን ለዛ፣ ሥርዓት እና የአከዋወን ስልት ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

የማኅሌትን የማጠናከር ተግባር በተመለከተ መምህር ብርሃነ ሕይወት በጽሐ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

---

[24] ሊቀ ትጉሃን ሞላ የሥርዓተ ማኅሌት የማስተማር ተግባር አስመልክተው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሥርዓተ ማኅሌቱ፡ የሚቆመው ስነ ፍጥረትን መነሻ በማድረግ ነው። በዚህም ስለ እጸዋቱ፣ ስለ እንስሳቱ፣ ስለ ህዝብ በአጠቃላይ ስለ ሀገር ይፀለያል። በዕለቱ የሚቆመው ቀለም የፃድቁን፣ የሰማዕቱን፣ የነብዩን ተጋድሎ የሚያወሳ በመሆኑ መንፈሳዊ እና ስጋዊ እውቀት ያስጨብጣል። በሊቃውንቱም ቢሆን እርስ በርስ የመከባበር፣ የመዋደድ ስነ ምግባርን እንዲያዳብሩ ያደርጋል። እንግዲህ በእኔ አመለካከት ትምህርት ማለት ሌላውን ማክበር ለሌላው ፍቅር መስጠት ተስፋ አለመቁረጥ ነው። እነዚህም ደግሞ ማህሌት ሲከናወን የሚታዩ ተግባራት ናቸው (ሚያዝያ19/09/2003 ካሴት ቁጥር 1, Side 1)::

*ማኅሌት ሲኖር ምዕመናን ከምን ጊዜውም በላይ ወደ ቤተክርስቲያን ይገሰግሳሉ። ሥርዓቱ በክብር፣ በጸናጽልና በመቋሚያ ታጅቦ ስለሚቀርብ ምዕመናን ይረካሉ። ስለዚህ ማኅሌት የምዕመናን ሐይማኖት ያጠናክራል። ስብሐተ እግዚአብሔር (ማኅሌት) ከሚቆምበት ቦታ ምዕመናን በሐይማኖታቸው ይጠነክራሉ። ለሊቃውንትም ቢሆን ማኅሌት ጸጋ ያበዛላቸዋል። በረከተ ስጋና በረከተ ነፍስ ያስገኝላቸዋል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ማኅሌት የምትጠቀመው ሐይማኖትን ለማጠናከር ስለሚያግዝ ነው (ሚያዝያ 20/09/2003 ካሴት ቁጥር 4 side 2)*

ከመምህር ብርሃነ ሕይወት ገለጻ የምንገነዘበው ማኅሌት ዋነኛ የሐይማኖት ማጠንከሪያ መሳሪያ መሆኑን ነው። ቤተ ክርስቲያን፣ ምዕመናን ሐይማኖታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን እንዲያከብሩ የምታደርገው በማኅሌት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ ማኅሌት የማጠናከር ተግባር አለው የሚባለው ሥርዓተ ክዋኔው በቀጣይነት እንዲከበር የሚያስችል በመሆኑ ነው። ማኅሌት እንደ ስነ ጥበብነቱ እየተከወነ ከአንድ ትውልድ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ፣ ከዘመን ወደ ዘመን ሲቀጥል ሥርዓተ ክዋኔው ይጠናከራል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የተገልጋዩ ህዝብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ የሥነ ምግባር፣ ጥበብ እንዲቀጥል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ከዚህ አንፃር ማኅሌት የማጠናከር ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

### 5.4.9 የመቆጣጠር ተግባር

ፎክሎር በአንድ ማሕበረሰብ ተቀባይነት ያላቸው እሴቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያደርግ የጥናት መስክ ነው።በማሕበረሰቡ ክፉ ባህሪያት የሚባሉት ስርቆት፣ መዋሸት፣ ስስት፣ሐሜት ወዘተ ይገሰጻሉ።

ማኅሌት የራሱ አከዋወን ሂደት ያለው በመሆኑ ሥርዓተ ክዋኔውን በጠበቀ መልኩ እንዲከወን መሪጌታው በቅኔ ማኅሌቱ መሃል በመሆን ይቆጣጠራል። ምዕመናንም የቤተክርስቲያን ሥርዓት በሚፈቅደው መሰረት በወረብ ጊዜ እንዲያጨበጭቡ እና እልል እንዲሉ ይፈቅድላቸዋል። ከዚያ ውጭ ከበሮ መምታትም ሆነ ጸናጽል መያዝ አይችሉም። በማኅሌት ሁሉም ድርሻ ድርሻ ያላቸው በመሆናቸው የመሪጌታው ድርሻ ለቀኝ ጌታ፣ የቀኝ ጌታ ድርሻ ለግራ ጌታ አይሰጥም። ይህ ሁሉ የሚደረገው ሥርዓተ ክዋኔውን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ ነው።

መምህር ዳንኤል አየነው የማኅሌትን የመቆጣጠር ተግባር በጠየቅኳቸው ጊዜ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

*ሥርዓተ ማኅሌት እግዚአብሄር የሚገለገልበት ሥርዓተ አገልግሎት ነው። እንግዲህ በማኅሌት ቁጥጥር አለ ሲባል አንደኛ አገልጋዮቹ ከሥርዓት እንዳይወጡ ለማድረግ ነው። ከሥርዓት የሚወጡትን ተግሳጽ፣ ምክር ይሰጣቸዋል። ከዚያም ባለፈ በትክክል የማያገለግሉ ከሆኑ በሰበካ ጉባኤ ይቀጣሉ። ስለዚህ የማኅሌት*

*ቁጥጥር ወደ መልካም ስነ ምግባር ለማምጣት እንጂ ሰውን ከቤተ ክርስቲያን ለማግለል አይደለም (ሚያዝያ 18/09/2003 ካሴት ቁጥር 7 side 2)።*

ከመምህር ዳንኤል ገለጻ ሁለት ነገሮች ማጤን ይቻላል። በማኅሌት ቀጥጥር የሚደረገው አንደኛ አገልጋዮች እግዚአብሔርን በሚገባ እንዲያገለግሉ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ መልካም ስነ ምግባር እንዲላበሱ ነው። ከእነዚህ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች በመነሳት ማኅሌት የመቆጣጠር ተግባር አለው ማለት ያስችላል።

ማኅሌት በመሪጌታው ቁጥጥር ስር የሚከናወን በመሆኑ ያጠፋውን በመምከር እና በመገሰጽ፣ ሥርዓት የማያውቁትን በማስተማር እና ሥርዓት በማስያዝ ሥርዓተ ክዋኔው በአግባቡ እንዲከናወን ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ መሰረት ያለው ነው። "ወንድሞች ሆይ እንመክራችኋለን ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገስጿቸው ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው። ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሱ። ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፣ ነገር ግን ሁል ጊዜ እርስ በርሳችሁ ለሁሉም መልካም ለማድረግ ትጉ። ሁል ጊዜ ደስ ይበላችሁ፣ ሳታቋርጡ ጸልዩ፣ በሁሉ አመስግኑ፣ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና" (1ኛ ተስ 5፡14)።

ስለዚህ በማኅሌት ሥርዓተ ክዋኔ ድፍረት የሌላቸው ድፍረት እንዲያገኙ፣ ደካሞች እንዲበረቱ ስህተት የሚፈጽሙ ደግሞ ከስህተታቸው እንዲታረሙ ይደረጋል። ከዚህ አንጻር ማኅሌት የቁጣጠር ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

### 5.4.10. የማሳተፍ ተግባር

በማኅሌት መዘምራን፣ ካህናት፣ ዲያቆናት እና ምዕመናን ይሳተፋሉ። ተሳትፎአቸው እንዳላቸው ሐይማኖታዊ እውቀት እና ማህበራዊ ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ግን የሥስርዓቱ ተሳታፊ መሆናቸው ነው። ይህም ሲባል ዕድሜ፣ ፆታ፣ ዘር፣ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ባህል ወዘተ... ሳይለይ መሳተፋቸውን ያመለክታ። በእርግጥ ማኅሌት በኦርቶዶክሳዊያን የሚከናወን ሥርዓተ አገልግሎት በመሆኑ ከእምነቱ ተከታዮች ውጭ ሌሎች ሰዎች በሥርዓቱ አይሳተፉም። የማሳተፍ ተግባር የተባለው የእምነቱን ተከታዮች የሚመለከት ሲሆን ልዩነታቸውን አጥፍተው ሁሉም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመገኘት ምስጋና፣ ጸሎት፣ መዝሙር በጋራ መዘመራቸውን ያመለክታል።

መምህር ዳንኤል አየነው የማኅሌትን የማሳተፍ ተግባር በጠየቅኳቸው ወቅት የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል።

"ማኅሌት ምስጋና በመሆኑ እግዚአብሔርን ለማመስገን የመጡ ሁሉም ክርስቲያኖች ይሳተፉበታል። መምህራኑ ሥርዓተ ማኅሌቱን በመምራት፣ መዘምራኑ በመዘመር፣ ካህናቱ በመጸለይ፣ ዲያቆናቱ በምስባክ፣ ምዕመኑ በእልልታ እና በጭብጨባ ይሳተፋሉ መሳተፍ ማለት ይህ ነው። ሁሉም ክርስቲያኖች የኃይማኖት ዜግነት ስላላቸው በቤተክርስቲያን እኩል አገልጋይ ይሆናሉ።" (ሚያዝያ18/09/2003፣ ካሴት ቁጥር 7፣ side 2)።

በአጠቃላይ ሥርዓተ ማኅሌት መዘምራን፣ሊቃውንት፣ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ምዕመናን ሴት፣ ወንድ፣ ትንሽ፣ ትልቅ፣ ሀብታም፣ ድሃ ሳይባል ሁሉም የሚሳተፉበት ሥርዓተ አገልግሎት ነው። በመሆኑም ከኪዳን፣ ከቅዳሴ፣ ከሰዓታት ይልቅ አገልግሎቱ ደማቅ እንደሆነ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከላይ ከተገለጹት ቀጥተኛ ተግባራት በተጨማሪ ማኅሌት የራሱ የሆኑ ጎንዮሻዊ ተግባራት አሉት። ጎንዮሻዊ ተግባራት የተባሉት በማኅሌት ሰበብ የሚከወኑ በመሆናቸው ነው። እነዚህም የተጣሉ ሰዎችን ማስታረቅ፣ ቤት የተቃጠለበትን ሰው መርዳት፣ ሽምግልና፣ ስብሰባ መሰብሰብ፣ የንግድ ልውውጥ ማድረግ ወዘተ.. ናቸው። እነዚህም በማኅሌት ሰበብ የመጡ ተግባራት በመሆናቸው ትኩረት ያስፈልጋቸዋል። የፎክሎር አንዱ የትኩረት አቅጣጫ በክብረ በዓል ሰበብ የመጡትን ግንኙነቶች እና ተግባራቱን ማጥናት ነው። ከዚህ አንጻር ማኅሌት ጎንዮሻዊ ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

# 6. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሐሳቦች

## 6.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በክብረ በዓላት ሥርዓት ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ ላይ ያተኮረ ነው። ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም በአካባቢው ከሚኖሩ አውራ የመረጃ ሰጭዎች ተሰብስበው ትንታኔ ተደርጐባቸዋል:: በትንታኔው መሠረት ከሚከተሉት የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ መድረስ ተችሏል።

ማኅሌት ጥንታዊ የሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሥነ ጥበብ ነው። እንደ ጥበብነቱም በከበሮ፣ መቋሚያ፣ ጸናጽል ባሉት ንዋያተ መዝሙራት ይከወናል። እነዚህ ዋና ዋናዎቹ የማኅሌት መከወኛ ንዋያተ ቅድሳት ቢሆኑም በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ሌሎች እንደ እጣን፣ ጧፍ፣ ጽንሐ፣ ደወል፣ ዣንጥላ፣ መስቀል፣ ጥንግ ድርብ፣ ቀሚስ፣ ድጓ፣ ጾመድጓ፣ ዝማሬ መዋስዕት ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት የያዘ ነው። በመሆኑም ንዋያተ መዝሙራቱ እንደ ዜማ፣ መከወኛ ቦታና ከዋኝ ከመሳሰሉት አበይት የሥርዓተ ማኅሌት ግብዓቶች መካከል የሚመደቡ በመሆናቸው ያለነሱ ማኅሌት ሊከወን አይችልም። እነዚህም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ የተለዩ በመሆናቸው ለዚሁ ተግባር ሲባል የተለየ ቅባት ይቀባሉ። ንዋያተ መዝሙራቱ ተምሳሌታዊ ውክልና ያላቸው ናቸው። ተምሳሌታዊ ውክልናቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀል ወይም ፀዋትወ መከራ ጋር እንዲሁም ከቅዱሳን ጋር በእጅጉ ተያያዥነት አለው። በማኅሌት ሥርዓተ ክዋኔ እግዚአብሔር ይመሰገንበታል፤ እርሱ ያከበራቸው ቅዱሳንም ይታሰቡበታል፤ በመሆኑም የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ የኢየሱስ ክርስቶስ የድኅነት ጉዞ የሚያስገነዝብ ሥነ ጥበብ ነው።

የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች አስር ሲሆኑ እነዚህም መቃኘት፣ መቀበል፣ መምራት፣ መመራት፣ ዝማሜ፣ ንዑስ መረግድ፣ ዓቢይ መረግድ፣ ጽፋት፣ ድርብ ጽፋትና የጭብጨባ ጽፋት ናቸው። እነዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ሃይማኖታዊ ተምሳሌት ይታይባቸዋል።

የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታዎች አሉት። እነዚህም ፎክሎራዊ ገጽታዎች ከደረጃዎቹ፣ ከንዋያተ መዝሙራቱ እና ከተግባራቱ የመነጩ ናቸው። ማኅሌት ፎክሎራዊ ገጽታን የሚያላብሱት የመከወኛ መሳሪያዎቹ (ከበሮ፣ መቋሚያ፣

ጸናጽል)፣ መከወኛ ምክንያት፣ ከዋኙ፣ ታዳሚያን፣ የክዋኔው አውድ፣ የክዋኔ መሪዎች እና የክዋኔ ማዕቀፍ የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በየአመቱ የሚፈጠሩ አዳዲስ ወረቦች፣ ቅኔዎች፣ ባህላዊ አልባሳት እንዲሁም ግላዊና ቡድናዊ ተግባራት ሌላኛዎቹ ፎክሎራዊ ገጽታን የሚያመላክቱ መሆናቸው ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል። ከዚህም ባሻገር ማኅሌት መንፈሳዊና ቁሳዊ ተዝናኖት ይገኝበታል። ህዝበ ክርስቲያኑ በጋራ ተሰብስበው ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኪነጥበባዊ፣ ሀገራዊና ሐይማኖታዊ ጉዳዮችን ያከናውኑበታል። በዚህም ግላዊና ቡድናዊ ክህሎታቸውን በመጠቀም የተለያዩ ፎክሎራዊ ክንዋኔዎችን እንደሚያካሂዱበት ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል።

ሥርዓተ ማኅሌት ከደረጃዎቹ እና ከንዋያተ መዝሙራቱ ትዕምርታዊ ውክልና በተጨማሪ የራሱ ተግባራት አሉት። እነዚህም ተግባራት ቀጥተኛና ሰበብ ማኅሌት በሚል በሁለት ተከፍለው የተጠኑ ሲሆን የማኅሌት ቀጥተኛ ተግባራት የሚባሉት ሐይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ሀገራዊ፣ ኪነጥበባዊ፣ ማህበራዊ እንዲሁም የማዝናናት፣ የመቆጣጠር፣ የማጠናከር፣ የማስተማርና የማሳተፍ ናቸው። ተግባራቱ በውስጣቸው ፎክሎራዊ ገጽታን የያዙ ናቸው።

በአጠቃላይ በታዳሚዎች መካከል የአስተሳሰብ፣ የእሴት፣ የስነምግባር፣ የሞራል ክህሎትን የሚያዳብር በመሆኑ ተግባራቱና ፎክሎራዊ ገጽታዎቹ የጎሉ መሆናቸው በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል።

## 6.2 ይሁንታ

አጥኚው ከጥናቱ ሂደት ግንዛቤ በመነሳት ወደፊት እንዲህ ቢሆኑ ብሎ የሚያስባቸውን ጉዳዮች በይሁንታነት ጠቁሟል።

በቤተ ክርስቲያን በዓውደ ምህረት ላይ ቤተክርስቲያኑን በገቢ ለማጠናከር ሲባል በስዕለት የገቡ እንደ ማር፣ በጎችና ጥቅል ጎመን ለጨረታ ቀርበው ተሸጠዋል። ጨረታው ረጅም ሰዓት በመፍጀቱ በህዝበ ክርስቲያኑ የመሰላቸትን ስሜት ፈጥሮ ነበር። ስለዚህ የጨረታውን ሰዓት ማሳነስ ወይም ደግሞ ሥርዓተ አገልግሎቱ ከተጠናቀቀና ታቦቱ ከገባ በኋላ ቢከናወን የሚፈጠረውን ችግር መቅረፍ ይቻላል።

ሥርዓተ ማኅሌት የሚከወነው በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በወቅታዊ የገቢ ማነስ ምክንያት ሥርዓተ ክዋኔውን የሚያከናውኑ ሊቃውንት እየቀነሱ እንደመጡ ከመስክ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሊቃውንቱ እንደ ደረጃቸው ተመጣጣኝ ደምወዝ ብትከፍላቸው ሥርዓተ ክዋኔው በደመቀ ሁኔታ በቀጣይነት እንዲከወን ያስችላል።

ሥርዓተ ማኅሌት አሁን እየተከበረ ባለት ደረጃ በቪዲዮ፣ በፎቶግራፍ እና በቴፕ ሪከርደር ቀርጾ ከትውልድ ወደ ትውልደ እንዲተላለፍ ማድረግ ከባህል አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አጥኚው ያምናል። ይህም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔን በቀላሉ እንዲገነዘቡት እገዛ ሊያደርግ ይችላል። በተጨማሪም ወደፊት የሚተኩት ትውልዶች በዚህ ዘመን የተከናወኑትን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ሁኔታዎች እንዲገነዘቡ ያደርጋል። በመሆኑም ጥናቱ ከአሁን ከፍ ባለ ደረጃ ጥልቀትና ስፋት ባለው መንገድ ቢጠና የበለጠ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል። ለዚህም የተለያዩ ባለሙያዎች ቴክኖሎጂ ባፈራቸው ዘመናዊ የምስል ወድምጽ መሳሪያዎች በመታገዝ የምርምር ስራ ቢያካሂዱ፤ የጥናቱም ግኝት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በዶክመንተሪ ፊልም ቢቀርብ፣ ጥናታዊ ጽሑፍም በተለያዩ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ እና ተሰንዶ ቢቀመጥ መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህላችንን የማስተዋወቅ ምቹ አጋጣሚ ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል። ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ማኅሌትን ለሀገር ልማት በማዋል የቱሪዝም መስህብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተ ማርያም ወርቅነህ። ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም።

ሄኖክ ወልደ ሚካኤል። መዳልወ አልባብ የአቋቋም ምልክት፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም።

ሉሌ መልአኩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1986 ዓ.ም።

ልሳነ ወርቅ ገ/ጊዮርጊስ። ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ ፣ መቀሌ የቋንቋ ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ 1997 ዓ.ም።

መሰበወርቅ ቅጣው። "የገና ክብረ በዓል አከባበር" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችናሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1997 ዓ.ም።

መቐለ ።"ቢሮ ከተማ ልምዓትን ኮንስትራክሽንን ቀንዲ ከይዲ ስራሕ ምልማዕ መሬታትን ምሃብ መረዳእታን ከተማታት"፣ 2001 (ያልታተመ)።

ማህበረ ቅዱሳን። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 2000 ዓ.ም።

__________።"ትምህርተ ኦርቶዶክስ መዝሙር"፣ አዲስ አበባ፣ 1993 (ያልታተመ)።

______።ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ አዲስ አበባ፣ ቁጥር 7፣ ታህሳስ/ጥር፣ 1986 ዓ.ም።

__________። ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ አዲስ አበባ፣ ቁጥር 2፣ የካቲት/መጋቢት፣ 1990 ዓ.ም።

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ። "አማርኛ የቤተ-ክርስቲያን መዝገበ ቃላት"፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ብራና ጽሑፎች ማይክሮ ፊልም ድርጅት በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ 1994 (ያልታተመ)።

ሥርግው ገላው። "የዜማ፣ የሙዚቃ መሳሪያ"፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)።

ሰለሞን ደርቤ። "የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችናሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ብርሃኑ አድማስ። በዓላት ምን? ለምን? እንዴት?፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኃ.የተ. የግ.ማህበር፣ 2002 ዓ.ም።

ቴዎድሮስ ገብሬ። በይነ-ዲስፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ የኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001 ዓ.ም።

አምደ ጽዮን ተሰማ። የቅዱስ ያሬድ ታሪክና የዜማው ምልክቶች፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም።

አሰፋ ብርሃኑ። "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በወፍላ ወረዳ ቤተ ክህነት የደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ" ፣ 1993 (ያልታተመ) ።

አሸናፊ ጌታሁን። "የሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ" ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችናሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ1996 ዓ.ም።

አበባው ይርጋ። "የጥምቀት በዓል ማኅበረ-ባህላዊ አውዶቹና ፋይዳዎቹ"፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መፅሔት፣ ቅፅ 39፣ 1-2፣ 1998 ዓ.ም።

ኤልያስ አብርሃ። ይትበሃል ዘጎንደር ዘውእቱ ሥርዓተ ማኅሌት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1999 ዓ.ም።

ኤርሚያስ ወልደኢየሱስ። ድርሳነ ቅዱስ ያሬድ በግዕዝና በአማርኛ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2000 ዓ.ም።

ወንጌሉ ዘወርቅ። "የኮረም ሐያሎ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" የካቲት 19፣ 1989 (ያልታተመ)።

ከፍያለው መራሒ። የቤተክርስቲያን አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ፣ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፣ 1986 ዓ.ም።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም።

ዘወንጌል ገ/ኪዳን እና ሌሎች። ቤተክርስቲያንህን እወቅ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ 1996 ዓ.ም።

ዞባ ደቡብ ትግራይ። "ስትራተጂታት፣ አንፈታት፣ ሽቶታትን ልምዓታት ቀጠናታት ማዕኸላትን" ፣ 2001 (ያልታተመ)።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን። መርሐ ጽድቅ ባህለ ሐይማኖት፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም።

ያሬድ ገ/መድህን። ኖኅተ ሰማይ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ እንተርፕራይዝ፣ 1996 ዓ.ም።

ደስታ ተክለወልድ፣ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ኣ.ም።

ጐርጐርዮስ (አባ)። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1974 ዓ.ም።

ጥዑመ ልሳን ካሳ። ያሬድና ዜማው፣ አዲስ አበባ፣ ት/ዘ/ማ/ቤት፣ 1962 ዓ.ም።

ፈቃደ አዘዘ። የስነ ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ 1991 ዓ.ም።

ፍሬ ሕይወት ባዩ። "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሐይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ገጽታ" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎቸችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኤም.ኤ. ዲግሪ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ፍትሐ ነገስት። ሥጋዊ ወመንፈሳዊ የህግ ምንጭ፣አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

Aymro Wondemagnehu and Joachim Motovu. The Ethiopian Orthodox Chruch. Addis ababa, Birhanina Selam H.S.I Printing Pess, 1970.

Ballenger, E.W. Figures of Speech Used in Bible:Expalined and Illustrated. Michigan Baker Books House: Grnad Rapids, 1988.

Bauman, Richard. Verbal Art as Performance. Waveland: Waveland University Press, 1997.

Ben -Amos, Dan, "Towards a Definition of Folklore in Context". The Journal of Folklore in Context. New Delhi: South Asian Publishers Inc,1982.

Budge, Sire Wallis. A History of Ethiopia, Nubia, Abissinia. Metuh and C0.Ltd.Essex Street wc, London :Great Britain 1928.

Challot, Chiristian. The Ethiopian Orthodox Tewahido Tradation. Poland: Orthodox, Bialy Stox, 2002.

Deborah, A. Kapchan. "Common Ground: Key Words for the Study of Expressive Culture" the Journal of American Folklore. Vol. 108, No. 430, p. 479-508, 1995.

Dundes, Alan. The Study of Folklore. N. J: Prentic-hall inc, 1965.

Finnegan, Ruth. Oral Literature in Africa. Oxford: Clarendon Press, 1970.

------------------.Oral Poetry, its Nature,Significance and Social Context. Cambr idge:Cambridge University Press,1977.

Fletcher, Ronald. Human Needs and Social Order. USA: Schocken Book Inc, 1966.

Glassie, Henery. Material Culture. Bloomington: Indiana University Press, 1999.

Goldstein, Kenneth. A Guide for Field Workers in Folklore. USA: Folklore Association Inc, 1964.

Jan, Vansina. Oral Tradition as History. USA: The University of Wisconsin Press, 1985.

Jerome, Smith. "Social Folk Custom of Festivals and Celebrations" in Richard Dorson. (ed). Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Jones, Michael Owen (ed). Putting Folklore to Use. Kentucky:The University Press of Kentucky, 1994.

________. "Concepts and Perspectives in Folk Art and Material Culture" Handbook of American Folklore. Bloomington: Indiana University Press, (1983): PP 11-12.

Kefyalew Merahi. The Most Versatile Ethiopian Scholar St. Yared and His Out Standing Works. Addis Ababa: Commercial Printing Press, 2004.

Korem Finance and Economic Development Office Five Year Strategic Plan, 1999-2003. (Unpublished).

Korem Municipal Office Annual Report. 2000 E.C. (Unpublished).

Korem Town Trade, Industry and Transport Bureau, 2003. ( Unpublished).

Kottak, P, Conrad. Cultural Anthropology. New York: Oxford University Press, 2002.

Levinson, David and Ember Melvin, ed. "Feasts and Festivals" Encyclopedia of Cultural Anthropology. Vol 2 Calvene Ceville: Red Sea Press, 1994.

Mackdonald, Donald A. "Field Work: Collecting Oral Literature" in Richard Dorson (ed), Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Maria Leach. (ed). Standard Dictionary of Folklore and Legend. New York: Publisher, p 398-503, 1949.

Martha, C. Sims, and Stephens Martine. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions. Ohio: The Ohio State University: Utah State University Press, 2005.

National Urban Planning Inistitute, Report on Development Plan of Korem Town, addis ababa, 1998. (Unpublished).

Offla Woreda Administration. Opportunities of Offla Woreda (first draft), Technical Team, Korem, 2001. (Unpublished)

Oring, Elliot. Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction, Utha: Utah University Press, 1986.

Pankhurst, Silvia.Ethiopian a Cultural History.Essex:Lalibela Houhse,1995.

Rapport, Roya. Ritual and Religion in the Making of Humanity. UK: United Kingdom at the University Press, Cambridge, 1999.

Richard M. Dorson (ed.) Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Ritezer, George. Sociological Theory. Singapore: The Singapore University Press, 2000.

Sergew Habile Sellassie. The Church of Ethiopia, a Panaroma of History and Spritual Life. Addis Ababa : The Ethiopian Orthodox Church United Printers, 1970.

Shipley, J.T. A Dictionary of World Literary Terms. Boston, The Writers' Inc Publisher, 1970.

Tigray Region the 1994 Population and Housing Census Commission (PHCC) of Ethiopia: Results for the Tigray Region, vol 1, part II,

Statistical Report on Education and Economic Activity, AA, CSA, 1996.

Ullendorff, Edward. The Ethiopians: An Introduction to Country and People. London: Oxford University Press, 1966.

Wallelgen Emiru. "The Dynamic of Religious Rituals and Secular Ceremonies in Public Places of Addis Ababa (Spatial, Temporal and Symbolic Aspects), MA Thesis Department of Social Anthropology , Addis Ababa University 2003.

William, Bascom. Context in Context. London: The University of Chicago Press, 1986.

# አባሪ አንድ

## የመረጃ ሰጪዎች አጭር ገለፃ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | እድሜ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ጊዜ | የመረጃ ሰጪዎች የሥራ መስክ አጭር ገለፃ | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህር ዮሐንስ ግርማይ | 52 | ሚያዚያ | በኮረም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በመምህርነት እያገለገሉ ሲሆን በቅኔ ተመርቀዋል። በዚህም ወንበር ዘርግተው ለአስራ አምስት አመታት ያስተማሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደ ሃምሳ የሚጠጉ የአብነት ተማሪዎች አሏቸው። ከዚህ በተጨማሪ በስብከተ ወንጌል ያገለግላሉ። (አውራ መረጃ ሰጪ) | 01 ቀበሌ |
| 2 | መምህር ዳንኤል አየነው | 60 | ✓ | በኮረም አቡን አረጋዊ ቤተክርስቲያን በመምህርት የሚያገለግሉ ሲሆን በዝማሬ መዋስዕት ተመርቀዋል። በዚህም ወንበር ዘርግተው ለብዙ ዓመታት ያስተማሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደ ሰላሳ የሚጠጉ የዜማ ተማሪዎች አሏቸው። ሙሉ ስልጣነ ክህነት አላቸው። ከዚህም በተጨማሪ በአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን በስከተ ወንጌል ያገለግላሉ። (ቁልፍ መረጃ ሰጪ) | 03 ቀበሌ |
| 3 | መምህር ብርሃነ ሕይወት በፅሐ | 50 | ✓ | በኮረም ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን በመምህርነት እያገለገሉ ሲሆን በአቋቋም ትምህርት ተመርቀዋል። ወንበር ዘርግተው ለተከታታይ 8 አመታት ያስተማሩ ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት 20 የአብነት ተማሪዎች አሏቸው። ቋሚ የድብሩ የአቋቋም መምህር ናቸው። (ቁልፍ መረጃ ሰጪ) | 02 ቀበሌ |
| 4 | መሪጌታ ተክለብረሃን ሐይሉ | 74 | ✓ | በኮረም ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን በመሪጌታነት እያገለገሉ ሲሆን በአቋቋምና ዝማሬ መዋስዕት ተመርቀዋል። | 02 ቀበሌ |
| 5 | ሊቀ ትጉሃን ሞላ አየነው | 55 | ✓ | የኮረም ወረዳ ቤተክህነት ስብከተ ወንጌል ሐላፊና ም/ስራ አስኪያጅ ናቸው። በስብከተ ወንጌል ያገለግላሉ። የተያዩ የስነ መለኮት ስልጠናዎች በመቀሌ፣ በአዲስ አበባ ሰልጥነዋል። የወረዳው ሰንበት ትምህር ቤቶች የበላይ ኃላፊ ናቸው። (ቁልፍ መረጃ ሰጪ) | 01 ቀበሌ |
| 6 | ሊቀ ትጉሃን ፀዳል ካሳው | 55 | ✓ | በኮረም ደብረ ሠላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እያገለገሉ ሲሆን በዜማ ትምህርት ተመርቀዋል። ለ10 ዓመታት ወንበር ዘርግተው ተማሪዎች ያስተማሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደ 30 የሚጠጉ የአብነት ተማሪዎች አሏቸው። የሰበካ ጉባኤ አባል በመሆን ለ3 ዓመታት አገልግለዋል። | የፅግአ ሚካኤል ገበሬ ማህበር |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | መላከ ሕይወት አበራ አወቀ | 60 | ✓ | የኮረም ወረዳ ቤተ ክህነት መዝገብ ቤትና ገንዘብ ያዥ ሲሆኑ በስብከተ ወንጌል ቤተክርስቲያንን ያገለግላሉ። ወደ ኮረም ከመዘዋወራቸው በፊት በማይጨው ሀገረ ስብከት የወረዳው ም/ስራ አስኪያጅ ሆነው አገልግለዋል። | 01 ቀበሌ |
| 8 | መሪጌታ አብርሃ አፍለኝ | 80 | ✓ | በኮረም በደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን ለ40 ዓመታት ያህል በመሪጌታነት አገልግለዋል። በአቋቋምና በዜማ ትምህርት ተምረው ተመርቀዋል። | 02 ቀበሌ |
| 9 | መሪጌታ ይባቤ አድሄና | 36 | ✓ | በኮረም ደብረ ሠላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እያገለገሉ ሲሆን በቅዳሴ ትምህርት ተመርቀዋል። የአቋቋም ትምህርትም ተምረዋል። | 03 ቀበሌ |
| 10 | መሪጌታ ንጉስ ሐፍቱ | 40 | ✓ | በኮረም ኮንዶሚኒየም ቤቶች ኤጀንሲ የሎጂስቲ ባለሙያ ናቸው። ዜማ፣ ቅኔ አቋቋም ተምረዋል። በትርፍ ጊዜያቸው ቤተክርስቲያንን ያገለግላሉ። | 01 ቀበሌ |
| 11 | መሪጌታ ጥዑመልሳን ሞላ | 35 | ✓ | በኮረም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በዜማና በአቋቋም ትምህርት መደበኛ አገልጋይ የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን የትርፍ ጊዜ አገልጋይ ናቸው። | 03 ቀበሌ |
| 12 | ቀሲስ ሐይሉ አምባዬ | 36 | ✓ | በኮረም በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በስብከተ ወንጌል የሚያገለግሉ ሲሆን በመቀሌ የስነ መለኮት ትምህርት ተምረው ተመርቀዋል። በቅስና ማዕረግ በበአለ እግዜአብሔር ቤተክርስቲያን እያገለገሉ ይገኛሉ። በኮረም ጤና ጣቢያ የስነ ተዋልዶ ባለሙያ ናቸው። | 03 ቀበሌ |
| 13 | አፈ መምህር ዘውዴ | 84 | ✓ | በኮረም ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያን በሊቀ ዲያቆንነት፣ በሰበካ ጉባኤ ሰብሳቢነት እና በቤተክርስቲያን አሰሪነት ቤተክርስቲያንን በማገልግል ላይ ይገኛሉ። | 01 ቀበሌ |
| 14 | እማሆይ ብርሃኔ ደርበው | 80 | ✓ | በኮረም ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ለ40 ዓመታት በዓቃቢነት አገልግለዋል። | 02 ቀበሌ |
| 15 | ወ/ሮ ዝማም ደመወዜ | 55 | ✓ | በኮረም በሚገኙ አብያተ ቤተክርስቲያናት የጽዋ ማህበራት በማስተባበር እና ለአብያተ ክርስቲያናት ህንፃ ማሰሪያ የሚውል ገንዘብ በመሰብሰብ ያገለግላሉ። | 02 ቀበሌ |
| 16 | አቶ አየለ ክልካይ | 86 | ✓ | የኮረም ደብረ ገነት ሐያሎ ማርያም ቤተክርስቲያነ አመሰራረት፣ እድገትና ታሪክ የሚያውቁ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የወረዳው አመሰራረት ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና አካባቢያዊ መረጃዎችን የሚያውቁ ናቸው። | ማዕዶ ኮረም ገበሬ ማህበር |

## አባሪ ሁለት

## በኮረም አብያተ ክርስቲያናት በሥርዓተ ማኅሌት ለሚያገለግሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የተዘጋጁ ዋናዋና የቃል ጥያቄዎች

ስሜ ተስፋዬ ሞላ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ነኝ፡፡ የማጠናው የጥናት ርዕስ "የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ በኮረም" የሚል ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በዓሉ እየተከበረ ባለበት ሁኔታ በቪ.ዱዮ፣ በፎቶ ግራፍና በቴፕ በመቅረፅ፣ በፅሑፍ በማቅረብ የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ተግባራትን በማስረዳት እና በማሳወቅ ካለንበት ዘመን ወደሚቀጥለው ዘመን እንዲተላለፍ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ ለዚህ ጥናት መሳካት የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ሃሳብዎትን ያለምንም ፍርሐትና ጥርጣሬ እንዲገልፁልኝ አለምናለሁ፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት ያልገባዎት ነገር ካለ መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን በቃለ መጠይቁ ወቅት ቴፕ የምጠቀመውም የሚሰጡኝን መረጃ በጽሑፍ ለማስፈር እንዲረዳኝ እንጂ ከዚህ ውጭ ሌላ ዓላማ የሌለው መሆኑን እንድያውቁልኝ በቅድሚያ አሳስባለሁ፡፡

ለሚሰጡኝ ጠቃሚ መረጃና ላደረጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

1. ስምዎን፣ ዕድሜዎን(የተወለዱበት ጊዜና ቦታ) እና የሥራ ኃላፊነትዎን ቢገልፁልኝ?
2. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስንት የበዓላት አካባበር አሉ? ከሐይማኖቱ ስርዓት አኳያ የበዓላቱ አካባበር ምን ገጽታ አለው?
3. ሐይማኖታዊ በዓላት ከሌሎች በዓላት በምን ይለያሉ?
4. የሥርዓተ ማኅሌት አይነቶች ስንት ናቸው? ቢዘረዘረልኝ፡፡ እነዚህ የሥርዓተ ማኅሌት አይነቶች በምን ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ?
5. የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት ከዘወትር የማኅሌት አይነቶች በምን ይለያሉ? በውስጣቸው ምን ምን ጉዳዮች ያጠቃልላሉ? ያላቸው ትዕምርታዊ ውክልና ምንድን ነው?
6. የሥርዓተ ማኅሌት ደረጃዎች ስንት ናቸው? ቢዘረዝሩልኝ፡፡ ምንምን ተምሳሌታዊ (ትዕምርታዊ) ውክልና አላቸው?
7. የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት የተጀመረው መቼ ነው? ማን ጀመረው? ሲጀመር ምን አይነት ገጽታ ነበረው?
8. አቋቋም ምንድን ነው? አቋቋምስ ለምን ተባለ?
9. የሥርአተ ማኅሌት አቋቋም በቅደም ተከተል ቢነግሩኝ፡፡ ምን ይቀድማል? ምን ይከተላል? ስንት ካህናት ያስረግጣሉ? ተምሳሌታዊ (ትዕምርታዊ) ውክልናው ምንድን ነው?
10. በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት የሚሳተፉ አካላት እነማን ናቸው? ድርሻቸውስ ምንድን ነው?
11. ንዋየተ ቅዱሳት ማለት ምን ማለት ነው? ምን ምንስ ያጠቃልላል? ከእነዚህ ሥርዓተ ማኅሌትን ለመከወኛ የሚያገለግሉ የትኞቹ ናቸው? ትዕምርታዊ ውክልናቸውስ ምንድን ነው?
12. ምሳሌና ንዋያተ ቅድሳት የሚያገናኛቸው ነገር ምንድን ነው?
13. የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ጠቀሜታ ምንድንነው? ለካህናት፣ ለምዕመናን፣ ለቤተክርስቲያን፣ ለሃገር፡፡
14. የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት በሂደት ያሳየው ለውጥ ካለ ቢገልፁልኝ፡፡
15. ሥርዓተ ማኅሌት ሐይማኖታዊ ገፅታ ብቻ ነው ያለው ይላሉ? ወይስ ሌሎች ገፅታዎች አሉት?
16. ሥርዓተ ማኅሌት ሐይማኖታዊ ገፅታውን ሳይለቅ በቀጣይነት እንዲከበር ምን መደረግ ይገባዋል ይላሉ?

~~አባሪ ሶስት~~

## በኮረም አብያተ ክርስቲያናት በሥርዓተ ማኅሌት ለሚሳተፉ ምዕመናን የተዘጋጁ ዋናዋና የቃል ጥያቄዎች

ስሜ ተስፋዬ ሞላ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ነኝ፡፡ የማጠናው የጥናት ርዕስ "የክብረ በዓላት ሥርዓተ ማኅሌት አቋቋምና ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ በኮረም" የሚል ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በዓሉ እየተከበረ ባለበት ሁኔታ በቪዲዮ፣ በፎቶ ግራፍና በቴፕ በመቅረፅ፣ በፅሑፍ በማቅረብ የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ተግባራትን በማስረዳት እና በማሳወቅ ካለንበት ዘመን ወደሚቀጥለው ዘመን እንዲተላለፍ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ ለዚህ ጥናት መሳካት የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ሃሳብዎትን ያለምንም ፍርሐትና ጥርጣሬ እንዲገልፁልኝ እለምናለሁ፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት ያልገባዎት ነገር ካለ መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን በቃለ መጠይቁ ወቅት ቴፕ የምጠቀመውም የሚሰጡኝን መረጃ በጽሑፍ ለማስፈር እንዲረዳኝ እንጂ ከዚህ ውጭ ሌላ ዓላማ የሌለው መሆኑን እንድያውቁልኝ በቅድሚያ አሳስባለሁ፡፡

ለሚሰጡኝ ጠቃሚ መረጃና ላደረጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

1. ስምዎን፣ ዕድሜዎን(የተወለዱበት ጊዜና ቦታ) እና የሥራ ኃላፊነትዎን ቢገልፁልኝ?
2. ከሁሉም የቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ኪዳን፣ ቅዳሴ፣ ሰዓታትና ማሕሌት የትኛው ደስ ይለዎታል? ለምን?
3. ማኅሌት በቀንና በሌሊት የሚፈፀም የቤተክርስቲያን አገልግሎት ነው፡፡ በቀንና በሌሊት እየመጡ በሥርዓተ ማኅሌት አገልግለት ይሳተፋሉ? ምን አይነት ጥቅም አገኛለሁ ብለው ነው?
4. የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ሐይማኖታዊ ገፅታ ብቻ ነው ያለው ይላሉ? ነው ወይስ ሌሎችም ገፅታዎች አሉት?
5. በሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት የምዕመናን ድርሻ ምንድን ነው? እርስዎ የስርዓቱ ተሳታፊ በመሆንዎ ምን ድርሻ አለኝ ይላሉ?
6. በእርስዎ አመለካከት የሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ ነው ወይስ የነበረውን የድሮ ገፅታ ይዞ እየቀጠለ ነው ይላሉ? ለምን?
7. ለሥርዓተ ማኅሌት አገልግሎት መከወኛ የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅዱሳት ምንምን ናቸው? ምን ዓይነት ሐይማኖታዊ ትርጓሜስ አላቸው ይላሉ?

አባሪ ሦስት



ሊቃውንቱ የበዓለ ትንሣኤ ሥርዓተ ማህሌት ቀለም ሲከውኑ



ሊቃውንቱ በበዓለ ትንሣኤ ሥርዓተ ማህሌት የተቆመው ቀለም ሲያመረግድ



የኮረም ኃያሉ ማርያም ቤተክርስቲያን



ሊቃውንቱ በኮረም ኃያሉ ማርያም ቤተክርስቲያን በሥርዓተ ማህሌት ክዋኔ ዝማሜ ሲያገርጉ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አባሪ ሥዕሎች



የኮረም ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን



በኮረም ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንቱ ሥርዓተ ማህሌት ሲያከናውኑ የሚያሳይ



ምዕመናን በሥርዓተ ማህሌት ክዋኔ ዑደት ሲያደርጉ



ሊቃውንቱ በሥርዓተ ማህሌት ክዋኔ ዑደት ሲያደርጉ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ቤት ፅሕፈት ምምሕዳር ከተማ ኮረም

KOREM TOWN ADMINSSTRATION OFFICE

ቁፅሪ 4ደ/ኮም1/2003
REF.NO

ዕለት 11 /08/ 2003 ዓ/ም
DATE

ናብ ቤት ፅሕፈት ከ/ል/ን/ኢንዳስትሪን

ኮረም፣

ዋኒኑ፦ ብዛዕባ ድጋፍ ደብዳቤ ምሃብ ይምልከት፣

ኣብ ርእሱ ከምዝተጠቐሰ ኣብ ዩኒቨርስቲ ኣዲስ ኣበባ ተምሃራይ ተስፋይ ሞላ ናይ 2ይ ድግሪ ተምሃሪ ምኧኑን ናይ መመረቒ ፅሑፍ ከተማና ማእኸል ዝገበረ ከካይድ ከምዝተልኣኸ ብዕለት 01/07/2003 ዓ.ም ካብ ዝፀሓፎ ደብዳቤ ምርዳእ ኪኢልና ኣለና። ስለዚ እቲ ዕንዓት ንከተማና ዝህልዎ ረብሓ ግምት ውሽጢ ብምእታው ምስ ናይ 10ተ ዓመት ዕብየት ፕላን ዝተኣሳሰረ ሙሉእ መረዳእታ ስለዘሎ ዘድሊዮም ንክወስዱ መረዳእታ ኣብ ምሃብ ክተተሓባበርዎም እዚ ድጋፍ ደብዳቤ ዝሃብናዮም ምኧና ንሕብር።

"ምስ ሰላምታ"

[illegible]ይለ ምስጉን

ም/ከንቲባን ሓላፊ ት/ቲን

ቅዳሕ

ንተምሃራይ ተስፋይ ሞላ

ኮረም፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

☏ 034 551 00 22/712 ፋክስ 034 551 03 68

ቁጥር [illegible]/2003

ቀን 01/09/2003 ዓ.ም

ለ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የኢተዮጰያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ጉዳዩ ፡- <u>የድጋፍ ደብዳቤ ስለመስጠት ይመለከታል</u>

ተማሪ ተስፋዬ ሞላ በአዲስ ኣበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጰያ ስነፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የሁለተኛ ድግሪ ተማሪ መሆኑን እና «የክብረ በዓላት ስርዓት ማህሌት አቋቋምና ክዋኔ ፎክሎራዊ ገፅታ» በሚል ርእስ የመመረቂያ ፅሑፍ ሊያጠና እንደመጣ በ 01/07/2003 ዓ.ም ካመለከተው ሕጋዊ ደብዳቤ መረዳት ችለናል ፡፡ በመሆኑም ተማሪ ተስፋዬ ሞላ በኮረም አብያተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን ፣የአብያተ ክርስቲያናቱ ታሪክ የሚያወቁ ግለሰቦችን ፣ በአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙ መፃሕፍቶችን በመዳሰስ እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናቱ በመገኘት የማሕሌቱ ስርዓተ አገልግሎት በቪድዮ እና በፎቶ ግራፍ በማስደገፍ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አጠናክሯል ። ጥናቱ ተጠናቅቆ ለውጤት እንዲበቃ መልካም ምኞታችን እየገለፅን መረጃዎቹ ከሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በቃለ መጠይቅ እና በቤተክርስትያኑ ከሚገኙ መፃሕፍት፣ ከታሪክ አዋቂዎች ጠይቆ እንደሰራ የሚገልፅ ይህንን የድጋፍ ደብዳቤ የፃፍንለት መሆናችንን እገልፃለን ፡፡

ከሰላምታ ጋር

መልአከ [illegible]

አስተዳዳሪ

<u>ግልባጭ</u>

✓ ለተማሪ ተስፋዬ ሞላ

ቤት ፅሕፈት ልምዓት ከተማ ንግድን ኢንዱስትሪን ከተማ ኮረም
KOREM URBAN DEVELOPMENT,TRADE & INDUSTRY OFFICE

BELAY SHORT DOCMENT.doc

ቁጥር ም/መ/መ/መ/፪50/2003

ቀን 01/09/2003 ዓ.ም

ለ አዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢተዮጲያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ጉዳዩ ፦ የድጋፍ ደብዳቤ ስለመስጠት ይመለከታል

ከላይ ከርእሱ እንደተገለፀው ተማሪ ተስፋዬ ሞላ በኣዲስ ኣበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ስነፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የሁለተኛ ድግሪ ተማሪ መሆኑን እና የመመረቂያ ፅሁፉን ከተማችን ማእከል ያደረገ ጥናት ሊያጠና እንደመጣ በ 01/07/2003 ዓ.ም ካመለከተው ደብዳቤ መረዳት ችለናል ፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ለከተማችን የሚሰጠው ኣስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ጠቃሚ የፅሁፍ መረጃዎች እና ሲዲ ሰጥተነዋል ፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ተጠናቅቆ ለወገን እና ለሃገር እንዲበቃ መልካም ሞኞታችን እየገለፅን ተማሪ ተስፋዬ ሞላ ጥናቱን በኮረም ከተማ ማእኸል በማድረግ እንዳጠና የሚያረጋግጥ ይህንን የድጋፍ ደብዳቤ የፃፍንለት መሆናችን እገልፃለን ፡፡


ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ


✓ ለተማሪ ተስፋዬ ሞላ

አባሪ አምስት


የሥርዓተ ማኅሌት መሣሪያ ንዋያተ መዝሙሮች



8 ጸናጽል



2. ከበሮ



መቋሚያ